الطريق إلى السعادة
The Path to Happiness

https://www.path-2-happiness.com/am




# ዘላለማዊው መልእክት

## ማውጫ

ዘላለማዊው መልእክት

ከነቢይነታቸው ﷺ ማረጋገጫዎች ጥቂቱ
የነቢይነት ድምዳሜ፦
ለዓለማት ሁሉ እዝነት፦
በነቢዩ ﷺ መላክ መላው የሰው ዘር መታደሉ ፦
የዘላለማዊው መልክት መጠሪያ ስም ምንድን ነው?
ዘላለማዊው መልክት ለመላው ዩኒቨርስ ጭምር ነው፦
ዘላለማዊው መልክት የሁሉም ነቢያትና መልክተኞች ሃይማኖት ነው፦
የዘላለማዊው መልክት ምሉእነት፦
የሕግና ድንጋጌ አወጣጥ መሰረቶች
የእስላማዊ ድንጋጌ መለያ ባሕርያት
እስላማዊው ሸሪዓና ሰው ሠራሽ ሕግጋት . . ልዩነቶችና ተቃርኖዎች
የእሰላም ምንጮች



# ዘላለማዊው መልእክት

ሰዎች ከመለኮታዊ መመሪያና ከነቢያት ተልእኮ በራቁ ቁጥር ዕድለቢስነትና ጨለማ በሰው ልጆች ሕይወት ላይ ያጠላሉ:: አላህም መልክተኞቹን አከታትሎ ይልካል፦

{رُّسُلًا مُّبَشِّرِينَ وَمُنذِرِينَ لِئَلَّا يَكُونَ لِلنَّاسِ عَلَى ٱللَّهِ حُجَّةٌۢ بَعْدَ ٱلرُّسُلِ ۚ وَكَانَ ٱللَّهُ عَزِيزًا حَكِيمًا ﴿١٦٥﴾}[النساء: ١٦٥].

‹‹ከመልክተኞቹ በኋላ ለሰዎች በአላህ ላይ አስረጅ እንዳይኖር፣አብሳሪዎችና አስጠንቃቂዎች የኾኑን መልክተኞች (ላክን)፤አላህም አሸናፊ ጥበበኛ ነው::››[አል ኒሳእ:165] አላህ መልክተኛ ሳይልክላቸው ማንንም አይቀጣም፦

{وَمَا كُنَّا مُعَذِّبِينَ حَتَّىٰ نَبْعَثَ رَسُولًا ﴿١٥﴾}[الإسراء: ١٥]،

‹‹መልክተኛንም እስከምንልክ ድረስ የምንቀጣ አይደለንም::››[አል እሰራእ:165]

ዒሳ عليه السلام ከተላኩና አላህ (ሱ.ወ.) ወደራሱ ካነሳቸው በኋላ የሰው ልጆች በማይምነት፣በጥመት፣በግፍና በጨለማ ተዋጡ:: መለኮታዊ ሃይማኖቶችም የጠራውን የተውሒድ እምነት በጣዖታዊነትና በሽርክ በለወጡ አጥፊዎች አማካይነት ለመዛበት ለመጣመምና ለክለሳ አደጋዎች ተጋለጡ:: ለአላህ ኃያልነትና ለተውሒዱ ተጻራሪ የሆኑ እምነቶችን በማራመድና ተገቢ ያልሆኑ ባሕርያትን ለርሱ በመስጠት ረገድ በአምልኮም ሆነ በአነዋነዋር በመጽሐፉ ባለቤቶችና በጣዖታውያን ሙሽሪኮች መካከል ልዩነት አልነበረም:: በዚህ ግዙፍ የሽርክ፣የኤቲዝም፣የአላህን ቃልና መለኮታዊ መጽሐፎችን የማዛባትና የመለዋወጥ ማዕበል ውስጥ፣የመጽሐፉ ባለቤቶች የአላህን ኪዳንና የአላህን ቃል በግድ የለሽነት ከጀርባቸው ኋላ በመጣላቸው፣እውነቱን ደብቀው ሐሰትን በግልጽ በመንዛታቸው፣የአላህን እገዳዎች በመጣስ የአላህን መብቶችና የፍጡራንን መብቶች በመጣሳቸው፣ግላዊ ጥቅሞቻቸውን ከእውነት ያበለጡ መሪዎቻቸውና ካህኖቻቸው እንዳደረጉት ሁሉ የሚያውቁትን እውነት ለገንዘብና ለሹመት በመለወጣቸው . . አውዳሚ ጦርነቶች ተስፋፉ፤አምባገነንነት ሰፈነ:: የሰው ልጆች በክህደትና በአለዐዋቂነት ምክንያት ልቦናን ባጠቆረ ድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ለመኖር ተገደዱ:: መልካም ስነምግባር ጨቀየ፤ሰብአዊ ክብርም ተዋረደ፤በምድሪቱ ላይ ጥፋት ተዛመተ:: በዘመኑ መንገዱን ለሰው ልጆች ሊያበራና ወደ ቀጥተኛው ጎዳና ይመራቸው ዘንድ የነቢይነትን ችቦ ያነገበ፣የቅን መመሪያን ብርሃን የያዘ ታላቅ የለውጥ አራማጅ መሪን በመላክ አላህ (ሱ.ወ.) ካልታደገው በስተቀር ሰብአዊነት በጣእረ ሞት ውስጥ መሆኑን፣ለውድመትና ለጥፋት መቃረቡን ዘመኑን ያስተዋለ ሰው በቀላሉ ይረዳል::

የሰው ልጆች በዚህ ጽልመታዊ ሁኔታ ውስጥ እያሉ ነበር አላህ ነቢዩን ﷺየላካቸው:: መልክተኛው ይሆኑ ዘንድም ሙሐመድን ﷺ መረጣቸው፦

{ رَّسُولَ ٱللَّهِ وَخَاتَمَ ٱلنَّبِيِّـۧنَ ۗ}[الأحزاب: ٤٠]،

ያሚደምደመ ችዮቢነየ ናኛተክልመ ህላአየ››
‹‹፤ውነ[አል አሕዛብ:40]

ከነቢዩም ጋር መላውን የሰው ዘር ከጥመትና ካለመታደል የሚታደገውን መሪ ብርሃንም ላከ:: በዚህም ይህን ሃይማኖት ምሉእ አድርጎ ለሰው ልጆች የለገሰውን ታላቅ ጸጋውን አዳረሰ:: ነቢዩም ﷺ ይህን ዘላለማዊ እውነታ ለዓለማት ሁሉ ተደራሽ ለማድረግ በጽናት ታገሉ፦

{وَمَآ أَرْسَلْنَٰكَ إِلَّا رَحْمَةً لِّلْعَٰلَمِينَ ﴿١٠٧﴾}[الأنبياء: ١٠٧]،

‹‹(ሙሐመድ ሆይ!) ለዓለማትም እዝነት አድርገን እንጅ አልላክንህም::››[አል አንቢያ:107]

ዓለማት ሁሉ የመታደልን መንገድ ይከተሉ ዘንድ በእዝነትና በርኅራሄ ተላኩ::



### ኃያል ክስተት

‹‹በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ የተከሰተ ከሁነቶች ሁሉ ይበልጥ የበለጸገ አንድ ሁነት ይገኛል፤እርሱም የእስላም መምጣት ነው::››

ጆርጅ ሳርቶን

በዋሽንግተንና በሃርቫርድ ዩኒቨርሲቲዎች ሌክቸረር

https://www.path-2-happiness.com/am



ለሰው ልጆች የዘላለማዊ ተድላና የደስተኝነት መንገድን ለማሳየት ላደረጉት ታላቅ ተጋድሎ ከማንም ሰው ዋጋም ሆነ ወሮታ ፈላጊ አልነበሩም። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

‹‹የሙሐመድን ሕይወት የመሰለ ሕይወት፣የአስተውሎት የፍካሬና የትግል ኃይሉን የመሰለ ኃይል፣በአገሩ አልባሌ ወግና ልማድ በሕዝቦቹ ማይምነት ላይ መዝመቱ፣የጣዖታት አምላኪዎችን ሲጋፈጥ ያሳየው ብርታትና ጀግንነት፣የአላህን ቃል ከፍ ማድረጉ፣የእሰላምን የእምነት ማእዘናት ለማጽናት ያሳየው ብርታትና ጽናት . . ይህ ሁሉ ድብቅ ዓላማ ያለውና ማጭበርበር የሚፈልግ ወይም በሐሰት ለማደር የሚያቅድ ላላመሆኑ ትልቅ ማስረጃ ነው። [ሙሐመድ] ፈላስፋ ነው፤ዲስኩረኛ ነው፤መልክተኛ ነቢይ ነው፤ሕግ አውጭ ነው። የሰው ልጆችን ወደ እሳቤና ወደ አስተዋይነት የመራ መሪ ነው። ክህደት የሌለበት ሃይማኖት መስራች ነው። በምድር ላይ የሃያ መንግስታት መስራች ነው። በሰማይም የመንፈሳዊ መንግስት በር ከፋች ነው። እርሱ ከደረሰበት የሰብአዊ ፍጡር ታላቅነት ደረጃ ማን ደርሶ!! እርሱ ከደረሰበት የምጥቀትና የምሉእነት ደረጃ ማን ቀርቦ!!››

{قُلۡ مَآ أَسۡـَٔلُكُمۡ عَلَيۡهِ مِنۡ أَجۡرٖ وَمَآ أَنَا۠ مِنَ ٱلۡمُتَكَلِّفِينَ ﴿٨٦﴾} [ص: ٨٦]

‹‹በላቸው፦ በርሱ ላይ ምንም ዋጋ አልጠይቃችሁም፤እኔም ከተግደርዳሪዎቹ አይደለሁም።››[ሷድ፡ 86]

ይልቅዬ ፈጣሪ አምላካቸው ንጉሥ መልክተኛ ከመሆንና አገልጋይ መልክተኛ ከመሆን አማርጧቸው የአላህ አገልጋይ ባሪያውና መልክተኛው መሆንን መርጠዋል። በመሆኑም ነቢዩ ﷺ እንደማንኛውም ሰው ሰብአዊ ሕይወትን ነበር የኖሩት፤ባልደረቦቻቸው እንደሚራቡ የሚራቡ፣እነሱ እንደሚቆስሉ የሚቆስሉም ነበሩ፤አብሯቸው ይሠሩም ነበር፤የአላህ ባሪያና አገልጋዩ በመሆናቸውም ይኮሩ ነበር፤ጌታቸው አላህም (ሱ.ወ.) ሲያከብራቸውና እርሱ ዘንድ የመጨረሻው ክቡር ደረጃ በሆነው ማዕረግ ‹‹ባሪያችን›› በማለት ነው የጠራቸው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦



### ታላቁ ድንቅ ዜና

‹‹ከዚያ ዘመን በፊት በማይታወቅ ሕዝብና ምንም ግምት በማይሰጠው አገር ውስጥ የእስላም መነሳት ዜና በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ የተመዘገበ እጅግ ታላቁ ድንቅ ዜና ነው ማለት ይቻላል። በሰፋፊ የምድር ክፍል የተንሰራፉ ታላላቅ ኢምፓይሮችን ገርስሶ፣ዘመናትን ያስቆጠሩ ጥንታዊ ሃይማኖቶችን አስወግዶ፣በሕዝቦች ልቦና ያለውን አስተሳሰብ ለውጦ በመሰራጨት፣ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ የተዘረጋውን የእስላም ዓለም በግማሹ የዓለም ክፍል ለመገንባት አስር አስርት ዓመታት አልፈጀበትም።››

**ሎሥሮብ እስቶታርድ**

**አሜሪካዊ ጸሐፊ**



### የዓለማት እዝነትና በረከት

‹‹የሙሐመድን ሕይወት የመሰለ ሕይወት፣የአስተውሎት የፍካሬና የትግል ኃይሉን የመሰለ ኃይል፣በአገሩ አልባሌ ወግና ልማድ በሕዝቦቹ ማይምነት ላይ መዝመቱ፣የጣዖታት አምላኪዎችን ሲጋፈጥ ያሳየው ብርታትና ጀግንነት፣የአላህን ቃል ከፍ ማድረጉ፣የእሰላምን የእምነት ማእዘናት ለማጽናት ያሳየው ብርታትና ጽናት . . ይህ ሁሉ ድብቅ ዓላማ ያለውና ማጭበርበር የሚፈልግ ወይም በሐሰት ለማደር የሚያቅድ ላላመሆኑ ትልቅ ማስረጃ ነው። [ሙሐመድ] ፈላስፋ ነው፤ዲስኩረኛ ነው፤መልክተኛ ነቢይ ነው፤ሕግ አውጭ ነው። የሰው ልጆችን ወደ እሳቤና ወደ አስተዋይነት የመራ መሪ ነው። ክህደት የሌለበት ሃይማኖት መስራች ነው። በምድር ላይ የሃያ መንግስታት መስራች ነው። በሰማይም የመንፈሳዊ መንግስት በር ከፋች ነው። እርሱ ከደረሰበት የሰብአዊ ፍጡር ታላቅነት ደረጃ ማን ደርሶ!! እርሱ ከደረሰበት የምጥቀትና የምሉእነት ደረጃ ማን ቀርቦ!!››

**ላማርቲን**

**ፈረንሳዊ ባለቅኔ**

https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am

{ٱلۡحَمۡدُ لِلَّهِ ٱلَّذِيٓ أَنزَلَ عَلَىٰ عَبۡدِهِ ٱلۡكِتَٰبَ وَلَمۡ يَجۡعَل لَّهُۥ عِوَجَاۜ ١} [الكهف: 1].

‹‹ምስጋና ለአላህ ለዚያ መጽሐፉን፣በውስጡ መጣመምን (መጣታትን ያላደረገበት) ሲኾን በባሪያው ላይ ላወረደው ይገባ::››[አል ከህፍ፡1]

ከዚህም አልፈው ነቢዩ ﷺ ማንም ሰው ከሚገባቸው ያለፈና የተጋነነ ክብር እንዳይሰጣቸው ያስጠነቅቁ ነበር:: ይህን በማስመልከትም እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹ክርስቲያኖች የመርየምን ልጅ (ዒሳን) ከልክ አሳልፈው እንዳሞገሱት ዓይነት አታሞግሱኝ:: እኔ የአላህ ባሪያ እንጅ ሌላ አይደለሁምና፤የአላህ ባሪያና መልክተኛው በሉኝም::›› [በቡኻሪ የተዘገበ] ነቢዩን ﷺ ያያቸውና ያወቃቸው ሰው ሁሉ እውነተኛነታቸውንና ፍጹምነታቸውን ወዲያውኑ ይረዳል፤በክቡር ስነምግባራቸውና በመጠቀ ባህርያቸውም ይመሰጣል:: ይህም ከወዳጆቻቸው በፊት ጠላቶቻቸው፣ከሙስሊሞችም በፊት ከሓዲዎች ራሳቸው አውቀው ምስክርነታቸውን የሰጡበት ጉዳይ ነው! ጌታቸው አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ሲል የመሰከረላቸው መሆኑ ብቻ በቂያቸው ነው፦

{وَإِنَّكَ لَعَلَىٰ خُلُقٍ عَظِيمٖ ٤}[القلم: ٤].

‹‹አንተም በታላቅ ጠባይ ላይ ነህ::››[አልቀለም:4]

አላህ (ሱ.ወ.) የነቢያትና የመልክተኞች መደምደሚያና ማጠቃለያ አድርጎ የመረጣቸው መሆኑ ብቻ ከምንም ምስክርነት በላይ ነው:: ተልእኮአቸው ተሟልቶ ሲጠናቀቅም፣አላህ (ሱ.ወ.) መልክታቸውን ለሰው ልጆች የተላለፈ የመደምደሚያው ዘላለማዊ መልክት አድርጎ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ በማቆየት እሳቸውን ወደራሱ ወስዷቸዋል::



### በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ የታላቆች ታላቅ

‹‹ሙሐመድ በታሪክ ውስጥ እጅግ በላቀና ጉልህ በሆነ መልኩ በሁለቱም ሃይማኖታዊና ዓለማዊ መስኮች አንጸባራቂ ስኬትን ያስመዘገበ ብቸኛው ሰው ነው:: ይህ ወደር የሌለው የሃይማኖታዊና ዓለማዊ ተጽእኖ ፈጣሪነት ልዩ ውሕደት፣በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ታላቁ ተጽእኖ ፈጣሪ ግለሰብ ተደርጎ እንዲወሰድ ያደርገዋል::››

**ማይክል ሃርት**

**አሜሪካዊ ጸሐፊ**

## ከነቢይነታቸው ﷺ ማረጋገጫዎች ጥቂቱ

1- አንድ አላህን (ሱ.ወ.) ብቻ ለማምለክና ከርሱ በስተቀር ሌላ እንዳይመለክ ጥሪ ማድረጋቸው፣በዚህም ከሁሉም ነቢያት ጋር አንድ መሆናቸው አንዱ የነቢይነታቸው ማረጋገጫ ነው:: ሙሳ ዒሳና ሙሐመድ ﷺ ያስተማሩትን ትክክለኛ እምነት፣ሕግጋትና ጠቃሚ ትምርቶችን አነጻጽሮ የተመለከተ ሰው፣ሁሉም ከአንድ ምንጭ ማለትም ከነቢያዊ ምንጭ የተቀዱ መሆናቸውን ይረዳል::



### ከሓዲ እንጂ ማንም አያስተባብለውም

‹‹ሙሐመድ በትክክለኛው የቃሉ ትርጉም እውነተኛው ነቢይ ነው:: ወደ መድህን መንገድ የሚያደርስ መሪ እርሱ መሆኑን ማስተባበል የምንችልበት መንገድም ፈጽሞ የለም::››

**ሃንዝ ኮንጅ**

**ስዊዘርላንዳዊ የስነመለኮት ሊቅ**

2- ለአላህ ነቢያት ብቻ እንጂ የማይከሰቱ ተአምራትና ግልጽ ምልክቶች ያሳዩ መሆናቸው ሌላው ማረጋገጫ ነው::

ለሕዝቦቻቸው አስረጅ ታምርና ለእውነተኛነታቸው ማረጋገጫ ይሆን ዘንድ ከተለምዶ ውጭ የሆነ ትንግርታዊ ነገር በቀደሙት ነቢያት እጅ እንዲከሰት ማድረግ የአላህ (ሱ.ወ.) ሕግ ነበር:: የያንዳንዱ ነቢይ ታምርም የተላከበት ሕዝብ ከተራቀቀበት ነገር ዓይነት ይሆን ነበር:: የነቢዩ ሙሳ عليه السلام ታምር የተላኩበት ሕዝብ የተራቀቀበት ነገር ማለትም ድግምት ነበር:: የነቢዩ ዒሳ عليه السلام ሕዝብ ደግሞ በሕክምናና በመድሃኒት ጉዳዮች የገነነ ስለነበር ለነቢዩ عليه السلام የተሰጣቸው ታምር አስቸጋሪ የሆኑ በሽታዎችን መፈወስና በአላህ (ሱ.ወ.) ፈቃድም ሙታንን እስከማስነሳት የደረሰ ነበር:: እነዚህ በሙሉ ቁሳዊ ታምራት ከመሆናቸውም ባሻገር በጊዜና በቦታ የተገደቡ ነበር:: የዓለም አቀፋዊነትና የቀጣይነት ባሕርይ የላቸውም::

ከነቢዩ ሙሐመድ ﷺ ታምሮች መካከልም መሰል ቁሳዊ ታምሮች ሲገኙ፣ከጣቶቻቸው መካከል ውሃ መፍለቁ፣ጥቂቱ ምግብ አብሯቸው የነበሩ

https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am

ሙስሊሞች እንዲያጠግብ በእጃቸው ላይ መብዛቱና ተርፎም መቅረቱ፣ሰራዊቱ በሙሉ እስኪጠጣና ውዱእ እስኪያደርግ ጥቂቱ ውሃ በዝቶ መበራከቱ፣ለጁሙዓ ኹጥባ ይደገፉበት የነበረው የተምር ግንድ የዲስኩር ማድረጊያ ምንበር ተሰርቶላቸው ሲለዩት ግንዱ እዬዬ ማለቱ፣መካ ውስጥ ድንጋይ ሰላምታ ያቀረበላቸው መሆኑ፣ዛፍ ወደሳቸው መምራቱ፣የአሸዋ በመዳፎቻቸው ውስጥ አላህን ማወደስ፣በአላህ ፈቃድ ሕሙማንን መፈወሳቸውና ሌሎችም ይገኛሉ።

ከነዚያ ቁሳዊ ታምራት መካከል የሌሊት ጉዞና የዕርገትን (የእስራእና የምዕራጅ) ተአምርን ቅዱስ ቁርኣን መዝግቦታል። ተአምሩ በአንድ ሌሊት ከመካው የተከበረ መስጊድ እየሩሳሌም ወደሚገኘው የአልአቅሷ መስጊድ እንዲሄዱና ከዚያ ሰባቱን ሰማያት እስኪያልፉ ድረስ ወደ ሰማየ ሰማያት ማረጋቸውን የሚመለከት ሲሆን አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{سُبۡحَٰنَ ٱلَّذِيٓ أَسۡرَىٰ بِعَبۡدِهِۦ لَيۡلٗا مِّنَ ٱلۡمَسۡجِدِ ٱلۡحَرَامِ إِلَى ٱلۡمَسۡجِدِ ٱلۡأَقۡصَا ٱلَّذِي بَٰرَكۡنَا حَوۡلَهُۥ لِنُرِيَهُۥ مِنۡ ءَايَٰتِنَآۚ إِنَّهُۥ هُوَ ٱلسَّمِيعُ ٱلۡبَصِيرُ ١} [الإسراء:١]

‹‹ከተከበረው መስጊድ፤ወደዚያ ዙሪያውን ወደ ባረክነው ወደ ሩቁ መስጊድ በሌሊት ውስጥ ያስኼደው (ጌታ) ጥራት ይገባው፤ከታምራቶቻችን ልናሳየው፤(አስኼድነው)፤እነሆ እርሱ (አላህ) ሰሚው፣ተመልካቹ ነው።››[አል እስራእ:1]

የጨረቃ ለሁለት መገመስም በቁርኣን የተዘገበ ሌላው ተአምራቸው ነው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{ٱقۡتَرَبَتِ ٱلسَّاعَةُ وَٱنشَقَّ ٱلۡقَمَرُ ١}[القمر: ١]،

‹‹ሰዓቲቱ (የትንሣኤ ቀን) ተቃረበች፤ጨረቃም ተገመሰ፤››[አል ቀመር:1]



## የአላህ ቃል

‹‹ቅዱስ ቁርኣንን አንብቤ ስጨርስ፣ይህ ፍጥረትን ለሚመለከቱና ለሌሎቹም ጥያቄዎች አጥጋቢ ምላሾችን ያካተተ እውነታ ነው የሚል ስሜት ውስጤን አጥለቀለቀው። በተቀሩት ሃይማኖታዊ መጽሐፎች ውስጥ እርስ በርስ ሲጣረሱ የምናገኛቸውን ሁነቶች ሎጂካዊ በሆነ መንገድ ያቀርብልናል። ሁነቶቹ ቁርኣን ውስጥ ሲቀርቡ ድንቅ በሆነ ቅንጅትና መጣጣም፣እውነታው ይህ ስለመሆኑና ይህ ንግግር የግድ ከአላህ ዘንድ ብቻ የተላለፈ ስለመሆኑ ለጥርጣሬ ምንም ቦታ በማይተው ቁርጥ ባለ የአቀራረብ ስልት ነው።››

**ዲቦ ራፖርተር**
**በአሜሪካ የሚታተም ጋዜጣ**

## ይለያል . .

‹‹እንደ እስላም ከዐረባዊው ነቢይ የቀደሙትን ነቢያትና መልክተኞች የሚያከብር ሌላ ሃይማኖት የለም። ነቢያቱን ማክበርና በነርሱ ማመንን በምእመናኑ ላይ ግዴታ አድርጎ ይደነግጋል። በመተላለፍና በመገለጥ ከርሱ የቀደሙትን መለኮታዊ ሃይማኖቶችንም እንደ እስላም የሚያከብር ሌላ ሃይማኖት አይገኝም።››

**ነስሪ ሰልሀብ**
**ሊባኖሳዊ የስነጽሑፍ ሰው**





ጣዖታውያን ሙሽሪኮች ስለ እውነተኛነታቸው ማረጋገጫ የሚሆን ግልጽ ተአምር እንዲያሳዩዋቸው ነቢዩን ﷺ ጠይቀው በዚህ ረገድ


በተለይ ጨረቃን ለሁለት እንድትገመስና ይህን ካደረጉ ለማመን ቃል ገቡላቸው። ዕለቱ ጨረቃ ሙሉ የምትሆንበት የወሩ አስራ አራተኛ ሌሊት ነበር። የአላህ መልክተኛ ﷺ ሰዎቹ የጠየቁትን ታምር ይሰጣቸው ዘንድ አላህን ለመኑትና ጨረቃ ለሁለት ተገመሰች፤ግማሹ በሶፋ ተራራ ግማሹ ደግሞ በትይዩው በሚገኘው የቀይቀዓን ተራራ በላይ ሆና ታየ። ይህ ታላቅ ታምር ከተከሰተ በኋላ ግን የቁረይሽ ሙሽሪኮች ድግምት አድርገው ወሰዱት እንጅ አላመኑበትም። ስልጣናቸው ከሐቅ ፊት መቆም ተስኖት ሲናድ በአላህ ሃይማኖት ያስተባበሉ ሰዎች የሚያደርጉት የተለመደ ተግባር ነው። በዚህ ጊዜ መርሆችን በማጣመም ወይም እውነታን በመደበቅ በሃይማኖቱ ላይ ተንኮል ከመሸረብና ደንቃራ ሆነው ከፊቱ ከመቆም አይመለሱም። ይህን የሚያደርጉትም ሃይማኖቱን ለማጥፋት በቂ መስሎ ስለሚታያቸው ነው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَإِن يَرَوۡاْ ءَايَةٗ يُعۡرِضُواْ وَيَقُولُواْ سِحۡرٞ مُّسۡتَمِرّٞ ٢ وَكَذَّبُواْ وَٱتَّبَعُوٓاْ أَهۡوَآءَهُمۡۚ وَكُلُّ أَمۡرٖ مُّسۡتَقِرّٞ ٣} [القمر: ٢ - ٣].

‹‹ታምርንንም ቢያዩ (ከእምነት) ይዞራሉ፤(ይህ) ዘውታሪ ድግምት ነውም ይላሉ። አስተባበሉም፤ዝንባሌዎቻቸውንም ተከተሉ፤ነገርም ሁሉ (ወሰን አለው)፤ረጊ ነው።››[አል ቀመር:2-3]

3- ቁርኣን፦ ከታምራቶቹ ሁሉ ታላቁ፣ዘመናትን ተሻጋሪና ቀጣይነት ያለው ዘላለማዊ፣ከነቢይነት ማረጋገጫ ምልክቶች አንዱና በጊዜና በስፍራ ያልተገደበ ሕሊናዊ

https://www.path-2-happiness.com/am



**ግልጽ በሆነ የዐረብኛ ቋንቋ**

‹‹ወደኛ ከደረሱ ሰው ሠራሽ ጽሑፎች መረዳት እንደሚቻለው፣መልክተኛው ሙሐመድ በነዚህ ታላላቅ ምዕራፎች ውስጥ የጠቀሳቸው አንቀጾች፣የሰው ልጆችን የቋንቋ ጠበብት በብዙ ርቀት ወደኋላ ጥለው የሚመጥቁ ናቸው::››

**ብላሽር ረጂሽ**

**ፈረንሳዊ ኦሪየንታሊስት**

ተአምር ነው:: ይህም በማያነብና በማይጽፍ ሰው ላይ አላህ (ሱ.ወ.) ያወረደው፣መሰሉን መጽሐፍ ወይም ከምዕራፎቹ አንዱን ምዕራፍ እንኳ እንዲያመጡ ለዐረብ የቋንቋ ሊቆች የአታደርጉትም ፈታኝ ጥያቄ ቀርቦ ማንም ያልመለሰው ተአምራዊና አሸናፊ ሕያው መጽሐፍ በመሆኑ ነው::የቁርኣንን አቻ ሊገኝለት ያልቻለ ኃያል አሸናፊነትና ታምርነት በሐቅ ላይ ያመጸ ትእቢተኛ እንጅ ማንም ሊክድ አይችልም:: በቋንቋ ምጥቀቱ፣በስነጽሑፋዊ ውበቱ፣በአደረጃጀቱና በስልቱ፣እውስጡ ባካተታቸው ያለፉና ወደፊት የሚመጡ ጉዳዮች፣በያዛቸው የጸኑ ሕግጋት፣በተራቀቁ ስነምግባራት፣በቅን መመሪያው፣በብርሃኑና በበረከቱ . . ተአምራዊ ሕያው መጽሐፍ ነው::

ዛሬ እየተደረሰባቸው ያሉትና ቀደም ሲል የሚታወቁ ያልነበሩ ሳይንሳዊ ግኝቶች ቁርኣን ውስጥ ከሰፈሩት እውነታዎች ጋር ሙሉ በሙሉ የሚጣጣሙ ሆነው መገኘታቸውም የነቢዩ ሙሐመድን ﷺ ነቢይነት የሚያረጋግጡ ግልጽ ማስረጃዎች ናቸው:: በዚህ ረገድ ዘመናዊ ሳይንስ ጽንስ በማሕጸን ውስጥ የሚያልፍባቸውን የእድገት ደረጃዎች አስመልክቶ የደረሰበት ግኝት፣በባሕር ጨዋማ ውሃና በመደበኛው ውሃ መካከል መደበላለቅ እንዳይኖር መለያ መኖሩን የሚመለከተውና ሌሎችም





**ቁርኣንና ዘመናዊ ሳይንስ ትከሻ ለትከሻ**

‹‹በቅዱስ ቁርኣን ላይ ጥናት አድርጌያለሁ፤ያጠናሁትም ያለ ምንም ቅድመ ውሳኔ፣የቁርኣን አንቀጾች ከዘመናዊው ሳይንስ ግኝቶች ጋር ምን ያህል እንደሚጣጣሙ ለመመርመር ስል አዎንታዊ በሆነ ነጻ አእምሮ ነው:: በጥናቴም በዛሬው ዘመን ካለው ሳይንሳዊ አመለካከት አንጻር ትችት ሊቀርብበት የሚችል አንድም አባባል ያላካተተ መሆኑን ደርሼበታለሁ::››

**ሞሪስ ቡካይ**

**ፈረንሳዊ ሳይንቲስትና ሐኪም**

ሳይንሳዊ ቁርኣናዊ እውነታዎች ይገኛሉ:: ከሁሉም በላይ ቁርኣን ከአላህ (ሱ.ወ.) ዘንድ የተላለፈ ስለመሆኑ ታላቁ ማስረጃ ለአስራ አራት ምእተ ዓመታት ከመዛባት ከመለዋወጥ፣ከመከለስና ከመበረዝ ተጠብቆ መኖሩና አንባቢው ያሻውን ያህል ቢደጋግመው ፈጽሞ የማይሰለች መሆኑ ነው:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{إِنَّا نَحۡنُ نَزَّلۡنَا ٱلذِّكۡرَ وَإِنَّا لَهُۥ لَحَٰفِظُونَ ٩}[الحجر: ٩]؛


‹‹እኛ ቁርኣንን እኛው አወረድነው፤እኛም ለርሱ ጠባቂዎቹ ነን::››

[አል ሕጅር፡9]

ቁርኣንን በመጠበቁም ትክክለኛውን ዐቂዳ (እምነት) ጠብቋል:: የተሟላ ሕግጋቱንም አካቶበታል:: በቁርኣን መሠረት ላይም ምርጥ ኡምማ (ሕዝብ) አንጾአል:: በዚህም የነቢዩ ሙሐመድ ﷺ ተአምር ከተቀሩት ነቢያት ወንድሞቻቸው ተአምራት በኃያልነቱ፣በዓለም አቀፋዊነቱና በዘላላማዊነቱ የተለየ ይሆናል:: የአታደርጉትም ፈታኝ ጥያቄም ለሁሌም እንደቀረበ ይቀጥላል፣የቁርኣንን መሰል ማምጣት ያለ መቻል ሽንፈትም እንደዚሁ እስከ ትንሣኤ ቀን ድረስ ቀጣይ ይሆናል:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{قُل لَّئِنِ ٱجۡتَمَعَتِ ٱلۡإِنسُ وَٱلۡجِنُّ عَلَىٰٓ أَن يَأۡتُواْ بِمِثۡلِ هَٰذَا ٱلۡقُرۡءَانِ لَا يَأۡتُونَ بِمِثۡلِهِۦ}[الإسراء: 88].

‹‹፦ ሰዎችም ጋኔኖችም የዚህን ቁርኣን ብጤ በማምጣት ላይ ቢሰባሰቡ፣ከፊላቸው ለከፊሉ ረዳት ቢኾንም እንኳ ብጤውን አያመጡም፤በላቸው::››[አል እስራእ፡88]



## በእርግጥ የአላህ ቃል ነው

‹‹እኔ በሙሐመድ መልክት እውነትነት ቅንጣት ጥርጣሬ የለኝም:: የነቢያትና የመልክተኞች መደምደሚያ መሆኑን፣ወደ መላው የሰው ዘር የተላከ መሆኑን፣መልእክቱም በኦሪትና በወንጌል ውስጥ የተላለፈውን መገለጥ ለማጠቃለል የመጣ መሆኑንም አምናለሁ:: ለዚህ ጥሩ ማስረጃ ታአምራዊው ቁርኣን ነው:: የእስላምና የሙስሊሞች ጥላቻ ያደረበት አውሮፓዊው ሊቅ ፓስካል የነዛቸውን አባባሎች ከአንዱ በስተቀር ሌሎቹን አልቀበልም:: እርሱም ‹ወንጌል የማቴዎስ ድርሰት እንዳልሆነ ሁሉ ቁርኣንም የሙሐመድ ድርሰት አይደለም› የሚለው አባባሉ ነው::››

**ፈንሳይ ሞንታይ**

**ፈረንሳዊ ፈላስፋና ተጓዥ**

4- ነቢዩ ﷺ ወደፊት ስለሚከሰቱት የዓለምና የሀገራት አያሌ ጉዳዮች የተነበዩ ሲሆን እርሳቸው እንደተናገሩት ሆነው በትክክል ተከስተዋል:: ከነዚህ መካከል ሻም፣ዒራቅና ቆስጠንጢኒያ (ቱርክ) ድል ሆነው የሚያዙ መሆናቸው አንዱ ነበር:: ከኣደም ﵇ ጀምሮ እስከ ኑሕ፣ኢብራሂም፣ሙሳና ዒሳ ﵇ ዘመን ስለነበሩ የቀደሙ ሕዝቦችና ነቢዮቻቸው ከመልክተኞቻቸው ጋር ስለነበሩባቸው ሁኔታዎችም ተናግረዋል:: ወደፊት ስለሚከሰቱት ነገሮች ተናግረውም በተነበዩት መሰረት ተፈጽመዋል:: ከነዚህ መካከል ፔርሽያ በሮማውያን ላይ ድል በተቀዳጀች ጊዜ አላህ (ሱ.ወ.) ሮማውያን ከጥቂት ዓመታት በኋላ ፔርሽያውያን ድል እንዲሚያደርጉ ማሳወቁ አንዱ ነው:: አላህ (ሱ.ወ.) ይህን በማስመልከት እንዲህ ብሏል፦

{الٓمٓ ۝١ غُلِبَتِ ٱلرُّومُ ۝٢ فِيٓ أَدۡنَى ٱلۡأَرۡضِ وَهُم مِّنۢ بَعۡدِ غَلَبِهِمۡ سَيَغۡلِبُونَ ۝٣ فِي بِضۡعِ سِنِينَۗ لِلَّهِ ٱلۡأَمۡرُ مِن قَبۡلُ وَمِنۢ بَعۡدُۚ وَيَوۡمَئِذٖ يَفۡرَحُ ٱلۡمُؤۡمِنُونَ ۝٤ بِنَصۡرِ ٱللَّهِۚ يَنصُرُ مَن يَشَآءُۖ وَهُوَ ٱلۡعَزِيزُ ٱلرَّحِيمُ ۝٥ وَعۡدَ ٱللَّهِۖ لَا يُخۡلِفُ ٱللَّهُ وَعۡدَهُۥ وَلَٰكِنَّ أَكۡثَرَ ٱلنَّاسِ لَا يَعۡلَمُونَ ۝٦ يَعۡلَمُونَ ظَٰهِرٗا مِّنَ ٱلۡحَيَوٰةِ ٱلدُّنۡيَا وَهُمۡ عَنِ ٱلۡأٓخِرَةِ هُمۡ غَٰفِلُونَ ۝٧} [الروم: ١ - ٧]،

‹‹አ.ለ.መ. (አሊፍ ላም ሚም):: ሩም ተሸነፈች:: በጣም ቅርብ በኾነችው ምድር:: እነሱም ከመሸነፋቸው በኋላ በእርግጥ ያሸንፋሉ:: በጥቂት ዓመታት ውስጥ (ያሸንፋሉ)፤ትእዛዙ በፊትም በኋላም የአላህ ነው:: በዚያ ቀንም ምእመናን ይደሰታሉ፤በአላህ ርዳታ (ይደሰታሉ)፤የሚሻውን ሰው ይረዳል፤እርሱም አሸናፊው፣አዛኙ ነው:: አላህ ርዳታን ቀጠረ [ለመርዳት ቃል ገባ]፤አላህ ቀጠሮውን አያፈርስም፤ግን አብዛኞቹ ሰዎች አያውቁም:: ከቅርቢቱ ሕይወት ግልጹን ብቻ ያውቃሉ፤እነርሱም ከኋለኛይቱ ዓለም ዘንጊዎች ናቸው::››[አልሩም:1-7]

ይህ ትንቢትም በትክክል አላህ (ሱ.ወ.) በተናገረው መሠረት በተግባር ተፈጽሚል::


5- ቀደምት ነቢዮች [በሁሉም ላይ የአላህ ሰላም ይውረድ] የነቢዩ ሙሐመድን ﷺ መምጣት ከረዥም ዘመናት በፊት ተንብየዋል:: የሚላኩበትን ሁኔታና አገራቸውን፣ሕዝቦችና ነገሥታት በርሳቸውና በኡመታቸው እንዴት እንደሚረቱ፣ሃይማኖታቸው እንዴት እንደሚስፋፋም ገልጸዋል::

6- የነቢያት መደምደሚያ መሆናቸውና ባይላኩ ኖሮ፣እንደሚመጡ ያበሰሩ ነቢያት ትንቢቶችም ውድቅ ይሆን የነበረ መሆኑ::

7- ነቢዩ ﷺ በተላኩበት ዘመን የነበሩና ሕሊናቸው በጭፍን ወገንተኝነት ያልታወረ እንደ መነኩሴው በሂራ፣ወረቀህ ብን ነውፈል፣ሰልማን አልፋሪሲ፣ዐብዱላህ ብን ሰላምና ዘይድ ብን ሰዕናህ የመሳሰሉ አንዳንድ የመጽሐፉ ባለቤቶች፣የነቢዩ ሙሐመድን ﷺ እውነተኛነትና በኦሪትና በወንጌልም ውስጥ የተወሱ መሆናቸውን መስክረዋል::

8- በተዋጓቸው ሕዝቦች ላይ ድል መቀዳጀታቸውም ከነቢይነት ማረጋገጫ ምልክቶች አንዱ ነው:: ለምን ቢባል አንድ ሰው በሐሰት ከአላህ የተላክሁ ነኝ እያለ፣አላህ (ሱ.ወ.) እገዛውን ሊሰጠው፣ጠላቶቹን ድል ሊያደርግለትና ጥሪው ተሰራጭቶ አያሌ ተከታዮችን ማፍራት የማይታሰብ በመሆኑ ነው:: ይህ እውን ሊሆን የሚችለው በእውነተኛ ነቢይ አማካይነት ብቻ ነው::

9- ነቢዩ ﷺ በአምልኮአቸው፣በቁጥብነታቸው፣በእውነተኛነታቸው፣በምስጉን ግለታሪካቸው፣በምሉእ ሰብእናቸው፣በምጡቅ ስነምግባራቸው፣ . . የነበሩበት አጠቃላይ ሁኔታቸው ሌላው የነቢይነታቸው ማረጋገጫ ነው:: ጌታቸው አላህ (ሱ.ወ.) በመልካምና



## የአላህ ሥራ!!

‹‹ቀደም ሲል ጥንታዊው የደቀልዲያኖስ ኢምፓይር ክፍል ተደርገው ይቆጠሩ በነበሩ አገሮች ውስጥ ስር በሰደደው የማሽቆልቆል ዘመን፣ከዐረቢያ በረሃዎች እምብርት አንዱድ ባለጋራ በድንገት ብቅ አለ:: እርጅና የተጫጫነውን ያንን ኢምፓይር ማሳደድም ያዘ:: በስተደቡብ አቆጥቁጠው ለነበሩ አዳዲስ ግዛቶችም ደመኛ ጠላት ሆነ:: ይህ ባለጋራ ዓይን እያየ ጥንካሬና ግዝፈት መጨመሩን ቀጠለ:: ፍጹምና ቅን የሆኑ፣የአላህ ቋሚ ረድኤት ወደ ጅሃድና ወደ አንጸባራቂ ድል የሚመራቸው ይመስል ነበር:: ሶርያና ግብጽን በድል አድራጊነት መያዝም ተከተለ:: በአጭር ጊዜ ውስጥም የሳሳኒያውያን ኢምፓይር ፈረካከሰ:: የፍልስጥኤም አጋሮችም ያንኑ የሽንፈት ጽዋ ለመጎንጨት ተገደዱ::››

**አልዶ ሚይሊ**

**ፈረንሳዊ ኦሪየንታሊስት**

https://www.path-2-happiness.com/am

ውብ ባሕርያት እንዲታነጹ አድርጓቸዋል፦

{وَإِنَّكَ لَعَلَىٰ خُلُقٍ عَظِيمٍ ﴿٤﴾}[القلم: ٤].

‹‹አንተም በታላቅ ጠባይ ላይ ነህ::››[አልቀለም:4]

ይህ ሊሆን የሚችለው ለእውነተኛ የአላህ ነቢይ ብቻ ነው::

10- የሙሐመድ ﷺ ነቢይነትና ታምራታቸው ከትውልድ ወደ ትውልድ የተላለፈበት ተከታታይነትና ቀጣይነት ያለው አዘጋገብ፤የነቢያትን ሁኔታና ታሪኮቻቸውን ያጠና ሰው፣የተቀሩት ነቢያት ነቢይነት በተረጋገጠባቸው መንገዶች ሁሉ የሙሐመድ ﷺ ነቢይነት በበለጠና በተጠናከረ ሁኔታ መረጋገጡን ይረዳል:: የሙሳና የዒሳ عليه السلام ነቢይነት ተረጋግጦ የተላለፈበትን ተከታታይነትና ቀጣይነት ያለውን መንገድ ብንመለከት፣የሙሐመድ ﷺ ነቢይነት የተላላለፈበት ዘገባ የበለጠ ጥንካሬ፣የበለጠ ተአማኒነትና ከዘመንም አንጻር ይበልጥ ቅርበት ባለው ዘገባ መተላለፉን በቀላሉ መገንዘብ እንችላለን:: የተሰጧቸው ታአምራቶችና ማረጋገጫ ምልክቶችም እንደዚሁ ተመሳሳይ መሆን ብቻ ሳይሆን የሙሐመድን ﷺ በተመለከተ ይበልጥ ታላቅና ዘላለማዊ ቀጣይነት ያላቸው ናቸው:: ከሁሉም ታላቁና ኃያሉ የሙሐመድ ﷺ ተአምርም በማያቋርጥ ሁኔታ በጽሑፍና በድምጽ ከትውልድ ወደ ትውልድ መተላለፉን የቀጠለው ታላቁ ቁርኣን ነው::

11- የነቢዩ ሙሐመድ ﷺ የማያነቡና የማይጽፉ ነቢይ መሆንም ከተአምራቶቻቸው አመላካቾች አንደኛው ነው:: አላህ (ሱ.ወ.) ሙሐመድን ﷺ የማያነብና የማይጽፍ ነቢይ አድርጎ የላካቸው ሲሆን ይህም ቅዱስ ቁርኣን ከአላህ የተላለፈላቸው ስለመሆኑ ብርቱ ማስረጃ ነው:: በተለይም ብዙ





ዓመታትን በሕዝባቸው መካከል የኖሩ በመሆኑ ነቢዩ ማንበብና መጻፍን የተማሩ ቢሆኑ ኖሮ ሙሽሪኮቹ የገዛ ራሱ ፈጠራ ነው ብለው በሞገቱ ነበር:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَكَذَٰلِكَ أَنزَلْنَآ إِلَيْكَ ٱلْكِتَٰبَ ۚ فَٱلَّذِينَ ءَاتَيْنَٰهُمُ ٱلْكِتَٰبَ يُؤْمِنُونَ بِهِۦ ۖ وَمِنْ هَٰٓؤُلَآءِ مَن يُؤْمِنُ بِهِۦ ۚ وَمَا يَجْحَدُ بِـَٔايَٰتِنَآ إِلَّا ٱلْكَٰفِرُونَ ﴿٤٧﴾ وَمَا كُنتَ تَتْلُوا۟ مِن قَبْلِهِۦ مِن كِتَٰبٍ وَلَا تَخُطُّهُۥ بِيَمِينِكَ ۖ إِذًا لَّٱرْتَابَ ٱلْمُبْطِلُونَ ﴿٤٨﴾}[العنكبوت: ٤٧- ٤٨]،

‹‹እንደዚሁም ወዳንተ መጽሐፍን አወረድን፤እነዚያም መጽሐፍን የሰጠናቸው በርሱ ያምናሉ፤ከነዚህም (ከመካ ሰዎች) በርሱ የሚያምኑ አልሉ፤በታምራቶቻችንም ከሓዲዎቹ እንጂ ማንም አይክድም:: ከርሱ በፊትም መጽሐፍን የምታነብ፣በቀኝህም የምትጽፈው፣አልነበርክም፤ያን ጊዜ አጥፊዎቹ በእርግጥ በተጠራጠሩ ነበር::››[አልዐንከቡት:47-48]

ነቢዩ ﷺ ይዘው የመጡት መልክት ከአላህ ዘንድ የተላለፈላቸው እንጂ ከራሳቸው አለመሆኑን በማረጋገጥም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{هُوَ ٱلَّذِى بَعَثَ فِى ٱلْأُمِّيِّۦنَ رَسُولًا مِّنْهُمْ يَتْلُوا۟ عَلَيْهِمْ ءَايَٰتِهِۦ وَيُزَكِّيهِمْ وَيُعَلِّمُهُمُ ٱلْكِتَٰبَ وَٱلْحِكْمَةَ وَإِن كَانُوا۟ مِن قَبْلُ لَفِى ضَلَٰلٍ مُّبِينٍ ﴿٢﴾}[الجمعة: 2].

‹‹እርሱ ያ በመሃይሞች ውስጥ አንቀጾቹን (ቁርአንን)፣በነርሱ ላይ የሚያነብላቸው፣(ከማጋራት) የሚያጠራቸውም፣መጽሐፍንና ጥበብን የሚያስተምራቸው የኾነን መልክተኛ (ሙሐመድን) ከነሱው ውስጥ የላከ ነው፤እነርሱም ከርሱ በፊት በግልጽ ስሕተት ውስጥ ነበሩ::››[አል ጁሙዓ:2]


የማያነብና የማይጽፈው መልክተኛ ነቢይ መገለጫ ባህርያትም፣የአላህን



https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am

አንቀጾች ለማይማን ሕዝቦች የሚያሰማ፣የሚያጠራቸውና ነቢያት ለሕዝቦቻቸው ያደርጉት እንደነበረው ሁሉ መጽሐፉን የሚያሳውቃቸው፣ቀደምት መልክተኞች ለሕዝቦቻቸው ያስተማሩትን ጥበብም የሚያስተምራቸው መሆኑን ቁርኣን ይገልጻል። ይህ ሁሉ የዚህ ነቢይ ﷺ የማያነብና የማይጽፍ መሆን በራሱ ታላቅ ተአምር መሆኑን፣ያልተማሩ ሆነው የተማሩ የነበሩ ቀደምት ነቢያት ለሕዝቦቻቸው ይዘው የመጡትን ሁሉ ለሕዝባቸው በተሟላ መልኩ ይዘው መምጣታቸው፣ሙሳን عليه السلام ከመሳሰሉ የሚያነቡና የሚጽፉ ነቢያት ካሳዩት ታምርም የበለጠና የላቀ ታምር ይሆናል።



## ነቢያዊ ስነምግባር

‹‹ተፈጥሮው ከታይታና ከማስመሰል የጸዳ በመሆኑ ሙሐመድን ከልብ እወደዋለሁ። ይህ የምድረበዳ ተወላጅ ነጻ የሆነ አስተሳሰብ ያለው ሰው ነበር። በራሱ ላይ እንጂ በማንም ትከሻ አይንጠለጠልም፤ያልሆነውንና የሌለበትን ነገርም ፈጽሞ አይናገርም። ኩራተኛም አልነበረም፤ግን ደግሞ ተዋራጅም አልነበረም። አላህ እንደ ፈጠረውና እንደሻለት በተጣፈ ልብስ ይሄድ ነበር። ግልጽ በሆነው ነጻ ቃሉ የሮምን ቄሳሮችና ዐረብ ያልሆኑ ነገስታትን ለዚህች ዓለምና ለወዲያኛው ዓለም ሕይወት ማድረግ ስላለባቸው ነገር ያሳውቃቸው ነበር። የራሱን ልክና ደረጃም ያውቅ ነበር። የዛሬን ሥራ ለነገ የማያቆይ ጽናትና ቁርጠኛነትን የተላበሰ ሰውም ነበር።››

**ቶማስ ካርላይል**

**እስኮትላንዳዊ ጸሐፊና የታሪክ ምሁር**





## የነቢይነት ድምዳሜ፦

አላህ (ሱ.ወ.) በጥበቡ ለመላው የሰው ልጅ አጠቃላይ፣ለሁሉም ዘመንና ስፍራ ምቹ የሆነ ዩኒቨርሳል መልክቱን አስይዞ ሙሐመድን ﷺ ልኳል። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَمَآ أَرۡسَلۡنَٰكَ إِلَّا كَآفَّةٗ لِّلنَّاسِ بَشِيرٗا وَنَذِيرٗا وَلَٰكِنَّ أَكۡثَرَ ٱلنَّاسِ لَا يَعۡلَمُونَ ٢٨} [سبأ: ٢٨]،

ሉሁ ችምሰለ ምንተንአ›› ንገርድአ ቂቃንጠስአ ናሪሳብአ፣ላመበ ንግ፤ምህንክላልአ ጂንእ ንኾቢ ‹‹።ምቁውያአ ችምሰ ቹኞዛብአ[ሰበእ፡28]

ይህን ዓለም አቀፍ ዘላለማዊ መልክቱንም ከመለወጥና ከመበረዝ ጠብቆት ከመዛባትና ከመቀያየር እንከን የተጠራ ሆኖ እስከመጨረሻው ድረስ ከሰው ልጆች ጋር የሚኖር ሕያው መልክት አድርጎታል። ለዚህም ነው የመጨረሻውና የማጠቃለያው መለኮታዊ መልክት እንዲሆን የተደረገውና ሙሐመድም ﷺ ከኋላቸው ምንም ነቢይ የማይመጣ የነቢያት መደምደሚያ የሆኑት። በዚህም አላህ (ሱ.ወ.) መለኮታዊ መልክቶቹን ምሉእ አድርጎ ሕግጋቶቹን በማጠቃለል



## ሃይማኖት በመሰረቱ አንድ ነውድን

‹‹የሁሉም ነቢያት ሃይማኖት አንድ ነው። ከአደም ጀምሮ እስከ ሙሐመድ ድረስ በአንድ መንገድ ላይ ይስማማሉ። ሦስት መለኮታዊ መጽሐፎች የተገለጡ ሲሆን እነሱም መዝሙር፣ኦሪትና ቁርኣን ናቸው። ቁርኣን ከኦሪት ጋር ያለው ትስስር ኦሪት ከመዝሙር ጋር ያለው ትስስር ዓይነት ነው። ሙሐመድ ከዒሳ አንጻር የሚታየው ዒሳ ከሙሳ አንጻር በሚታይበት መልኩ ነው። እዚህ ላይ ሊታወቅ የሚገባው ጉዳይ ግን ቁርኣን ወደ ሰዎች የተላለፈ የመጨረሻው መለኮታዊ መጽሐ ሲሆን ነቢዩ መሐመድም የነቢያትና የመልክተኞች መደምደሚያ መሆኑ ነው። በመሆኑም ከቁርኣን በኋላ ሌላ መጽሐፍ፣ከሙሐመድ በኋላም ሌላ ነቢይ የለም።››

**ሄንሪ ዴ ካስትሪ**

**የፈረንሳይ ጦር የቀድሞ ሻምበል**

https://www.path-2-happiness.com/am



## የመለኮታዊ መጻሕፍት መደምደሚያ

‹‹ኦሪት አንድ ወቅት ላይ የሰው ልጅ መሪና የስነምግባሩ መሰረት ነበር። አልመሲሕ ዒሳ ሲመጣ ክርስቲያኖች የወንጌልን ትምሕርቶች ተከተሉ። ከዚያም ቁርኣን በሁለቱ ቦታ ተተካ። ቁርኣን ከቀደሙት ሁለቱ መጽሐፎች የበለጠ የአጠቃላይነትና የተንታኝነት ባህርይ ያለው ሲሆን፣በነዚ ሁለቱ መጽሐፎች ላይ የደረሱትን የማዛባት፣የመለዋወጥና የመበረዝ ሁኔታዎች አርሟል። የመለኮታዊ መጻሕፍት ማጠቃለያ እንደመሆኑም ሁሉንም ሕግጋት አጠቃልሎ ይዟል።››

**ዋሽንግተን ኤርቨንጅ**

**አሜሪካዊ ኦሪየንታሊስት**

ግንባታውን አጠናቋል።

በዚህ ምክንያትም ሙሐመድ ﷺ ይዘው የመጡትን መጽሐፍ የቀደሙት መለኮታዊ መጻሕፍት ተቆጣጣሪ ገዥ፣ሸሪዓቸውንም የቀደሙትን ሸሪዓዎች (ሕግጋት) ሁሉ የሚሽር አድርጎ ጠብቆ የማኖር ኃላፊነቱን አላህ (ሱ.ወ.) ራሱ በመውሰዱ ታላቁ ቁርኣን በድምጽና በጽሑፍ ባልተቋረጠ ተከታታይ የዘገባ ሰንሰለት ከትውልድ ወደ ትውልድ በመተላለፍ ላይ ይገኛል። የሃይማኖቱ ሕግጋት ተግባራዊ አፈጻጸምም ከዕባዳዎቹና ከዝርዝር ድንጋጌዎቹ ጋር ምሉእ በሆነ የተአማኒነት ደረጃ ባልተቋረጠ የዘገባ ሰንሰለት ለኛ ደርሷል።

የነቢዩን ﷺ የሕይወት ታሪክና ነቢያዊ ፈለጋቸው (ሱንና) የተጠናቀሩባቸውን መድበሎች ያነበበ ሰው፣ባልደረቦቻቸው (ሶሓባ) የነቢዩን ﷺ አጠቃላይ ሁኔታዎች፣የተናገሩትን የሠሩትን ሁሉ በተሟላ መልኩ ጠብቀው ለሰው ልጆች አቆይተዋል። አላህን እንዴት ያመልኩ እንደነበረ ዕባዳቸውን፣ዝክራቸውንና ዱዓቸውን፣እስትግፋራቸውን፣ጅሃዳቸውን፣ደግነታቸውንና ፣ለባልደረቦቻቸውና ወደርሳቸው ለሚመጡትም ያደርጉ የነበረውን አያያዝ ወደር በሌለው ታማኝነትና ጥንቃቄ ለትውልዶች ጠብቀው አስተላልፈዋል። ደስታና ሐዘናቸውን፣ጉዞና ዕረፍታቸውን፣እንዴት ይበሉና እንዴት ይጠጡ እንደነበረ፣እንዴት ይተኙና ከእንቅልፍ እንዴት ይነሱ እንደነበረ ጭምር ዘግበዋል።

ይህን ሁሉ አስተውለን ስንመለከት ይህ ሃይማኖት ከመበረዝና ከመዛባት አደጋ በአላህ (ሱ.ወ.) ጥበቃ የሚደረግለት ሃይማኖት መሆኑን እንገነዘባለን።

በዚህን ጊዜም ሙሐመድ ﷺ የነቢያትና የመለክተኞች መደምደሚያ መሆናቸውን እንረዳለን። አላህ (ሱ.ወ.) ይህ መልክተኛ የነቢያት መደምደሚያ መሆኑን ሲነግረን እንዲህ ብሏልና፦


{مَّا كَانَ مُحَمَّدٌ أَبَآ أَحَدٍ مِّن رِّجَالِكُمْ وَلَٰكِن رَّسُولَ ٱللَّهِ وَخَاتَمَ ٱلنَّبِيِّـۧنَ ۗ وَكَانَ ٱللَّهُ بِكُلِّ شَىْءٍ عَلِيمًا ۝٤٠}[الأحزاب: 40].

ህላአየ ንግ፤ምለደይአ ትባአ ውሰ ምድንአየ ሁችቻዱንወከ፣ድመሐሙ›› ‹‹::ውነ ቂዋዐ ሉሁ ሩገነበ ምህላአ፤ውነ ያሚደምደመ ችዮቢነየ ናኛተክልመ[አል አሕዛብ:40]

## የሰው ልጆች ሁሉ መምሕር

‹‹የዐረባዊው ነቢይ የሕይወት ታሪክ የተከታዮቹን ልብ ማርኮ ይዟል። ሰብእናውም እነሱ ዘንድ ወደ ሰማየ ሰማያት መጥቋል። በመሆኑም ወደርሱ የተላለፈውን ሁሉ እንዲቀበሉ የሚያደርጋቸውን እምነት በመልክቱ አምነዋል። በሱንና እንደ ተጠናቀረው ሁሉ ተግባራዊ ክንዋኔዎቹም የሕግ ምንጭ ሲሆኑ፣ይህም የእስላማዊውን ማህበረሰብ ሕይወት አቀናጅቶ በመምራት ላይ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን ድል አድራጊ ሙስሊሞች ሙስሊም ካልሆኑ ዜጎቻቸው ጋር የሚኖራቸውን ግንኙነትም የሚገዛ ነው።››


**አርኖልድ ቶይንቢ**
**እንግሊዛዊ ታሪክ ጸሐፊ**



## የነቢያት መደምደሚያ

‹‹የመለኮታዊ መልክቶች ማጠቃላያ የርሱ መልክት እንዲሆንና እርሱ ራሱም የነቢያት መደምደሚያ ይሆን ዘንድ አላህ በመረጠው በነቢዩ ሙሐመድ ከተደመሙ ሰዎች መካከል እኔ አንዱ ነኝ።››

**ቶሊስቶይ**
**ሩሲያዊ የስነጽሑፍ ሰው**





## አላህን ብቻ ተገዙ

‹‹ሙሐመድ የነቢዮች መደምደሚያና ሰዎችን ወደ አምልኮተ አላህ ለመጥራት ከተላኩት መልክተኞችም ታላቁ መልክተኛ ነበር።››

**ዋሽንግተን ኤርቨንጅ**

**አሜሪካዊ ኦሪየንታሊስት**



https://www.path-2-happiness.com/am





## ለዓለማት ሁሉ እዝነት፦

አላህ (ሱ.ወ.) ነቢዩ ሙሐመድን ﷺ ወደ መላው የሰው ዘር የላካቸው፣ለዓለማት ሁሉ ለወንዱም ለሴቱም፣ለትንሹም ለትልቁም እዝነት ርህራሄና ጸጋ አድርጓቸው ነው። ይህም ብቻ ሳይሆን በርሳቸው ላላመኑትም ጭምር ረሕመት አድጓቸው ነው አላህ የላካቸው። እዝነትና ጸጋው ነቢዩ ﷺ በሕይወት ዘመናቸው በወሰዷቸው አቋሞች ውስጥ የተንጸባረቀ ሲሆን፣በተለይም በርህራሄና በእዝነት ሕዝባቸውን ወደ አላህ ተውሒድ በጠሩ ጊዜ ሰዎቹ አስተባበሏቸው፤ ከትውልድ አገራቸው ከመካ እንዲሰደዱ አድርጓቸዋል፤የመግደል ሙከራም ፈጽመውባቸዋል፤አላህ (ሱ.ወ.) ግን በቂያቸው ነበርና የቁረይሾችን ሴራ አክሽፎ ውድቅ አደረገ። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَإِذْ يَمْكُرُ بِكَ ٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ لِيُثْبِتُوكَ أَوْ يَقْتُلُوكَ أَوْ يُخْرِجُوكَ ۚ وَيَمْكُرُونَ وَيَمْكُرُ ٱللَّهُ ۖ وَٱللَّهُ خَيْرُ ٱلْمَٰكِرِينَ ﴿٣٠﴾} [الأنفال: ٣٠]

‹‹እነዚያም የካዱት ሊያስሩህ፣ወይም ሊገድሉህ፣ወይም (ከመካ) ሊያስወጡህ ባንተ ላይ በመከሩብህ ጊዜ፣(አስታውስ)፤ይመክራሉም፣አላህም ተንኮላቸውን ይመልስባቸዋል፤አላህም ከመካሪዎቹ ሁሉ በላይ ነው።››[አል አንፋል፡ 30]

የተፈጸመባቸው ያ ሁሉ ግፍ ግን ለነርሱ

## የእስላም ዓለም አቀፋዊነት

‹‹ወደ ነቢዩ የተላለፈ ለዓለማት ሁሉ እዝነት የሆነ ሃይማኖት መሆኑን በመግለጽ የእስላምን ዓለም አቀፋዊነት የሚያመለክተው ቁርኣናዊ አንቀጽ፣ለመላው ዓለም የተላለፈ ቀጥተኛ ጥሪ ነው። ይህም መልክተኛው ይዞ የመጣው መለኮታዊ መልክት ከዐረብ ሕዝብ ክልል አልፎ እንዲሄድ የተጻፈለት ስለመሆኑ ፍጹማዊ እርግጠኛነት እንደ ነበረው፣አዲሱን ቃል የተለያዩ ቋንቋዎች ላሏቸው የተለያዩ ሕዝቦች የማድረስ ግዴታ እንዳለበትም የሚያመለክት ግልጽ ማስረጃ ነው።››

**ኦራ ፊሽያ ቫግሌሬ**
**ጣሊያናዊት ኦሪየንታሊስት**



ማዘንንና ወደ አላህ መንገድ እንዲመጡ ያላቸውን ጉጉትን ብቻ ነበር ለነቢዩ ﷺ የጨመረው። ይህን አስመልክቶ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{لَقَدْ جَآءَكُمْ رَسُولٌ مِّنْ أَنفُسِكُمْ عَزِيزٌ عَلَيْهِ مَا عَنِتُّمْ حَرِيصٌ عَلَيْكُم بِٱلْمُؤْمِنِينَ رَءُوفٌ رَّحِيمٌ ﴿١٢٨﴾}[التوبة: ١٢٨]

‹‹ከነሳችሁ የኾነ፣ችግራችሁ በርሱ ላይ ጥኑ የኾነ፣በናንተ (እምነት) ላይ የሚጓጓ፣ለምእመናን ርኅሩህ አዛኝ የኾነ መልክተኛ፣በእርግጥ መጣላችሁ።››[አል ተውባህ፡128]



በተጨማሪም ድል አድርጓቸው በአሸናፊነት መካ በገቡት ቀንም ያለ ምንም በቀል ‹‹ነጻ ናችሁ ሂዱ›› ብለው ነበር ምሕረት ያደረጉላቸው። ከሐዲዎቹን በሁለት ተራራዎች መሀል አጣብቆ ለማጥፋት አላህ (ሱ.ወ.) መልኣክ በላከላቸው ጊዜ፣‹‹አላህ (ሱ.ወ.) ከአብራኮቻቸው አንድ አላህን ብቻ የሚግገዙ ሰዎችን ያወጣ ይሆናልና የለም እታገሳለሁ›› ነበር ያሉት። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَمَآ أَرْسَلْنَٰكَ إِلَّا رَحْمَةً لِّلْعَٰلَمِينَ ﴿١٠٧﴾}[الأنبياء: ١٠٧]

‹‹(ሙሐመድ ሆይ!) ለዓለማትም እዝነት አድርገን እንጅ አልላክንህም።››[አል አንቢ.ያ፡107]

ነቢዩ ﷺ በእርግጥ ለዓለማት ሁሉ፣ለሰዎች ሁሉ፣የቆዳ ቀለም፣ቋንቋ፣አመለካከት፣እምነትና ቦታ ሳይለይ ለመላው የሰው ዘር የተላኩ እዝነትና ዘላለማዊ የአላህ ጸጋ ናቸው።

የነቢዩ ﷺ እዝነትና ጸጋ በሰው ልጆች ላይ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን ለእንስሳትና ለግዑዝ አካላትም ጭምር የተዘረጋ ነው። የአንድ የመዲና ነዋሪ ባልደረባቸውን ግመል ባለቤቱ በረሃብ ስላሰቃየው የአላህ መልክተኛ ﷺ በግመሉ ሁኔታ አዝነውና ራርተው ባለቤቱ ለግመሉ ደግ እንዲሆን እንዳያስርበውና ከአቅሙ በላይ እንዳይጭንበት አዘዋል። ነቢዩ ﷺ አንድ ሰው ጫጩቶቿን የወሰደባትን እርግብ አይተው ልባቸው በማዘኑ ጫጩቶቹን እንዲመልስላት አዘዋል። ‹‹ባረዳችሁ ጊዜ አስተራረዱን አሳምሩ›› [በሙስሊም የተዘገበ] ያሉትም ነቢዩ ﷺ ናቸው። እዝነትና ርህራሄያቸው ወደ ግዑዝ አካላትም ተዳርሷል፤በዚህ ረገድ ነቢዩ ﷺ ስለተለዩት ዋይታ ላሰማው የተምር ግንድ ሆዳቸው ራርተው ከመናገሪያ ምንበራቸው (መድረክ) ወርደው ግንዱ እስኪረጋጋ ድረስ አቅፈውታል።

ርህራሄና እዝነታቸው በግላዊ አቋምና በሁነቶች ላይ ብቻ የተወሰነ የግል ዝንባሌ ሳይሆን ለሰዎች የደነገጉት መለኮታዊ ትእዛዝ፣ሕግ፣መመሪያና ቋሚ ስነምግባርም ነው። ለሰዎች ርህሩህ አዛኝና ገር መሆንን ሲያበረታቱና አስቸጋሪና አስጨናቂ መሆንን ሲያስጠነቅቁም ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹አላህ ሆይ! ከሕዝቦቼ ጉዳዮች መካከል በአንዱ ነገር ኃላፊነት ተሰጥቶ ለነሱ አስቸጋሪና አስጨናቂ የሆነን ሰው አንተ አስቸጋሪና አስጨናቂ ሁንበት፤ከሕዝቦቼ ጉዳዮች መካከል በአንዱ ነገር ኃላፊነት ተሰጥቶ ለነሱ ገርና ርህሩህ የሆነውን ሰው ደግሞ አንተ ገርና ርህሩህ ሁንለት።›› [በሙስሊም የተዘገበ] እናም እዝነትና ርህራሄ ከነቢዩ ﷺ ታላላቅ ባህርያት መከከል አንዱ ሲሆን፣የእዝነትና የሰላም ሃይማኖት በሆነው እስላም ውስጥም አንዱ መሰረታዊ መርሕ ነው።

**ለሰው ልጆች የተበረከተ እዝነት**

‹‹ታሪካዊው የሙሐመድ ሕይወት አላህ ‹ለዓለማት እዝነት አድርገንህ እንጂ አልላክንህም› በማለት ከገለጸው ይበልጥ ባማረ አገላለጽ ሊቀርብ አይችልም። ታላቁ የቲም (የሙት ልጅ) ለድኩማን ሁሉና እርዳታውን ለሚሹ ሰዎች ሁሉ ታላቁ እዝነትና ታላቁ ርህራሄ መሆኑን በገዛ ራሱ አስመስክሯል። በእርግጥም ሙሐመድ ለየቲሞች፣ለመንገደኞች፣አደጋ ለደረሰባቸው ሰዎች፣ለድሆች ሁሉና ጥረው ግረው ለሚኖሩ ሠራተኞች እውነተኛው ርህራሄና እውነተኛው እዝነት ነበር።››

**ጃን ሊክ**
**እስፔናዊ ኦሪየንታሊስት**



https://www.path-2-happiness.com/am



## በነቢዩ ﷺ መላክ መላው የሰው ዘር መታደሱ ፦

የሙሐመድ ﷺ ዘመነ ተልእኮ መጥቶ በሙሐመድ ነቢይነት በረከት አላህ (ሱ.ወ.) ሰዎችን ወደ ቀጥተኛው የተውሒድ መንገድ መራቸው:: መመሪያው በያዛቸው ማብራሪያዎችና መግለጫዎች ጥልቀትና ምጥቀት ከቃላት ገለጻና ከዐዋቂዎች ዕውቀት በላይ ነው:: ጠቃሚ ዕውቀትን፣በጎ ሥራን፣ታላላቅ ስነምግባራትንና ቀጥተኛ ፈለግን ለሰው ልጆች ያበሰረ ሲሆን፤ እውቀትና ተግባርን ያካተተ የሁሉም ሕዝቦች ጥበብ አንድ ላይ ተደምሮ ቢመጣ ከዚህ ዘላለማዊ መለኮታዊ መመሪያ በብዙ እጅ አንሶ ይታያል:: ለዚህም ምስጋና ሁሉ ለጌታችን ለአላህ ይሁን::

ዐቂዳን (እምነትን ) በተመለከተ ከሙሐመድ ﷺ መላክ በፊት ባእድ አምልኮና በአላህ ማጋራት ቀደም ሲል ለክለሳና ለመዛባት አደጋ የተጋለጡ መለኮታዊ መጻሕፍት ባለቤቶች በሆኑት ዘንድ እንኳ ሳይቀር ምድርን አጥለቅልቀው ነበር:: ይህን አስከፊ ሁኔታ ለመለወጥ የአላህ መልክተኛ ﷺ የጠራ ተውሒድንና አንድ አላህን ብቻ ከርሱ ጋር ማንንም ምንንም ሳያጋሩ እርሱን ብቻ የመግገዛት እምነትን ይዘው መጡ:: ሰዎችንም ከፍጡራን አምልኮ ወደ አንዱ ፈጣሪ ጌታ አምልኮ አሸጋገሩ:: በተውሒድ ልቦናን ከሽርክ ርክሰትና ከባዕድ አምልኮ ቆሻሻ አጸዱ:: አላህ (ሱ.ወ.) የላካቸው ከርሳቸው የቀደሙ ነቢያትና መልክተኞች ይዘው የመጡትን ትምሕርት በማስያዝ ነበር:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَمَآ أَرۡسَلۡنَا مِن قَبۡلِكَ مِن رَّسُولٍ إِلَّا نُوحِيٓ إِلَيۡهِ أَنَّهُۥ لَآ إِلَٰهَ إِلَّآ أَنَا۠ فَٱعۡبُدُونِ ٢٥}[الأنبياء: ٢٥]

‹‹ከአንተ በፊትም፣እነሆ ከኔ ሌላ አምላክ የለምና ተገዙኝ በማለት ወደርሱ የምናወርድለት ቢኾን እንጂ ከመልክተኛ አንድንም አልላክንም::››[አል አንቢያእ፡25]

አላህ (ሱ.ወ.) በተጨማሪ እንዲህ ብሏል፦

{وَإِلَٰهُكُمۡ إِلَٰهٞ وَٰحِدٞۖ لَّآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ ٱلرَّحۡمَٰنُ ٱلرَّحِيمُ ١٦٣}
[البقرة: ١٦٣]

‹‹አምላካችሁም አንድ አምላክ ብቻ ነው፤ከርሱ በቀር ሌላ አምላክ የለም፤(እርሱ) እጅግ በጣም ርኅሩህ አዛኝ ነው::››[አል በቀራህ፡163]

በማሕበራዊው ሕይወት በኩልም ነቢዩ ﷺ የተላኩት ግፍና ጭቆና በተንሰራፋበት፣የሰው ልጆች በጌታና በሎሌ መደብ ተከፋፍለው በአስከፊ የመደብ ጭቆና በሚሰቃይበት ወቅት ነበር:: ነቢዩ ﷺ ሰዎችን ሁሉ ዐረብና ዐረብ ያልሆነ፣ነጭና ጥቁር ሳይባል እኩልነትን የሚያሰፍን፣አላህን በመፍራትና በሚፈጽሙት መልካም ተግባር ብቻ ካልሆነ ማንም ሰው ከሌላው ሰው ፈጽሞ የማይበልጥ መሆኑን የሚያበስር ሰብአዊ እኩልነትን ይዘው ነው የመጡት:: ይህን በማስመልከት አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{إِنَّ أَكۡرَمَكُمۡ عِندَ ٱللَّهِ أَتۡقَىٰكُمۡ}[الحجرات: ١٣]

‹‹በላጫችሁ፣በጣም አላህን ፈሪያችሁ ነው፤››[አል ሑጁራት፡13]

አላህ (ሱ.ወ.) ለፍትሕ አስተካካይነት፣ለበጎ ሥራና ለማሕበራዊ ተራድኦ ጥሪ ሲያደርግ፣ከግፍ ከመጥፎ ድርጊትና ከማንኛውም በደል ከልክሏል:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{إِنَّ ٱللَّهَ يَأۡمُرُ بِٱلۡعَدۡلِ وَٱلۡإِحۡسَٰنِ وَإِيتَآيِٕ ذِي ٱلۡقُرۡبَىٰ وَيَنۡهَىٰ عَنِ ٱلۡفَحۡشَآءِ وَٱلۡمُنكَرِ وَٱلۡبَغۡيِۚ يَعِظُكُمۡ لَعَلَّكُمۡ تَذَكَّرُونَ ٩٠}[النحل: ٩٠ ]



### የሰው ልጆችን ከጨለማ ወደ ብርሃን የሚያወጣ

‹‹ነቢዩ ሙሐመድ ፍጡራንን በትንግርታዊ ፍጥነት ወደ መጨረሻው የመታደል ደረጃ አድርሷቸዋል። የሰው ልጆች ከርሱ በፊት የነበሩበትን የጥመት ሁኔታ አስተውሎ የቃኘ ሰው፣ከርሱ በኋላ ያለውን ሁኔታቸውንና በርሱ ዘመን የደረሱበትን ታላቅ ምጥቀት ያስተዋለ ሰው፣በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት የሰማይና የምድርን ያል የተራራቀ መሆኑን ይገነዘባል።››

**ኬ.ዊልያም**

**እንግሊዛዊ ፈላስፋ**



### ለሰው ልጆች በመላ የተላለፈ ሃይማኖት

‹‹ሁለቱ ታላላቅ አንቀጾች ማለትም ‹‹አላህ ዘንድ የተወደደ ሃይማኖት እስላም ብቻ ነው፤›› [ኣሊ ዒምራን፡ 19] እና ‹‹አንተንም ለሰዎች ሁሉ በመላ፣አብሳሪና አስፈራሪ [አስጠንቃቂ] አድርገን እንጂ አልላክንህም፤›› [ሰበእ፡28] አእምሮዬ ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ አሳድረዋል፤ ምክንያቱም እስላምን ከሌሎች ሥርዓቶችና ሕግጋት ልዩ ለሚያደርገው ለዚያ የዓለም አቀፋዊነት ባህርይውና የነቢዩ ዒሳን عليه السلام እውነታ አስመልክቶ ላቀረበው የተሟላ ማብራሪያ ማስረጃ በመሆናቸው ነው። ታድያ ሁሉም ነቢያትና መልክተኞች ይዘው የመጡትን ሁሉ እንድናከብር ከሚያዙን ከነዚያ ራሳቸውን የቻሉ ነጻ ትምሕርቶች ይበልጥ ጠንካራና ይበልጥ እውነት የሆነ ምን ነገር ይኖራል?! ያለ ምንም ጥርጥር የእስላም ሃይማኖት የሐቅ የእርግጠኝነትና የማስረጃ ሃይማኖት ነው።››

**ዋጅነር**

**ሆላንዳዊ ተመራማሪ**





https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am

‹‹አላህ በማስተካከል፣ በማሳመርም፣ ለዝምድና ባለቤት በመስጠትም ያዛል፤ ከአስከፊም፣(ከማመንዘር)፣ከሚጠላም ነገር ሁሉ፣ከመበደልም ይከለክላል፤ ትገነዘቡ ዘንድ፣ይገሥጻችኋል::››[አል ነሕል:90]

ይህ ብቻ ሳይሆን የሌሎችን ሕሊናዊ መብቶች እንዲከበሩ አድርጎ ሰዎች አንዱ በሌላው ላይ እንዳይሳለቅ ከልክሏል:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{يَـٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ لَا يَسْخَرْ قَوْمٌ مِّن قَوْمٍ عَسَىٰٓ أَن يَكُونُواْ خَيْرًا مِّنْهُمْ وَلَا نِسَآءٌ مِّن نِّسَآءٍ عَسَىٰٓ أَن يَكُنَّ خَيْرًا مِّنْهُنَّ وَلَا تَلْمِزُوٓاْ أَنفُسَكُمْ وَلَا تَنَابَزُواْ بِٱلْأَلْقَـٰبِ بِئْسَ ٱلِٱسْمُ ٱلْفُسُوقُ بَعْدَ ٱلْإِيمَـٰنِ وَمَن لَّمْ يَتُبْ فَأُوْلَـٰٓئِكَ هُمُ ٱلظَّـٰلِمُونَ ﴿١١﴾}[الحجرات: ١١]

‹‹ወንዶች ከወንዶች አይቀልዱ፤ከነርሱ የበለጡ ሊኾኑ ይከጀላልና፤ሴቶችም ከሴቶች (አይሳለቁ)፤ከነሱ የበለጡ ሊኾኑ ይከጀላልና፤ነፍሶቻችሁንም አታነውሩ (ከፊላችሁ ከፊሉን አይዝለፍ)፤በመጥፎ ስሞችም አትጠራሩ፤ከእምነት በኋላ የማመጥ ስም ከፋ፤ያልተጸጸተም ሰው፣እነዚያ እነሱ በዳዮቹ ናቸው::››[አል ሑጁራት:11]

በስነምግባር መስክም የሰው ልጆች ግብረገብነትና መልካም ባሕርያት ክፉኛ ባዘቀዘቁበት ወቅት ነበር ነቢዩ ﷺ የተላኩት:: የመጡትም ሰዎችን ወደ መልካም ስነምግባርና ምስጉን ባሕርያት እንዲመለሱና በበጎ በይነሰባዊ ግንኙነቶች እንዲታደሉ ለማድረግ ነው:: የአላህ መልክተኛ ﷺ እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹የተላክሁት መልካም ስነምግባራትን ምሉእ ለማድረግ ነው::›› [በበይሀቂ የተዘገበ] አላህ (ሱ.ወ.) ስለ ነቢዩ ﷺ ታላቅ ስነምግባር ሲገልጽ እንዲህ ብሏል፦

{وَإِنَّكَ لَعَلَىٰ خُلُقٍ عَظِيمٍ ﴿٤﴾}[القلم: ٤]

‹‹አንተም በታላቅ ጠባይ ላይ ነህ::››[አልቀለም:4]

ነቢዩ ﷺ የምጡቅ ስነምግባርና የመልካም ባሕርያት ሁሉ፣የቁጥብነት፣የተግባቦት፣የአብሮነትና የመልካም አነጋገር ቁንጮ ምሳሌ ብቻ ሳይሆኑ የመልካም ነገሮች ሁሉ መልካም አርአያ ነበሩ:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{لَّقَدْ كَانَ لَكُمْ فِى رَسُولِ ٱللَّهِ أُسْوَةٌ حَسَنَةٌ لِّمَن كَانَ يَرْجُواْ ٱللَّهَ وَٱلْيَوْمَ ٱلْـَٔاخِرَ وَذَكَرَ ٱللَّهَ كَثِيرًا ﴿٢١﴾}[الأحزاب: ٢١]

‹‹ለናንተ፣አላህንና የመጨረሻውን ቀን የሚከጅል ለኾነ ሰው፣አላህንም በብዙ ለሚያወሳ፣በአላህ መልክተኛ መልካም መከተል [አርአያ] አላቸው::››[አል አሕዛብ:21]

የሴት ልጅን በተመለከተ በቅድመ እስላም አስከፊ ግፍና ጭቆና ይደርስባት የነበረ ሲሆን፣ነቢዩ ﷺ የተላኩት ሴቶች በሕብረተሰቡ ውስጥ ምንም መብት ያልነበራቸውና የተዋረዱ፣ሌላው ቀርቶ ሰው ነች ወይስ አይደለችም? በሚለው ላይ እንኳ ወንዶች በሚወዛገቡበት፣በሕይወት የመኖር መብት አላት ወይስ እንደተወለደች ተግደላ ትቀበር ?! ብለው በሚከራከሩበት ዘመን ነበር:: የማህበረሰቡ ሁኔታም አላህ (ሱ.ወ.) ቁርኣን ውስጥ ቀጥሎ የገለጸውን ይመስል ነበር፦

{وَإِذَا بُشِّرَ أَحَدُهُم بِٱلْأُنثَىٰ ظَلَّ وَجْهُهُۥ مُسْوَدًّا وَهُوَ كَظِيمٌ ﴿٥٨﴾ يَتَوَٰرَىٰ مِنَ ٱلْقَوْمِ مِن سُوٓءِ مَا بُشِّرَ بِهِۦٓ أَيُمْسِكُهُۥ عَلَىٰ هُونٍ أَمْ يَدُسُّهُۥ فِى ٱلتُّرَابِ أَلَا سَآءَ مَا يَحْكُمُونَ ﴿٥٩﴾}[النحل:٥٨ - ٥٩]

‹‹አንዳቸውም በሴት ልጅ በተበሰረ ጊዜ፣እርሱ የተቆጨ ኾኖ፣ፊቱ ጠቁሮ ይውላል:: በርሱ ከተበሰረበት ነገር መጥፎነት፣በውርደት ላይ ኾኖ፣ይያዘውን? ወይስ በዐፈር ውስጥ



## ከመሰናበቻው ሐጅ ትምሕርቶች

‹‹ሙሐመድ የመሰናበቻውን ሐጅ ከመዲና ወደ መካ ያደረገው ከመሞቱ አንድ ዓመት ቀደም ብሎ ነበር:: በዚህ የሐጅ ሥርዓት ላይ ለሕዝቦቹ ታላቅ መካሪ ዲስኩር ያደረገ ሲሆን የንግግሩ የመጀመሪያ አንቀጽ ብቻውን በሙስሊሞች መካከል ያለውን ዝርፊያና ንጥቅያ፣የበቀልና የደም ጉዳዮችን ሁሉ ነቅሎ የመጣል አቅም ነበረው:: የዲስኩሩ የማጠቃለያ አንቀጽ ደግሞ ጥቁሩን ሰው ከሙስሊሞች መሪ ኸሊፋ ጋር ፍጹም እኩል የማድረግ ኃይል ነበረው:: በእውነትም በዓለም ላይ ፍትሐዊ ለሆነ በይነሰባዊ ግንኙነት ታላቅ መሰረትን ጥሏል::››

**ሄርበርት ጆርጅ ዌልዝ**

**እንግሊዛዊ የቋንቋ ሊቅ**




## የነቢዩ ሙሐመድ ስነምግባር

‹‹ሙሐመድ በሰው ልጅ ሊደረስበት በሚቻለው የመጨረሻው ታላቅ መልካም ጸባያትና ክቡር ስነምግባራት ላይ ነበር::የመጨረሻው የይሉኝታ ደረጃና ጥልቅ የሆነ የርህራሄ ስሜት ነበረው:: እጅግ አስገራሚ የሆነ የግንዛቤ ኃይል፣ወደር የሌለው የሰላ አእምሮ፣ክቡር የሆኑ የመውደድና የእዝነት ስሜቶች ባለቤትም ነበር:: በእርግጥ በታላቅ ስነምግባርና በተወዳጅ ባሕርያት ላይ ነበር::››

**ዐብዱላህ ኮዊልያም**

**እንግሊዛዊ ፈላስፋ**


https://www.path-2-happiness.com/am



### የዓለም መንገድ

‹‹የእስላምን ነቢይ የሕይወት ታሪክ በሚገባና ደጋግሜ አንብቤያለሁ። መሆን የሚገባውን ታላቅ ስነምግባር እንጂ ሌላ አላገኘሁበትም፤እስላም የዓለም መንገድ ይሆን ዘንድም በጽኑ ተመኘሁ።››

**በርናርድ ሾው**
**እንግሊዛዊ ጸሐፊ**



### የሴት ደረጃ

‹‹እስላም በዐረቦች አገር የሴትን ደረጃ ከፍ አድርጓል። ሴት ሕጻናትን ከነሕይወታቸው የመቅበርን ልማድ አስወግዷል። በፍርድ ሂደቶችና በንብረት ባለቤትነት መብት ወንድና ሴትን እኩል አድርጓል። ለሴቷ ሐላል በሆነ ሥራ ላይ የመሰማራት፣የመውረስና ሥርታ ያገኘችውን ሀብት በባለቤትነት እንዳሻት የማድረግ መብት ሰጥቷል። በዘመነ ጃህሊያ የዐረቦች ልማድ የነበረውን ሴቶችን ከሌላው ንብረት ጋር ከአባት ወደ ልጅ ማስተላፍን ያስቀረ ሲሆን፣የሴትን የውርስ ድርሻ የወንዱ ድርሻ ግማሽ አድርጎ ያለ ፍቃዳቸው እንዳይዳሩም ከልክሏል።››

**ዖል ዲዮራንት**
**አሜሪካዊ ደራሲ**

ይደብቀውን? (በማለት እያምታታ) ከሰዎች ይደበቃል፤ንቁ፣የሚፈርዱት (ፍርድ) ምንኛ ከፋ!››[አልነሕል፡58-59]

ሴት ልጅ ተራ መጫወቻና፣የሚገበያዩባት አሻንጉሊትና ተዋራጅ አልባሌ ዕቃ ተደርጋ ትቆጠር ነበር።

አላህ (ሱ.ወ.) ነቢዩን ﷺ ሲልካቸው ለሴት ልጅ

ክብሯን አስመለሰላት። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَمِنْ ءَايَٰتِهِۦٓ أَنْ خَلَقَ لَكُم مِّنْ أَنفُسِكُمْ أَزْوَٰجًا لِّتَسْكُنُوٓا۟ إِلَيْهَا وَجَعَلَ بَيْنَكُم مَّوَدَّةً وَرَحْمَةً ۚ إِنَّ فِى ذَٰلِكَ لَءَايَٰتٍ لِّقَوْمٍ يَتَفَكَّرُونَ ﴿٢١﴾} [الروم: ٢١]


‹‹ለናንተም ከነፍሶቻችሁ (ከጎሶቻችሁ) ሚስቶችን ወደነርሱ ትረኩ ዘንድ መፍጠሩ፣በመካከላችሁም ፍቅርንና እዝነትን ማድረጉ፣ከአስደናቂ ምልክቶቹ ነው፤››[አል ሩም፡21]


ይልቅዩም በእናትነቷ እንድትከበርም ትእዛዝ አስተላለፈ። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَقَضَىٰ رَبُّكَ أَلَّا تَعْبُدُوٓا۟ إِلَّآ إِيَّاهُ وَبِٱلْوَٰلِدَيْنِ إِحْسَٰنًا}[الإسراء: ٢٣]

‹‹ጌታህም (እንዲህ አዘዘ)፤-እርሱን እንጂ ሌላን አትገዙ፤በወላጆቻችሁም መልካምን ሥሩ፤››[አል እስራእ፡23]

ነቢዩም ﷺ ለሴት እንደ እናት ከወንድ ቅድሚያ ሰጥተዋታል። አንድ ሰው ወደ ነብዩ ﷺ መጥቶ ፦ ‹‹የአላህ መልክተኛ ሆይ! ለኔ መልካም አያያዝና ለደግነቴ ከሁሉም ይበልጥ ባለመብት የሆነው ማነው? ሲላቸው ፦ እናትህ ናት አሉት፤ከዚያስ? አላቸው፤እናትህ ናት፣አሉት፤ከዚያስ? አላቸው፤እናትህ ናት አሉት፤ከዚያስ? አላቸው፤አባትህ ነው አሉት።››[በቡኻሪና ሙስሊም የተዘገበ] ትንሽ ልጃገረድ ሆናም አክብሮት እንዲቸራት ሲያዙ ነቢዩ ﷺ ፦ ‹‹ሦስት የሚያስጠጋቸው፣የሚራራላቸውና የሚያሳድጋቸው ሴቶች ልጆች ያሉት ሰው ገነት ለርሱ ተገቢው ሆናለች›› ሲሉ የአላህ መልክተኛ ሆይ! ሁለት ብቻ ቢሆኑም? ተብለው ሲጠየቁ ‹‹አዎ፣ሁለት ብቻ ቢሆኑም›› ብለዋል። [በአሕመድ የተዘገበ] በተጨማሪም እንደ ሚስትም ክብር እንዲሰጣት አዘው ይህን ማድረግ ከበላጭነት መለኪያ ጋር አያይዘዋል፦ ‹‹በላጫችሁ ለቤተሰቡ ከሌላው ይበልጥ ጥሩ የሆነ ሰው ነው፤እኔ ከሁላችሁም ይበልጥ ለቤተሰቤ ጥሩ ነኝ።›› ብለዋል። [በትርምዚ የተዘገበ]





### ግፍና በደል

‹‹በአውሮፓ የፈላስፎች ጉባኤ ይጠራና ሴት እንደ ወንዱ ሁሉ ነፍስ አላት ወይስ የላትም? ያላት ነፍስ የሰው ልጅ ነፍስ ነው ወይስ የእንስሳት ነፍስ ነው? የሚሉ ነጥቦች ለክርክር ይቀርቡ ነበር። ክርክሩም ‹ሴት ነፍስ ወይም መንፈስ አላት ግን ከወንዱ ነፍስ በብዙ ደረጃዎች ያነሰ ነው› በሚል የጋራ አቋም ይቋጭም ነበር።››



## ዘላለማዊው መልክት መጠሪያ ስም ምንድን ነው?

እያንዳንዱ ሃይማኖት መጠሪያ ስሙን ያገኘው ከሃይማኖቱ መስራች ግለሰብ ስም፣ወይም ሃይማኖቱ ከተገኘበት የተለየ ሕዝብ ወይም ጎሳ ስም ነው:: ዞሮስቲሪያኒዝም ከመስራቹ ከዞሮስት፣ቡድሂዝም ከመስራቹ ከቡድሃ፣ይሁዳዊነት እምነቱ ከተገኘበት ነገድ ከይሁዳ፣ክርስትናም ከመስራቹ ከኢየሱስ ክርስቶስ የተገኙ መጠሪያ ስሞች ናቸው:: እስላም ግን ከዚህ ሁሉ የተለየ ነው::


እስላም ከግለሰብ ወይም ከአንድ የተለየ ሕዝብ ወይም ነገድ ጋር የተሳሰረ አይደለም:: ለአላህ (ሱ.ወ.) እርሱን ብቻ ለመግገዛትና ለርሱ ብቻ ለመታዘዝ ራሱን ለርሱ የሰጠ ሰው ሁሉ ለርሱ የሰለመ ሰው ነው:: የነቢያትና የመልክተኞች መደምደሚያ የሆኑትን ሙሐመድን ﷺ የተከተለ፣ይዘው ለመጡት እውነተኛው ሃይማኖት የተገዛ፣ነቢዩን አምኖ በመቀበል ፈለጋቸውን ተከትሎ የተጓዘ ሰው ሁሉ፣በየትኛውም ዘመንና ስፍራ ቢሆን፣የየትኛውም የቆዳ ቀለም ወይም ጎሳና ብሔር አባል ቢሆን እውነተኛው ሙስሊም እርሱ ነው::

### አላህ ተጋሪ የለውም

‹‹ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም፣እርሱ አንድና ምንም ተጋሪ የሌለው ነው:: እርሱ እውነት ነው፣ከርሱ ውጭ ያለው ሁሉ ሐሰት ነው:: ፈጥሮናል ይመግበናልም:: እስላም ነገሮችን ሁሉ ለአላህ ሰጥተን መስለም ማለት ነው:: ወደርሱ መጠጊያ መያዝ ነው:: በርሱ ላይ መተማመን ነው:: ሁሉም ኃይል ያለው ለርሱ ጥበብ ቀጥ ብሎ በመግገዛት ውስጥ ነው:: ድርሻችን የፈለገውንም ቢሆን አላህ የሰጠን ዕጣ ፈንታችን - አስበርጋጊውን ደራሽ ሞት ቢሆን እንኳ - ወደን በቀና ስሜት መቀበል ነው:: መልካሙ እርሱ የመረጠው መሆኑንና ሌላው መልካም አለመሆኑን ማወቅ ነው:: የሰው ልጅ ኢምንት አንጎሉን የዓለማትና የሁኔታዎቻቸው መመዘኛ አድርጎ መውሰዱ የከፋ ጅልነት ነው::ማድረግ ያለበት ከርሱ ግንዛቤ በላይ ቢሆንም ይህ ዩኒቨርስ ፍትሐዊ የሆነ ሕግ እንዳለው ማወቅ፣በጎ ነገር የዩኒቨርሱ መሰረት መሆኑን፣ሰናይነት የዩኒቨርሱ መንፈስ መሆኑን መረዳት ነው . . ይህን ሁሉ አውቆ አምኖበት በእርጋታና በጽድቅ ስሜት በዚህ መጓዝ ይኖርበታል::››

ቶማስ ካር ላይል

እስኮትላንዳዊ የታሪክ ሊቅና ጸሐፊ




### በዐረባዊውና ዐረባዊ ባልሆነው መካከል ልዩነት የለም

‹‹ሙስሊሞች የሚዛመዱባቸው አገሮችና ሕዝቦች የፈለገውን ያህል የተለያዩ ቢሆኑም እርስበርስ የሚተያዩት እንደ ባእዳን አይደለም:: በአገረ እስላም በሁሉም መብቶች እኩል በመገልገል ረገድ በቻይናዊው ሙስሊምና በዐረባዊው ሙስሊም መካከል አንዳች ልዩነት የለም::እሰላማዊ መብቶችም ከአውሮፓዊ መብቶች በዚህ መሠረታዊ ነጥብ ይለያሉ::››

ጎስታፍ ሎቦን

ፈረንሳዊ ታሪክ ጸሐፊ





## ዘላለማዊው መልክት ለመላው ዩኒቨርስ ጭምር ነው፦

እስላም መላው ዩኒቨርስ የሚጓዝበትና የሚመራበት ነው:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{أَفَغَيۡرَ دِينِ ٱللَّهِ يَبۡغُونَ وَلَهُۥٓ أَسۡلَمَ مَن فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ طَوۡعٗا وَكَرۡهٗا وَإِلَيۡهِ يُرۡجَعُونَ ٨٣} [آل عمران: ٨٣]


‹‹በሰማያትና በምድር ያሉ ሁሉ፤በውድም በግድም ለርሱ የታዘዙ [የሰለሙ፣ሙስሊም የሆኑ]፣ወደርሱም የሚመለሱ ሲኾኑ (ከሓዲዎች) ከአላህ ሃይማኖት ሌላን ይፈልጋሉን?››[ኣሊ ዒምራን:83]

በዩኒቨርስ ውስጥ ያለው ማንኛውም ነገር ለተወሰነና ቋሚ ለሆነ ሕግ ተገዥ መሆኑ የሚታወቅ ነው:: ፀሐይ፣ጨረቃ፣ከዋክብትና መሬት ቅንጣት ያህል እንኳ ሊጥሱት በማይችሉና አላህ (ሱ.ወ.) በተፈጥሮ ውስጥ ባኖራቸው ቋሚ ሕግጋት ይመራሉ:: የሰው ልጅም ጭምር አስተውለን ብንመለከት ሙሉ በሙሉ ለአላህ የተፈጥሮ ሕግጋት ተገዥ መሆኑን እንረዳለን:: ሕይወቱን ከሚመራው መለኮታዊ ውሳኔ ውጭ መተንፈስ፣የውሃ የምግብ የብርሃንም ሆነ የሙቀት ፍላጎት ሊሰማው አይችልም፤የሰራ አካላቱ ለዚህ የአላህ (ሱ.ወ.) ውሳኔ ተመሪ ሲሆን እያንዳንዱ አባለ ገላ ተግባሩን ሚፈጽመው በዚህ አላህ (ሱ.ወ.) ባኖረለት የተፈጥሮ ሕግ መሰረት ብቻ ነው::



https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am



ይህ አጠቃላይ መለኮታዊ የተፈጥሮ ሕግም በፍጥረተ ዓለሙ ውስጥ ከግዙፉ የጠፈር ኮከብ እስከ ቅንጣቷ የምድር አቶም ድረስ ምንምና ማንም በውድም ይሁን በግድ የሚገዛለትና የሚመራበት መለኮታዊ ሥርዓት ነው:: በሰማያትና በምድር፣በመካከላቸውም ያለው ሁሉ ለዚህ መለኮታዊ ቅንብር ተገዥና ተመሪ (የሰለመ) እስከሆነ ድረስም እስላም (ለአላህ ተመሪ መሆን) የመላው ዩነቨርስ ሃይማኖት መሆኑ ግልጽ ይሆናል፤እስላም ማለት የአላህን ትእዛዛት በመፈጸምና ከከለከለው በመታቀብ ወደ ለርሱ መግገዛትና ማደር ነውና:: ፀሐይ፣ጨረቃና መሬት፣አየርና ውሃም፣ብርሃን ጨለማና ሙቀትም፣ዛፉና ድንጋዩም፣አራዊትና እንስሳቱም . . ሁሉም ለርሱ ተገዥዎችና ተመሪዎች ናቸው:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَسَخَّرَ لَكُم مَّا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِي ٱلۡأَرۡضِ جَمِيعٗا مِّنۡهُۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَٰتٖ لِّقَوۡمٖ يَتَفَكَّرُونَ ١٣} [الجاثية: ١٣]

‹‹ለናንተም በሰማያት ያለውንና በምድርም ያለውን ሁሉ በመላ ከርሱ ሲኾን የገራላችሁ ነው፤››[አል ጃሢያህ:13]

ሌላው ቀርቶ ጌታውን የማያውቅ፣መኖሩንና ፈጣሪ አምላክ መሆኑን የሚያስተባብል ኢአማኝ፣ወይም ከርሱ ሌላ ባእድ አምልኮ የሚያካሄድና የሚያጋራ ሙሽሪክ ሰው እንኳ ከተፈጠረበት ፍጥረቱ አኳያ መለኮታዊ የተፈጥሮ ሕጉ የሚገዛው በመሆኑ ተገዥና ተመሪ ነው::

የሰውን ልጅ ሁለት ነገሮች ይጋፈጡታል፦

የመጀመሪያው፦ ለርሱ መመራትንና መታዘዝን፣እርሱን መግዛትን፣እርሱን መውደድና ወደርሱ መቃረብን፣እርሱ የሚወደውን ሐቅን፣በጎ ምግባርንና እውነት መናገርን መውደድን፣እርሱ የሚጠላቸውን ውሸት፣ሸርና ተንኮል፣ግፍና በደልን መጥላትን፣እነዚህን ተከትለው የሚመጡ ገንዘብ፣ቤተሰብና ልጅ መውደድን፣የመብላት የመጠጣትና የወሲብ ፍላጎቶችን የመሳሰሉና አላህ (ሱ.ወ.) በሰዎች ውስጥ ያኖራቸው ተፈጥሮአዊ ጉዳዮችን ሁሉ የሚመለከት ነው::



ሁለተኛው፦ የሰው ልጅ መሻትና ምርጫው ነው:: አላህ (ሱ.ወ.) መልክተኞችን ወደ ሰው ልጆች ልኳል፤እውነትን ከሐሰት፣ቅን መመራትን ከጥመት፣በጎውን ከክፉው ይለይበት ዘንድ መላኮታዊ መጻሕፍትን አስተላልፎአል:: ምርጫውን በግልጽ ግንዛቤ ላይ ይመሰርት ዘንድም አእምሮንና የማስተዋል ብቃትን ቸሮታል:: ስለዚህም ከሻ በጎውን መንገድ መርጦ ይከተልና ወደ እውነትና ወደ ቀጥተኛው መንገድ ይመራዋል፤ካስፈለገውም በምርጫው እኩይ መንገድ ይከተልና ወደ ክፋትና ውድመት መንገድ ይወስደዋል:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَقُلِ ٱلۡحَقُّ مِن رَّبِّكُمۡۖ فَمَن شَآءَ فَلۡيُؤۡمِن وَمَن شَآءَ فَلۡيَكۡفُرۡۚ إِنَّآ أَعۡتَدۡنَا لِلظَّٰلِمِينَ نَارًا أَحَاطَ بِهِمۡ سُرَادِقُهَاۚ وَإِن يَسۡتَغِيثُواْ يُغَاثُواْ بِمَآءٖ كَٱلۡمُهۡلِ يَشۡوِي ٱلۡوُجُوهَۚ بِئۡسَ ٱلشَّرَابُ وَسَآءَتۡ مُرۡتَفَقًا ٢٩} [الكهف: ٢٩]

‹‹ ፦ እውነቱም ከጌታችሁ ነው፤የሻም ሰው ይመን፤የሻም ሰው ይካድ፣በላቸው፤እኛ ለበደለኞች አጥርዋ በነሱ የከበበ የኾነችውን እሳት አዘጋጅተናል፤(ከጥም) እርዳታንም ቢፈልጉ፣እንደ ዘይት ዝቃጭ ባለ፣ፊቶችን በሚጠብስ ውሃ፣ይረዳሉ፤መጠጡ ከፋ! መደገፊያይቱም ምንኛ አስከፋች!››[አል ከህፍ:29]

ከመጀመሪያው ነጥብ አንጻር የሰውን ልጅ ከተመለከትነው ከጥንተ መሰረቱ ለአላህ ተመሪ ለመሆን የተፈጠረ፣ለዚሁ የተገራና እንደተቀሩት ፍጥረታት ሁሉ ከዚህ ውጭ መሆን የማይችል መሆኑን እንገነዘባለን::

ከሁለተኛው ነጥብ አኳያ ካስተዋልነው ደግሞ የመምረጥ አቅም የተቸረው፣የፈለገውን የሚመርጥ ከሻው ተመሪ ሙስሊም መሆን ከፈለገም አስተባባይ ከሓዲ መሆን የሚችል ሆኖ እናገኘዋለን:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{إِنَّا هَدَيۡنَٰهُ ٱلسَّبِيلَ إِمَّا شَاكِرٗا وَإِمَّا كَفُورًا ٣}[الإنسان: ٣]

‹‹እኛ፣ወይ አመስጋኝ ወይም ከሓዲ ሲኾን መንገዱን መራነው፤(ገለጽንለት):፡››[አል ደህር:3]

በዚህ ምክንያትም ሰዎችን ሁለት ዓይነት ሆነው እናገኛቸዋለን:: እነሱም፦

ፈጣሪውን የሚያውቅ፣ጌታው ገዥውና አምላኩ መሆኑን አምኖ እርሱን ብቻ የሚያመልክ፣ወዶና ፈቅዶ በሚመርጠው ሕይወቱ የርሱን ሕግና ሥርዓት የሚከተል፣በተፈጥሮው ለጌታው ወደደም ጠላ ተመሪ እንደሆነ ሁሉ

https://www.path-2-happiness.com/am

በፍላጎቱና በምርጫውም ለርሱ ውሳኔ ተገዢ የሆነ ሰው ነው። ሙስሊምነቱን (ለአላህ ተገዢነቱን) ምሉእ ያደረገ ምሉእ ሙስሊምም እንዲህ ዓይነቱ ሰው ሲሆን፤ነቢያትና መልክተኞችን ወደርሱ የላካቸውን፣የዕውቀትና የመማር ችሎታን የቸረውን ፈጣሪ ጌታውን ያወቀ በመሆኑ ዕውቀቱ ትክክለኛ ዕውቀት ሆኗል። አእምሮውን አሰርቶ ግንዛቤንና ማስተዋልን ያጎናጸፈውን አንድ አላህ ብቻ እንጂ ሌላን ላለመግገዛት የወሰነ በመሆኑም አእምሮውና አስተሳሰቡ ትክክለኛ ሆኗል። የመናገርንና የአንድበትን ጸጋ የሰጠውን የአንድ አላህን ጌትነት ብቻ የሚቀበል በመሆኑ አንደበቱም ሐቅን ብቻ የሚናገር ትክክለኛ አንደበት ሆኗል። አሁን በገዛ ምርጫውና በፍላጎቱ በሚሆኑት ነገሮች በአላህ ሕግና መመሪያ ተመሪ በመሆኑ በሕይወቱ ውስጥ የቀረው ነገር እውነት ብቻ ሆኗል። ፍጥረታት ሁሉ የሚግገዙትንና ለወሳኔዎቹ ተገዢ የሆኑትን ጥበበኛውንና ዐዋቂውን አንድ አላህን ብቻ የሚያመልክ በመሆኑም በርሱና በዩኒቨርሱ ውስጥ ባሉት የተቀሩ ፍጥረታት - አላህ (ሱ.ወ.) ለርሱ የተገሩ አድርጓቸዋልና - መካከል የትውውቅና የመናበብ ትስስርም ተመስርቷል። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَمَن يُسۡلِمۡ وَجۡهَهُۥٓ إِلَى ٱللَّهِ وَهُوَ مُحۡسِنٞ فَقَدِ ٱسۡتَمۡسَكَ بِٱلۡعُرۡوَةِ ٱلۡوُثۡقَىٰۗ وَإِلَى ٱللَّهِ عَٰقِبَةُ ٱلۡأُمُورِ ٢٢} [لقمان: ٢٢]


‹‹እርሱ መልካም ሠሪ ኾኖ ፊቱን ወደ አላህ የሚሰጥም ሰው፣ጠንካራን ገመድ በእርግጥ ጨበጠ፤የነገሩም ሁሉ ፍጻሜ ወደ አላህ ነው።››[ሉቅማን:22]

### ልዩነቱ የት የሌለ ነው

‹‹እንደ ክርስቲያን በቁርኣናዊው እሳቤ ተውሒድ (የአላህ አንድነት) መርሕና በሥላሴ እምነቴ መካከል ንጽጽር ከማድግ ውጭ ሌላ አማራጭ አልነበረኝም። እናም የሥላሴ መርሕ በብዙ እጅ ከእስላማዊው መርሕ ያነሰ መሆኑን ደረስኩበት። በማንኛውም ሃይማኖት ውስጥ በአላህ ማመን ዋነኛውና የመጀመሪያው መርሕ ከመሆኑ አንጻር ልክ በዚህ ነጥብ ላይ በክርስትና ላይ እምነት ማጣት ጀመርኩ። በትክክለኛው ሃይማኖታዊ ግንዛቤ እምነቴ የተሳሳተ ከሆነ፣ያ ማለት ማንኛውም ሌላ ነገር ጥቅም አልባ ከንቱና ትርጉም የለሽ ሆኖ ይቀራል ማለት ነው።››

ናጂሞ ራሞኒ
ጋናዊ ሰባኪ





## ዘላለማዊው መልክት የሁሉም ነቢያትና መልክተኞች ሃይማኖት ነው፦

እስላም አላህ ለመላው የሰው ልጅ ያስተላለፍው ዩኒቨርሳል ሃይማኖት ነው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{فَإِلَٰهُكُمۡ إِلَٰهٞ وَٰحِدٞ فَلَهُۥٓ أَسۡلِمُواْۗ وَبَشِّرِ ٱلۡمُخۡبِتِينَ ٣٤} [الحج: ٣٤]

‹‹አምላካችሁም አንድ አምላክ ብቻ ነው፤ለርሱም ብቻ ታዘዙ፤ለአላህ ተዋራጆችንም አብስራቸው።›› [አል ሐጅ:34]

እስላም የሁሉም ነቢያትና መልክተኞችም ሃይማኖት ነው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{قُولُوٓاْ ءَامَنَّا بِٱللَّهِ وَمَآ أُنزِلَ إِلَيۡنَا وَمَآ أُنزِلَ إِلَىٰٓ إِبۡرَٰهِـۧمَ وَإِسۡمَٰعِيلَ وَإِسۡحَٰقَ وَيَعۡقُوبَ وَٱلۡأَسۡبَاطِ وَمَآ أُوتِيَ مُوسَىٰ وَعِيسَىٰ وَمَآ أُوتِيَ ٱلنَّبِيُّونَ مِن رَّبِّهِمۡ لَا نُفَرِّقُ بَيۡنَ أَحَدٖ مِّنۡهُمۡ وَنَحۡنُ لَهُۥ مُسۡلِمُونَ ١٣٦} [البقرة: ١٣٦]

‹‹በአላህና ወደኛ በተወረደው (ቁርኣን)፣ወደ ኢብራሂምም፣ወደ እስማዒልና ወደ ኢስሐቅም፣ወደ ያዕቁብና ወደ ነገዶቹም በተወረደው፣በዚያም ሙሳና ዒሳ በተሰጡት፣በዚያም ነቢያት ሁሉ ከጌታቸው በተሰጡት፣ከነርሱ በአንድም መካከል የማንለይ ስንኾን አመንን፤እኛም ለርሱ (ለአላህ) ታዛዦች ነን በሉ።››[አል በቀራህ: 136]

ሁሉም የአላህ መልክተኞች አምነውበታል፤ለአላህ (ሱ.ወ.) መስለማቸውንም አውጀው ወደርሱ እንዲመጡም ለሌሎች ጥሪ አድርገዋል። አላህ (ሱ.ወ.) ነቢዩ ኑሕን عليه السلام አስመልክቶ እንዲህ ብሏል፦

{وَٱتۡلُ عَلَيۡهِمۡ نَبَأَ نُوحٍ إِذۡ قَالَ لِقَوۡمِهِۦ يَٰقَوۡمِ إِن كَانَ كَبُرَ عَلَيۡكُم مَّقَامِي وَتَذۡكِيرِي بِـَٔايَٰتِ ٱللَّهِ فَعَلَى ٱللَّهِ تَوَكَّلۡتُ فَأَجۡمِعُوٓاْ أَمۡرَكُمۡ وَشُرَكَآءَكُمۡ ثُمَّ لَا يَكُنۡ أَمۡرُكُمۡ عَلَيۡكُمۡ غُمَّةٗ ثُمَّ ٱقۡضُوٓاْ إِلَيَّ وَلَا تُنظِرُونِ ٧١ فَإِن تَوَلَّيۡتُمۡ فَمَا سَأَلۡتُكُم مِّنۡ أَجۡرٍۖ إِنۡ أَجۡرِيَ إِلَّا عَلَى ٱللَّهِۖ وَأُمِرۡتُ أَنۡ أَكُونَ مِنَ ٱلۡمُسۡلِمِينَ ٧٢} [يونس: ٧١- ٧٢]

‹‹የኑሕንም ወሬ በነሱ ላይ አንብብላቸው፤ለሕዝቦቼ ባለ ጊዜ (አስታውስ)፤፦ ሕዝቦቼ ሆይ! በናንተ ውስጥ ብዙን ጊዜ መቆየቱ በአላህም ታምራት ማስታወሴ በናንተ ላይ የከበደ ቢኾን፤በአላህ ላይ ተጠግቻለሁ፣ነገራችሁንም ከምታጋሩዋቸው (ጣዖታት) ጋር ኾናችሁ ቁረጡ፤ከዚያም ነገራችሁ በናንተ ላይ ድብቅ አይኹን (ግለጹት)፤ከዚያም (የሻችሁትን) ወደኔ አድርሱ፤ጊዜም አትስጡኝ (ከምንም አልቆጥራችሁም)::››[ዩኑስ:71-72]

ነቢዩ ኢብራሂምን (عليه السلام) አስመልክቶም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{إِذۡ قَالَ لَهُۥ رَبُّهُۥٓ أَسۡلِمۡۖ قَالَ أَسۡلَمۡتُ لِرَبِّ ٱلۡعَٰلَمِينَ ١٣١}[البقرة: ١٣١]

‹‹ጌታው ለርሱ ታዘዝ [ስለም] ባለው ጊዜ (መረጠው)፤ለዓለማት ጌታ ታዘዝኩ [ሰለምኩ] አለ::››[አልበቀራህ:131]

ኢብራሂምም (عليه السلام) ልጆቻቸውንና ዝርዮቻቸውን ከርሳቸው በኋላም እስላምን እንዲከተሉ አዘዋል:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَوَصَّىٰ بِهَآ إِبۡرَٰهِـۧمُ بَنِيهِ وَيَعۡقُوبُ يَٰبَنِيَّ إِنَّ ٱللَّهَ ٱصۡطَفَىٰ لَكُمُ ٱلدِّينَ فَلَا تَمُوتُنَّ إِلَّا وَأَنتُم مُّسۡلِمُونَ ١٣٢ أَمۡ كُنتُمۡ شُهَدَآءَ إِذۡ حَضَرَ يَعۡقُوبَ ٱلۡمَوۡتُ إِذۡ قَالَ لِبَنِيهِ مَا تَعۡبُدُونَ مِنۢ بَعۡدِيۖ قَالُواْ نَعۡبُدُ إِلَٰهَكَ وَإِلَٰهَ ءَابَآئِكَ إِبۡرَٰهِـۧمَ وَإِسۡمَٰعِيلَ وَإِسۡحَٰقَ إِلَٰهٗا وَٰحِدٗا وَنَحۡنُ لَهُۥ مُسۡلِمُونَ ١٣٣}[البقرة: ١٣٢-١٣٣]

‹‹በርሷም (በሕግጋቱ) ኢብራሂም ልጆቹን አዘዘ፤ያዕቆብም፣(እንደዚሁ አዘዘ)፤ልጆቼ ሆይ! አላህ ለናንተ ሃይማኖትን መረጠ፤ስለዚህ እናንተ ሙስሊሞች ኾናችሁ እንጂ አትሙቱ (አላቸው):: ያዕቆብን ሞት በመጣበት ጊዜ፣ለልጆቹ ከኔ በኋላ ማንን ትግገዛላችሁ? ባለ ጊዜ፣ቀራቢዎች ነበራችሁን? (እነርሱም) አምላክህንና የአባቶችህን፣የኢብራሂምን፣የእስማዒልንና የእስሐቅንም አምላክ፣አንድ የኾነውን አምላክ፣ እኛ ለርሱ ፍጹም ታዛዦች [ሙስሊሞች] ኾነን እናመልካለን አሉ::››[አልበቀራህ:132-133]

ስለ ነቢዩ ሙሳም (عليه السلام) አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَقَالَ مُوسَىٰ يَٰقَوۡمِ إِن كُنتُمۡ ءَامَنتُم بِٱللَّهِ فَعَلَيۡهِ تَوَكَّلُوٓاْ إِن كُنتُم مُّسۡلِمِينَ ٨٤}[يونس: ٨٤]



‹‹ሙሳም አለ፦ ሕዝቦቼ ሆይ! በአላህ አምናችሁ እንደኾነ፣በርሱ ላይ ተጠጉ፤ታዛዦች [ሙስሊሞች] እንደ ኾናችሁ (አላህ ላይ ትመካላችሁ)::››[ዩኑስ:84]

የአልመሲሕ ዒሳን (عليه السلام) ዜና አስመልክቶም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَإِذۡ أَوۡحَيۡتُ إِلَى ٱلۡحَوَارِيِّـۧنَ أَنۡ ءَامِنُواْ بِي وَبِرَسُولِي قَالُوٓاْ ءَامَنَّا وَٱشۡهَدۡ بِأَنَّنَا مُسۡلِمُونَ ١١١}[المائدة: ١١١]

‹‹ወደ ሐዋርያትም በኔና በመልክተኛዬ እመኑ፣በማለት ባዘዝኩ ጊዜ፣(አስታውስ)፤አመንን፤እኛም ሙስሊሞች መኾናችንን፣መስክር አሉ::››[አልማእዳህ:111]

እስላም ነቢዩና መልክተኛው ሙሐመድ ﷺ ይዘው የመጡትና ለመላው የሰው ዘር የተላለፈ፣አላህ (ሱ.ወ.) ለባሮቹ ምሉእ አድርጎት ከሃይማኖት በኩል የወደደላቸው የመጨረሻውና የመደምደሚያው መለኮታዊ መልክት (መገለጥ) ነው:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{ٱلۡيَوۡمَ أَكۡمَلۡتُ لَكُمۡ دِينَكُمۡ وَأَتۡمَمۡتُ عَلَيۡكُمۡ نِعۡمَتِي وَرَضِيتُ لَكُمُ ٱلۡإِسۡلَٰمَ دِينٗا}[المائدة: ٣]

‹‹ዛሬ ሃይማኖታችሁን ለናንተ ሞላሁላችሁ:: ጸጋዬንም በናንተ ላይ ፈጸምኩ:: ለናንተም እስላምን ከሃይማኖት በኩል ወደድኩ፤››[አል ማእዳህ:3]

በዚህ ክቡር ቁርኣናዊ አንቀጽ ውስጥ አላህ (ሱ.ወ.) ለመላው የሰው ልጅ ከሃይማኖት በኩል እስላምን የወደደላቸውና ፈጽሞ የማይጠላው መሆኑን ተናግሯል:: እውነተኛው ሃይማኖት እርሱ ብቻ መሆኑንና ከርሱ በስተቀር ከማንም ሰው ሌላ ሃይማኖት ተቀባይነት እንደሌለውም አውጇል:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{إِنَّ ٱلدِّينَ عِندَ ٱللَّهِ ٱلۡإِسۡلَٰمُ}[آل عمران: ١٩]

‹‹አላህ ዘንድ (የተወደደ) ሃማኖት እስላም ብቻ ነው፤››[አሊ ዒምራን:19]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَمَن يَبۡتَغِ غَيۡرَ ٱلۡإِسۡلَٰمِ دِينٗا فَلَن يُقۡبَلَ مِنۡهُ وَهُوَ فِي ٱلۡأٓخِرَةِ مِنَ ٱلۡخَٰسِرِينَ ٨٥}[آل عمران: ٨٥]

‹‹ከእስላም ሌላ ሃይማኖትን የሚፈልግ ሰው፣ፈጽሞ ከርሱ ተቀባይ የለውም፤እርሱም በመጨረሻይቱ ዓለም ከከሳሪዎቹ ነው::››[አሊ ዒምራን:85]

አላህ (ሱ.ወ.) በመጀመሪያው አንቀጽ ውስጥ እርሱ ዘንድ ተቀባይነት ያለው ሃይማኖት እስላም ብቻ መሆኑን ሲያረጋግጥ፣በሁለተኛው አንቀጽ ውስጥ ደግሞ

https://www.path-2-happiness.com/am

www.path-2-happiness.com/am

ከእስላም ውጭ ከማንም ሌላ ሃይማኖትን እንደማይቀበልና ከሞት በኋላ መድህን የሚያገኙት የመታደል ባለቤቶች ሙስሊሞች ብቻ መሆናቸውን፣ሙስሊሞች ሳይሆኑ የሚሞቱ ሁሉ በወዲያኛው ሕይወት በእሳተ ገሀነም የሚቀጡ ከሳሪዎች መሆናቸውንም አስታውቋል:: ነቢያት ሁሉ ለአላህ የሰለሙና የተገዙ ሙስሊሞች መሆናቸውና ለአላህ ሰልመው ለርሱ ከማይገዙት ነጻ መሆናቸውን ያወጁትም ለዚህ ነው:: መዳንንና መታደልን የፈለገና እውነተኛው የሙሳና የዒሳ ﵇ ተከታይ ይሆን ዘንድ የወደደ ይሁዲና ክርስቲያን ሁሉ፣ሙሳ ዒሳ፣ሙሐመድና ﷺ ሁሉም የአላህ መልክተኞች ሙስሊሞችና ለእስላም ጥሪ ያደረጉ በመሆናቸው፣የመጨረሻውን የእስላም መልክተኛ ሙሐመድን ﷺ መከተል ይኖርበታል:: እስላም የሁሉም ነቢያትና መልክተኞች ሃይማኖት በመሆኑ ከመደምደሚያቸው ከሙሐመድ ﷺ መላክ በኋላ ለኖረ ማንኛውም ሰው እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሙሐመድን አምኖ በመቀበል ካልተከተላቸውና በቁርኣን ካልተመራ በስተቀር ለአላህ ተገዥ ሙስሊም ነኝ ብሎ ራሱን ሊጠራ አይችልም:: ይህን በማስመልከት የአላህ መልክተኛ ﷺ እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹ነፍሴ በእጁ በሆነችው [አላህ] እምላለሁ፣ከዚህ ሕዝብ (ኡምማ) ውስጥ ስለኔ የሰማና በተላኩበት ነገር ሳያምን የሞተ ማንኛውም ይሁዲ ይሁን ክርስቲያን (ዕጣ ፈንታው) ከእሳት ሰዎች አንዱ መሆን ብቻ ነው::›› [በሙስሊም የተዘገበ]

## ገሩ እስላም

‹‹የታላቁ እስላም ገርነት ከፍጹማዊው ተውሒድ የመጣ ነው፤በዚህ ገርነት ውስጥም የእስላም የጥንካሬ ምስጢር ይገኛል:: እስላምን መረዳት በጣም ቀላል ሲሆን ሃይማኖቱ በሌሎች ሃይማኖቶች ውስጥ ከምናያቸውና ሚዘናዊ አእምሮ ከማይቀበላቸው እርስበርስ ከሚጣረሱ ነገሮችና ከውስብስብ ድብቅ ምስጢራትም የጠራ ነው:: አንድ ብቸኛ አምላክ መኖሩን ከሚናገረውና ሰዎች ሁሉ አላህ ፊት እኩል ናቸው ከሚለው የእስላም መሰረታዊ መርህ ይበልጥ ግልጽ የሆነ ነገር የለም::››

ጎስታፍ ሎቦን

ፈረንሳዊ ታሪክ ጸሐፊ





## የዘላለማዊው መልክት ምሉእነት፦

አላህ (ሱ.ወ.) በመልክተኛ በሙሐመድ ﷺ አማካይነት ለመላው የሰው ልጆች ያስተላለፈው ይህ እስላም በአንድ አላህ ብቻ የማመን የተውሒድ ሃይማኖት ነው:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{هُوَ ٱلْحَىُّ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ فَٱدْعُوهُ مُخْلِصِينَ لَهُ ٱلدِّينَ ۗ ٱلْحَمْدُ لِلَّهِ رَبِّ ٱلْعَٰلَمِينَ ﴿٦٥﴾ ۞ قُلْ إِنِّى نُهِيتُ أَنْ أَعْبُدَ ٱلَّذِينَ تَدْعُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ لَمَّا جَآءَنِىَ ٱلْبَيِّنَٰتُ مِن رَّبِّى وَأُمِرْتُ أَنْ أُسْلِمَ لِرَبِّ ٱلْعَٰلَمِينَ ﴿٦٦﴾} [غافر: ٦٥ـ٦٦]

‹‹ብታጋራ ሥራህ በእርግጥ ይታበሳል፤በእርግጥም ከከሓዲዎቹ ትኾናለህ ማለት ወደ አንተም ወደነዚያም ካንተ በፊት ወደነበሩት በእርግጥ ተወርዷል:: እርሱ ብቻ (ሁል ጊዜ) ሕያው ነው፤ከርሱ ሌላ አምላክ የለም፤ሃይማኖትንም ለርሱ ያጠራችሁ ስትኾኑ፣ምስጋና ለዓለማት ጌታ ለአላህ ይኹን፣የምትሉ ኾናችሁ ተገዙት:: እኔ ከጌታዬ አስረጂዎች በመጡልኝ ጊዜ፣እነዚያን ከአላህ ሌላ የምትግገዙዋቸውን እንዳልገዛ ተከልክያለሁ፤ለዓለማት ጌታም እንድግገዛ [እንድሰልም] ታዝዠለሁ በላቸው::››[አልሙእሚን:65-66]

እስላም አለአላህ (ሱ.ወ.) ብቻ ሃይማኖትን ፍጹም አድርጎ ማጥራት ነው:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{ءَأَرْبَابٌ مُّتَفَرِّقُونَ خَيْرٌ أَمِ ٱللَّهُ ٱلْوَٰحِدُ ٱلْقَهَّارُ ﴿٣٩﴾ مَا تَعْبُدُونَ مِن دُونِهِۦٓ إِلَّآ أَسْمَآءً سَمَّيْتُمُوهَآ أَنتُمْ وَءَابَآؤُكُم مَّآ أَنزَلَ ٱللَّهُ بِهَا مِن سُلْطَٰنٍ ۚ إِنِ ٱلْحُكْمُ إِلَّا لِلَّهِ ۚ أَمَرَ أَلَّا تَعْبُدُوٓا۟ إِلَّآ إِيَّاهُ} [يوسف: ٣٩ـ ٤٠]

‹‹የተለያዩ (ከብር ከወርቅ ከእንጨት የተሠሩ) አምላኮች ይሻላሉን ወይስ አሸናፊው አንዱ አላህ? ከርሱ ሌላ እናንተና አባቶቻችሁ (አማልክት ብላችሁ) የጠራችኋቸውን ስሞች እንጅ አትግገዙም፤አላህ በርሷ ምንም አስረጅ አላወረደም፤ፍርዱ የአላህ እንጅ የሌላ አይደለም፤እርሱን እንጅ ሌላን እንዳትግገዙ አዟል፤ይህ ትክክለኛው ሃይማኖት ነው፤ግን አብዛኞቹ ሰዎች አያውቁም::››[ዩሱፍ :39-40]

እስላም በእውነታውና በጠራ ይዘቱ ቢቀርብለት የሰው ልጅ ተፈጥሮ የሚታዘዝለትና የሚቀበለው የአስተዋይ ሚዘናዊ አእምሮ ሃይማኖት ነው:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{ذَٰلِكَ ٱلدِّينُ ٱلْقَيِّمُ وَلَٰكِنَّ أَكْثَرَ ٱلنَّاسِ لَا يَعْلَمُونَ ﴿٤٠﴾} [يوسف: ٤٠]

‹‹ይህ ትክክለኛው ሃይማኖት ነው፤ግን አብዛኞቹ ሰዎች አያውቁም::››[ዩሱፍ: -40]

የማስረጃ የአስረጅና የማሳመኛ ነጥብ የአቀራረብ ስልት ያለው ሃይማኖትም

ነው:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{قُلْ هَاتُوا۟ بُرْهَٰنَكُمْ إِن كُنتُمْ صَٰدِقِينَ ﴿٦٤﴾} [النمل: ٦٤]

‹‹እውነተኞች እንደ ኾናችሁ፣አስረጃችሁን አምጡ በላቸው::››[አልነምል:64]

የእፎይታ፣የመታደል፣የደስተኝነትና የመረጋጋት ሃይማኖትም ነው፦

{مَنْ عَمِلَ صَٰلِحًا مِّن ذَكَرٍ أَوْ أُنثَىٰ وَهُوَ مُؤْمِنٌ فَلَنُحْيِيَنَّهُۥ حَيَوٰةً طَيِّبَةً}[النحل: ٩٧]

‹‹ከወንድ ወይም ከሴት፣እርሱ አማኝ ኾኖ በጎን የሠራ፣መልካም ኑሮን በእርግጥ እናኖረዋለን፤ይሠሩትም ከነበሩት ነገር በመልካሙ ምንዳቸውን እንመነዳቸዋለን::››[አል ነሕል:97]

ሙሐመድ ﷺ ከአላህ (ሱ.ወ.) ተልከው ይዘውት በመጡት ሃይማኖት መልካም የሆኑ ነገሮች ሁሉ የተፈቀዱበት፣ጎጂ የሆኑ እኩይ ነገሮች ሁሉ የተከለከሉበት፣በበጎና ሰናይ ተግባራት ሁሉ የሚያዝ፣ከእኩይና ክፉ ሥራዎች ሁሉ የሚከለክል ሃይማኖት ነው:: ገርና ቀላል የሆነ፣አስቸጋሪ ነገር የሌለበት፣መሸከምና መወጣት የማይችሉትን ኃላፊነት በሰዎች ጫንቃ ላይ የማይጥል ምቹ ሃይማኖት ነው:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{ٱلَّذِينَ يَتَّبِعُونَ ٱلرَّسُولَ ٱلنَّبِيَّ ٱلْأُمِّيَّ ٱلَّذِى يَجِدُونَهُۥ مَكْتُوبًا عِندَهُمْ فِى ٱلتَّوْرَىٰةِ وَٱلْإِنجِيلِ يَأْمُرُهُم بِٱلْمَعْرُوفِ وَيَنْهَىٰهُمْ عَنِ ٱلْمُنكَرِ وَيُحِلُّ لَهُمُ ٱلطَّيِّبَٰتِ وَيُحَرِّمُ عَلَيْهِمُ ٱلْخَبَٰٓئِثَ وَيَضَعُ عَنْهُمْ إِصْرَهُمْ وَٱلْأَغْلَٰلَ ٱلَّتِى كَانَتْ عَلَيْهِمْ ۚ فَٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ بِهِۦ وَعَزَّرُوهُ وَنَصَرُوهُ وَٱتَّبَعُوا۟ ٱلنُّورَ ٱلَّذِىٓ أُنزِلَ مَعَهُۥٓ ۙ أُو۟لَٰٓئِكَ هُمُ ٱلْمُفْلِحُونَ ﴿١٥٧﴾}[الأعراف: ١٥٧]

‹‹ለነዚያ፣ያንን እነሱ ዘንድ በተውራትና በኢንጂል ተጽፎ የሚያገኙትን፣የማይጽፍና የማያነብ ነቢይ የኾነውን መልክተኛ የሚከተሉ ለኾኑት፣(በእርግጥ እጽፋታለሁ)፤በበጎ ሥራ ያዛቸዋል፤ከክፉም ነገር ይከለክላቸዋል፤መልካም ነገሮችንም ለነርሱ ይፈቅድላቸዋል፤መጥፎ ነገሮችንም በነሱ ላይ እርም ያደርግባቸዋል:: ከነሱም ላይ ሸክማቸውንና እነዚያንም በነሱ ላይ የነበሩትን እንዛዝላዎች (ከባድ ሕግጋቶች) ያነሳላቸዋል፤እነዚያም በርሱ ያመኑ፣ያከበሩትም፣የረዱትም፣ያንንም ከርሱ ጋር የተወረደውን ብርሃን የተከተሉ፣እነዚያ እነሱ የሚድኑ ናቸው::››[አል አዕራፍ:157]



### ተገዥነት ለአላህ ብቻ ነው

‹‹የእስላም የተውሒድ ሥርዓት ቆም ብዬ ብዙ እንዳስተነትነው አድርጎኛል:: ከእስላም አበይተ ገጽታዎች ዋነኛው እርሱ ነውና:: ተውሒዱ ለአንድ አላህ ብቻ እንጂ ለማንም ሰብአዊ ፍጡር ተገዥ እንዳልሆን ያደርገኛል:: ሰውን ነጻ አድርጎ ለሌ ማንም ሰብአዊ ፍጡር እንዳያጎበድድ ያደርገዋል::እውነተኛው ነጻነትም ይኸ ነው፤ተገዥነት ለአንድ አላህ ብቻ ነው::››

ኢብራሂም ኸሊል

ግብጻዊ ሰባኪ ቄስ

እስላም ለሁሉም ዘመንና በየትኛውም ስፍራ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ገርና ምቹ የሆነ የተሟላ ሃይማኖት ሲሆን፣የሰው ልጆች ለዚህች ዓለም ሕይወታቸውና ለመጪው ዘላለማዊ ሕይወታቸው የሚያስፈልጓቸውን መንፈሳዊና ቁሳዊ ነገሮች ሁሉ ያካተተ እምነት ነው::

የመታደል፣የደስተኝነትና የሕሊና ዕረፍት መንገድ ነው:: የዕውቀትና የስልጣኔ፣የፍትሕና የደግነት፣የክብርና የነጻነት፣የሁሉም በጎና ሰናይ ነገሮች ጎዳና ነው:: ምንኛ ምልእ ምንኛ ድንቅ ሃይማኖት!! በጎ ሠሪ ሆኖ ራሱን ለአላህ (ሱ.ወ.) ተገዥ አድርጎ ፊቱን ወስኖ ከሰለመ ሰው ይበልጥ ያማረ ማን አለና? አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦


{وَمَنْ أَحْسَنُ دِينًا مِّمَّنْ أَسْلَمَ وَجْهَهُۥ لِلَّهِ وَهُوَ مُحْسِنٌ وَٱتَّبَعَ مِلَّةَ إِبْرَٰهِيمَ حَنِيفًا ۗ وَٱتَّخَذَ ٱللَّهُ إِبْرَٰهِيمَ خَلِيلًا ﴿١٢٥﴾}[النساء: ١٢٥]

‹‹እርሱም መልካም ሠሪ ኾኖ ፊቱን ለአላህ ከሰጠና የኢብራሂምንም መንገድ ቀጥተኛ ሲኾን፣ከተከተለ ሰው፣ይበልጥ ሃይማኖቱ ያማረ ማነው? አላህም ኢብራሂምን ፍጹም ወዳጅ አድርጎ ያዘው::››[አልኒሳእ:125]

ይህ ካንተ ከራስህ ይበልጥ ለአንተ አሳቢና ርህሩህ ከሆነው ከፈጣሪ አምልክህ የተላለፈልህ ጥሪ ነው:: ከጨለማ ወደ ብርሃን ትወጣ ዘንድ የቀረበልህ ጥሪ ነው:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{قُلْ يَٰٓأَهْلَ ٱلْكِتَٰبِ تَعَالَوْا۟ إِلَىٰ كَلِمَةٍ سَوَآءٍۭ بَيْنَنَا وَبَيْنَكُمْ أَلَّا نَعْبُدَ إِلَّا ٱللَّهَ وَلَا نُشْرِكَ بِهِۦ شَيْـًٔا وَلَا يَتَّخِذَ بَعْضُنَا بَعْضًا أَرْبَابًا مِّن دُونِ ٱللَّهِ ۚ فَإِن تَوَلَّوْا۟ فَقُولُوا۟ ٱشْهَدُوا۟ بِأَنَّا مُسْلِمُونَ ﴿٦٤﴾}[آل عمران: ٦٤]

‹‹የመጽሐፉ ባለቤቶች ሆይ! በኛና በናንተ መካከል ትክክል ወደኾነች ቃል ኑ፤(እርሷም) አላህን እንጅ ሌላን ላንገዛ፣በርሱም ምንንም ላናጋራ፣ከፊላችንም ከፊሉን ከአላህ ሌላ አማልክት አድርጎ ላይይዝ ነው፤በላቸው:: እምቢ ቢሉም፦



### ሃይማኖትና ዓለማዊ ሕይወትን በጥምረት

‹‹ይህ ወደር የሌለው የሃይማኖታዊና ዓለማዊ ተጽእኖ ፈጣሪነት ልዩ ውሕደት፣በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ልዩና ታላቅ ተጽእኖ ፈጣሪ ግለሰብ ተደርጎ እንዲወሰድ ያደርገዋል::››

ማይክል ሃርት

አሜሪካዊ ጸሐፊ



### ለምን አንሆንም?!

‹‹እስላም ይኸ ከሆነ፣ሁላችንም ሙስሊሞች ለምን አንሆንም?!››

ጎቴ

ጀርመናዊ የስነጽሑፍ ሰው

https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am

እኛ ሙስሊሞች መኾናችንን መስክሩ በሏቸው፡፡››[አለ. ዒምራን፡64]

ራሱን ለአላህ (ሱ.ወ.) ተገዥ አድርጎ ለርሱ ከተመራ ሰው በተቃራኒ ደግሞ፣ለዚህ ሃይማኖት ትክክለኛነትና እውነተኛነት አረጋጋጭና አስረጅ የሆኑ ታምራትና ምልክቶች እየጎረፉለት አላህ ያነጸበትን ንጹሕ ተፈጥሮ በክህደትና በማስተባበል መጋረጃ ሸፍኖ፣ተውሒድን በመጻረር በአላህ ማጋራትን (ሺርክን)፣ከእውነት ብርሃን፣ከእርግጠኝነትና ከቀን መመሪያ ይልቅ ተረትና ቅዠትን ለራሱ የመረጠ ሌላ ሰው እናገኛለን፡፡

ለአንድ አላህ ብቻ አገልጋይ ከመሆን ይልቅ ቀሳውስትና ካህናትን ለመሳሰሉ መሰሉ ለሆኑ ሰብአዊ ፍጡራንና ለመልክተኞችም ጭምር ራሱን ተገዥ ባሪያ ያደረገ ሰው፣ንጹሕ ተፈጥሮውን በክሏል፡፡ ሰብአዊ አእምሮውን አውልቆ አስቀምጧል፡፡ የጠራ ተፈጥሮውን ወደ ጎን ብሎ ለስሜታዊ ዝንባሌዎችና ለተለያዩ ውዥንብሮች ተገዥ ሆኗል፤የሚወለድ ሕጻን ሁሉ የሚወለደው በተፈጥሮው እስላምን ይዞ ነውና፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፡-

{فِطۡرَتَ ٱللَّهِ ٱلَّتِي فَطَرَ ٱلنَّاسَ عَلَيۡهَاۚ لَا تَبۡدِيلَ لِخَلۡقِ ٱللَّهِۚ ذَٰلِكَ ٱلدِّينُ ٱلۡقَيِّمُ وَلَٰكِنَّ أَكۡثَرَ ٱلنَّاسِ لَا يَعۡلَمُونَ ٣٠} [الروم: ٣٠]

‹‹የአላህን ፍጥረት ያችን አላህ ሰዎችን በርስዋ ላይ የፈጠረባትን (ሃይማኖት ያዙዋት)፤የአላህን ፍጥረት መለወጥ የለም፤ይህ ቀጥተኛ ሃይማኖት ነው፤ግን አብዛኞዎቹ ሰዎች አያውቁም፡፡››[አል ሩም፡30]

አሁን አንባቢ ራሱ በአላህ ያስተባበለ ሰው የተዘፈቀበትን የከፋ ጥመትና ግልጥ ማፈንገጥ መገመት ይችላል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፡-

{هُوَ ٱلَّذِي جَعَلَكُمۡ خَلَٰٓئِفَ فِي ٱلۡأَرۡضِۚ فَمَن كَفَرَ فَعَلَيۡهِ كُفۡرُهُۥۖ وَلَا يَزِيدُ ٱلۡكَٰفِرِينَ كُفۡرُهُمۡ عِندَ رَبِّهِمۡ إِلَّا مَقۡتٗاۖ وَلَا يَزِيدُ ٱلۡكَٰفِرِينَ كُفۡرُهُمۡ إِلَّا خَسَارٗا ٣٩}[فاطر: ٣٩]

‹‹እርሱ ያ በምድር ውስጥ ምትኮች ያደረጋችሁ ነው፤የካደም ሰው ክሕደቱ በርሱው ላይ ብቻ ነው፤ከሓዲዎችንም ክሕደታቸው ከጌታቸው ዘንድ መጠላትን እንጂ ሌላ አይጨምርላቸውም፤ከሓዲዎችንም ክሕደታቸው ኪሳራን እንጂ አይጨምርላቸውም፤››[ፋጢር፡39]


### ሙሐመድ በመልክቱ ላይ ያለው መተማመን

‹‹የነቢዩ ደብዳቤዎች የደረሳቸው ነገስታትና ገዥዎች፣እንዲታዘዙት ጥሪ በሚያደርግላቸው በዚህ ተራ ሰው ምናልባት ተገርመው ሊሆን ይችላል፡፡ እነዚህን ደብዳቤዎች መላክ ግን ሙሐመድ በራሱና በመልክቱ ላይ ያለው መተማመንና ጽናት ምን ያህል እንደነበረ ያሳየናል፡፡ በዚህ መተማመንና በዚህ ጽኑ እምነት ለሕዝቦቹ የጥንካሬ፣የልዕልና እና የእምቢ ባይነት ምክንያትና መረማመጃዎችን አመቻችቶላቸዋል፡፡ ከምድረበዳ ነዋሪነት በዘመኑ ይታወቅ ከነበረው ዓለም የግማሹ ገዥ ጌቶች ወደ መሆን አሸጋገሯቸዋል፡፡ ሙሐመድ የሞተው እርስበርስ ሲናቆሩ የኖሩትን የዐረብ ነገዶች ቀናኢነትና ወኔ ከውስጡ የሚደፍቅ አንድ ሕዝብ (ኡምማ) ካደረገ በኋላ ነበር፡፡››

ጀዋር ላል ኔህሩ


የመጀመሪያው የሕንድ ጠቅላይ ሚኒስትር





የዚህ የመልክተ እስላም መሰረቶች ምንጮችና ልዩ ባሕርያት ምንድን ናቸው?

## የሕግና ድንጋጌ አወጣጥ መሰረቶች



### የሙሐመድ ነቢይነት መልክት

‹‹ሙሐመድ በዐረባዊው ማሕበረሰባዊ አካባቢ የሚከተሉትን ሁለት ገጽታዎች በማስፈን ተልእኮውን እውን ለማድረግ ነው ሕይወቱን የሰጠው፡፡ እነሱም፦ ሃይማኖታዊ ፍካሬን በተውሒድ ላይ የማነጽና አስተዳደርን በተመለከተ ሕግና ሥርዓትን የማስፈን ገጽታዎች ናቸው፡፡ ምስጋና ተውሒድና የአስፈጻሚ ስልጣንን አጣምሮ ለያዘው የእስላም አጠቃላይ ሥርዓት ይሁንና ይህ በተግባር ተፈጽሟል፡፡ በዚህም ምክንያት እስላም ዐረቦችን ከማይም ሕዝብነት ወደ ስልጡን ሕዝብነት ያሸጋገረ ወደፊት የሚፈናጠር ኃያል ጥንካሬ ሊያገኝ ችሏል፡፡››

አርኖልድ ቶዊንቢ

እንግሊዛዊ ታሪክ ጸሐፊ

እስላማዊው ሸሪዓ ለሰው ልጆች ሁሉ በየትኛውም ዘመንና ስፍራ ተስማሚ እንዲሆን የሚያደርጉት መሰረቶችና መደላድሎች አሉት፡፡ ከነዚህም መካከል የሚከተሉትን እናገኛለን፦

### አንደኛ - ገርነትና ችግር አስወጋጅነት፦

ሁሉም ሸሪዓዊ ግዴታዎች ኃላፊነቱ ከሚመለከታቸው ሰዎች አቅምና ችሎታ በላይ የሚሆኑ አይደሉም፡፡ ሃይማኖቱ ገር በመሆኑ ከተለመዱ ሥራዎች ተለይተው ለአፈጻጸም አስቸጋሪ የሆኑ ነገሮች የሉበትም፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፡-

{يُرِيدُ ٱللَّهُ بِكُمُ ٱلۡيُسۡرَ وَلَا يُرِيدُ بِكُمُ ٱلۡعُسۡرَ}[البقرة: ١٨٥]

‹‹አላህ በናንተ ገሩን (ነገር) ይሻል፤በናንተም ችግሩን አይሻም፤››[አልበቀራህ፡185]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፡-

{يُرِيدُ ٱللَّهُ أَن يُخَفِّفَ عَنكُمۡۚ وَخُلِقَ ٱلۡإِنسَٰنُ ضَعِيفٗا ٢٨}[النساء: ٢٨]

‹‹አላህ ከናንተ ሊያቃልልላችሁ ይሻል፡፡ ሰውም ደካማ ኾኖ ተፈጠረ፡፡››[አልኒሳእ፡28]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፡-

{لَا يُكَلِّفُ ٱللَّهُ نَفۡسًا إِلَّا وُسۡعَهَا}[البقرة: ٢٨٦]

‹‹አላህ ነፍስን ከችሎታዋ በላይ አያስገድድም፤››[አልበቀራህ፡185]

ከዓእሻ (ረ.ዐ.) በተላለፈው መሰረት ፦ ‹‹ነቢዩ ﷺ ሁለት አማራጮች ሲቀርብላቸው ኃጢአት እስከሌለበት ድረስ ቀለል ያለውን እንጅ አይመርጡም ነበር፤ኃጢአት ካለበት ግን ከማንም በላይ ከርሱ ይርቁ ነበር:: በአላህ እምላለሁ፣የአላህ ሕግ ተጥሶ የሚበቀሉ እስካልሆነ ድረስ በምንም ነገር ራሳቸውን በተመለከተ ማንንም ሰው ተበቅለው አያውቁም::›› [በቡኻሪ የተዘገበ]

ከእስላማዊ ሕግ ችግር ማስወገጃና ገርነት ገጽታዎች አንዱ ድካምና አታካችነት ሳይኖርበት አማኙ ግዴታዎቹን በቀላሉ ይወጣ ዘንድ ግዴታዎቹ ገርና ቀላል መሆናቸው አንዱ ነው:: አድካሚነትና አስጨናቂነት አለመኖሩን ሲገልጽ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَمَا جَعَلَ عَلَيۡكُمۡ فِي ٱلدِّينِ مِنۡ حَرَجٖ} [الحج: ٧٨]

‹‹በናንተም ላይ በሃይማኖቱ ውስጥ ምንም ችግር አላደረገባችሁም፤››[አልሐጅ፡78]

የታዘዙ ግዴታዎች ዓላማቸው በዚህች ሕይወትና በወዲያኛው ዓለም ሕይወት ሰውን ወደ መታደልና ወደ ደስተኝነት ሕይወት ማድረስ እንደመሆኑ፣ ሕግጋቱ የመጡት የሰው ልጅ ተፈጥሮ ሊሸከመውና በቀላሉ ሊወጣው በሚችለው ተገቢ



## ጽኑ መሰረት ያለው እምነት

‹‹በአምስቱ የእስላም ማእዘኖች ውስጥ ሙስሊም ያልሆነን ሰው የሚያስበረግግ አንድም ነገር የለም:: ከነዚህ ግዴታዎች ቅለትና ከቁጥራቸው ማነስ ጋር የእስላምን እምነት በያንዳንዱ ሙስሊም ውስጥ ለማጽናት የሚያስችል አንዳች ማሻያ ማድረግ አስፈላጊ አልነበረም:: የእስላማዊ ዐቂዳ ተግባራዊ እሴት ከጥንካሬው፣ከጽናቱና ከስርጭቱ የሚመነጭ የራሱ ውስጣዊ ማስረጃ አለው::››

**ጆርጅ ሳርቶን**

**በዋሽንግተንና በሃርቫርድ ዩኒቨርሲቲዎች ሌክቸረር**



## ቅድሚያ ለሃይማኖት

‹‹የሙስሊሞች ስነምግባራዊ መርሆዎች፣ ሕጋቸው፣መንግስታቸው፣ሁሉም በሃይማኖት መሰረት ላይ የቆሙ ነበሩ:: እስላም ከሃይማኖቶች ሁሉ እጅግ ቀላሉና ግልጹ ሃይማኖት ነው:: መሰረቱም ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ አለመኖሩንና ሙሐመድ የአላህ መልክተኛ መሆናቸውን መመስከር ነው::››

**ዎል ዲዮራንት**

**አሜሪካዊ ደራሲ**



ተመጣጣኝ ሁኔታ ብቻ ነው:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{يَـٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ لَا تَسۡـَٔلُواْ عَنۡ أَشۡيَآءَ إِن تُبۡدَ لَكُمۡ تَسُؤۡكُمۡ وَإِن تَسۡـَٔلُواْ عَنۡهَا حِينَ يُنَزَّلُ ٱلۡقُرۡءَانُ تُبۡدَ لَكُمۡ عَفَا ٱللَّهُ عَنۡهَاۗ وَٱللَّهُ غَفُورٌ حَلِيمٞ ١٠١ قَدۡ سَأَلَهَا قَوۡمٞ مِّن قَبۡلِكُمۡ ثُمَّ أَصۡبَحُواْ بِهَا كَٰفِرِينَ ١٠٢} [المائدة: ١٠١-١٠٢]

‹‹እላንተ ያመናችሁ ሆይ! ለናንተ ቢገለጹ ከሚያስከፏችሁ ነገሮች አትጠይቁ፤ቁርኣንም በሚወርድበት ጊዜ ከርሷ ብትጠይቁ፣ለናንተ ትገለጻለች፤ከርሷ (ካለፈው ጥያቄያችሁ) አላህ ይቅርታ አደረገ፤አላህም መሓሪ ታጋሽ ነው:: ከናንተም በፊት ሕዝቦች በእርግጥ ጠየቋት፤ከዚያም በርሷ (ምክንያት) ከሓዲዎች ኾኑ::››[አልማእዳህ፡101-102]

### ሁለተኛ - የሰው ልጆችን ጥቅሞች ግንዛቤ ውስጥ ማስገባቱ፦

የእስላምን ሸሪዓዊ ድንጋጌዎች ተከታትሎ ያስተዋለ ሰው፣ዓላማቸው የሰው ልጆችን ጥቅምና ቅን ፍላጎቶች በግልም ሆነ በጋራ በሁሉም ዘመንና ስፍራ እውን የሚያደርግ፣በዚህ ዓለምና በወዲያው ዓለም ሕይወቱ መጥፎና እኩይ የሆነውን ሁሉ የሚያስወግድ መሆኑን ይገነዘባል:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَمَآ أَرۡسَلۡنَٰكَ إِلَّا رَحۡمَةٗ لِّلۡعَٰلَمِينَ ١٠٧} [الأنبياء: ١٠٧]

https://www.path-2-happiness.com/am

‹‹(ሙሐመድ ሆይ!) ለዓለማትም እዝነት አድርገን እንጅ አልላክንህም፡፡››[አል አንቢ.ያ፡107]

የነቢዩ ሙሐመድ ﷺ መላክ የሰው ልጆችን ጥቅሞች እውን ለማድረግ የታቀደ እዝነትና ጸጋ ሲሆን፣ይህ ባይኖር ኖሮ ነቢዩ ﷺ በእዝነትና በርህሩህነት ባልተገለጹ ነበር፡፡ ከአላህ የታዘዙ ግዴታዎች ሁሉ መነሻና መድረሻቸው የሰው ልጆች መንፈሳዊና ቁሳዊ ጥቅሞች ናቸው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) ከባሮቹ ምንም የማይፈልግ በራሱ የተብቃቃ ጌታ ነውና የሰዎች በጎ ሥራ አይጠቅመውም፤ክፉ ሥራቸውም አይጎዳውም፡፡ የሸሪዓ ሕጉም በጥቅሉ ፍትሕ ነው፤በጥቅሉ እዝነትና ርህራሄ ነው፤በጥቅሉ ጠቀሜታ ነው፤በጥቅሉ ጥበብ ነው፡፡ ከፍትሕ ወደ ግፍ፣ከእዝነት ወደ ጭካኔ፣ከጥቅም ወደ ጉዳት፣ከጥበብ ወደ ከንቱነት የወጣ ነገር ሁሉ የሸሪዓው አካል አይደለም፡፡



## ሦስተኛ - በሁሉም መልኩ ፍትሕን እውን ማድረግ፡-

ፍትሕን እውን ማድረግና ማጽናትን መሰረታዊ አጠቃላይ መርሕ የሚያደርጉ ቁርኣናዊ አንቀጾች በርካታ ናቸው፡፡ አንዳንዶቹ ለፍርድ ማስተካከልና ለፍትሕ ማስፈን ጥሪ የሚያደርጉ ሲሆኑ፣ሌሎቹ ደግሞ በተቃራኒ ወገን ላይ እንኳ ቢሆን ግፍና በደልን መፈጸም የሚያጥላሉና የሚያወግዙ ናቸው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፡-

{يَـٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ كُونُوا۟ قَوَّٰمِينَ لِلَّهِ شُهَدَآءَ بِٱلْقِسْطِ ۖ وَلَا يَجْرِمَنَّكُمْ شَنَـَٔانُ قَوْمٍ عَلَىٰٓ أَلَّا تَعْدِلُوا۟ ۚ ٱعْدِلُوا۟ هُوَ أَقْرَبُ لِلتَّقْوَىٰ ۖ وَٱتَّقُوا۟ ٱللَّهَ ۚ إِنَّ ٱللَّهَ خَبِيرٌۢ بِمَا تَعْمَلُونَ ﴿٨﴾}[المائدة: ٨]

‹‹እላንተ ያመናችሁ ሆይ! ለአላህ ቀጥተኞች፣በትክክል መስካሪዎች ኹኑ፤ሕዝቦችንም መጥላት፣ባለማስተካከል ላይ አይገፋፋችሁ፤አስተካክሉ፤(ማስተካከል) ለአላህ ፍራቻ የቀረበ ነው፡፡ አላህንም ፍሩ፡፡ አላህ በምትሠሩት ሁሉ ውስጠ ዐዋቂ ነው፡፡››[አልማእዳህ፡8]

## አራተኛ - አጠቃላይነትና አንዱ ሌላውን የሚያሟላ መሆኑ፡-

የአንድን ሃይማኖትና መልክት ትክክለኛነት ከሚያመለክቱ አበይተ ነገሮች አንዱ የተለየ የአጠቃላይነትና አንዱ ሌላውን የሚያሟላበት ልዩ መለያ ያለው መሆኑ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፡-

{مَّا فَرَّطْنَا فِى ٱلْكِتَـٰبِ مِن شَىْءٍ}[الأنعام: ٣٨]

‹‹በመጽሐፉ ውስጥ ምንም ነገር [ሳንገልጽ] አልተውንም፡፡››[አል አንዓም፡38]

በተጨማሪም እንዲህ ብሏል፡-

{وَنَزَّلْنَا عَلَيْكَ ٱلْكِتَـٰبَ تِبْيَـٰنًا لِّكُلِّ شَىْءٍ وَهُدًى وَرَحْمَةً وَبُشْرَىٰ لِلْمُسْلِمِينَ ﴿٨٩﴾}[النحل: ٨٩]

‹‹መጽሐፉንም፣ለሁሉ ነገር አብራሪ፣መሪም እዝነትም፣ለሙስሊሞችም አብሳሪ ኾኖ ባንተ ላይ አወረድነው፡፡››[አል ነሕል፡89]

ይህ አጠቃላይነት በዐቂዳው (በእምነት)፣በአመለካከት፣በዕባዳ (አምልኮተ አላህ) እና በጽድቅ ሥራ፣በስነምግባርና በሰናይ ተግባራት፣በሕግ አወጣጥ፣በቅንብርና በአገዛዝ ሥርዓት፣በሁሉም የሕይወት ፈርጆች ውስጥ የሚንጸባረቅ ነው፡፡

## አምስተኛ - ተመጣጣኝነት ሚዘናዊነትና መካከለኛነት፡-

የእስላም ሃይማኖት የተመጣጣኝነት የሚዛናዊነትና የመካከለኛነት ሃይማኖት ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፡-

{وَكَذَٰلِكَ جَعَلْنَـٰكُمْ أُمَّةً وَسَطًا}[البقرة: ١٤٣]

‹‹እንደዚሁም (እንደ መራናችሁ) . . ምርጥና ሚዘናዊ ሕዝቦች (ኡመት) አደረግናችሁ፤››[አል በቀራህ፡143]

በሕግጋቱና በሥርዓቱ ውስጥ ያለው ማንኛውም ነገር በተራቀቀ ሚዘናዊነት የተዘጋጀ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፡-

{وَٱلسَّمَآءَ رَفَعَهَا وَوَضَعَ ٱلْمِيزَانَ ﴿٧﴾} [الرحمن: ٧]

**እስላም . . ሰላምና አማን ነው**

‹‹አይሁዶች በእስላም ሰንደቅ ስር ከጭቆና እና ከጥቃት ተጠብቀው ፍትሕን አግኝተዋል፡፡ ለበርካታ ምእተ ዓመታትም በመልካም አያያዝ የብልጽግና ኑሮ መርተዋል፡፡››

**ነሲም ሱሳ**

**ዕራቃዊ ይሁዲ ሌክቸረር**





https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am



‹‹ሰማይንም አጓናት፤ትክክለኛነትንም [ፍትሐዊነትንም] ደነገገ፡፡››[አልረሕማን፡7]

አላህ (ሱ.ወ.) ሙስሊሞችን በሁሉም ነገር ሚዘናዊ እንዲሆኑ ያዘዘ ሲሆን ከዚህ ውስጥ የሚከተለውን የአላህ (ሱ.ወ.) ቃል እናገኛለን፦

{وَٱلَّذِينَ إِذَآ أَنفَقُواْ لَمۡ يُسۡرِفُواْ وَلَمۡ يَقۡتُرُواْ وَكَانَ بَيۡنَ ذَٰلِكَ قَوَامًا ٦٧} [الفرقان: ٦٧]

‹‹እነዚያም፣በለገሱ ጊዜ የማያባክኑት፣የማይቆጥቡትም ናቸው፤በዚህም መካከል (ልግስናቸው) ትክክለኛ [ሚዛናዊ] የኾነ ነው፡፡››[አልፉርቃን፡67]

ነቢዩም ﷺ ማክረርንና ጫፍ ረጋጭነትን ሲከለክሉ እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹በሃይማኖት ጉዳይ ከልክ አልፎ ከማክረር ራቁ፣ከናንተ በፊት የነበሩትን ያጠፋው ከልክ ያለፈ አክራሪነት ነውና፡፡›› ለተመጣጣኝነትና ለሚዘናዊነት ሲያዙም ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹ለጌታህ መፈጸም ያለበት ግዴታ አለብህ፤ለገዛ ራስህም መፈጸም ያለበት ግዴታ አለብህ፤ለባለቤትህም መፈጸም ያለበት ግዴታ አለብህ፤እናም ለሁሉም ተገቢና ተመጣጣኝ መብቱን ስጥ፡፡››

## የእስላማዊ ድንጋጌ መለያ ባሕርያት

### አንደኛ - የምንጩ መለኮታዊነት፦

የእስላማዊው ሃይማኖት ምንጭ ሰዎችንና ፍጥረተ ዓለሙን በመላ የፈጠረው ኃያል ፈጣሪ አምላክ ነው። የመሰረቱና የምንጩ መለኮታዊ መሆን ብዙ መለያ ባሕርያትን የሚያሰጠው ሲሆን፣ከነዚህ መካከል አላህ (ሱ.ወ.) ፈጣሪና መጋቢ አምላክ መሆኑ፣ሕግ የመስጠትና የመደንገግ መብት የርሱ ብቻ መሆኑ ይገኙበታል። ነቢያትና መልክተኞች ተከታዮቻቸውም ሕግ ማውጣትንና መደንገግን ለአላህ (ሱ.ወ.) ብቻ የተሰጠ መብት ያደርጉ የነበረ ሲሆን ከርሱ ውጭ ያለውን ሁሉ ውድቅ ያደርጉ ነበር። ሸሪዓውን አስመልክቶ የነቢዮቹና የመልክተኞቹ መደምደሚያ ያሉትን ሲያወሳ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{قُلۡ مَا كُنتُ بِدۡعًا مِّنَ ٱلرُّسُلِ وَمَآ أَدۡرِي مَا يُفۡعَلُ بِي وَلَا بِكُمۡۖ إِنۡ أَتَّبِعُ إِلَّا مَا يُوحَىٰٓ إِلَيَّ وَمَآ أَنَا۠ إِلَّا نَذِيرٞ مُّبِينٞ ٩} [الأحقاف: ٩]

‹‹ከመልክተኞች ብጤ የሌለኝ አይደለሁም፤በኔም በናንተም ምን እንደሚሠራም አላውቅም፤ወደኔ የሚወረደውን እንጅ ሌላን አልከተልም፤እኔም ግልጽ አስፈራሪ [አስጠንቃቂ] እንጅ ሌላ አይደለሁም በላቸው፡፡››[አልአሕቃፍ፡9]

የአላህ መልክተኛ - አላህ ዘንድ ካላቸው ደረጃና የላቀ ከበሬታ ጋር - ወደርሳቸው የተላለፈው የአላህ (ሱ.ወ.) ሸሪዓ ተከታይ፣ለርሱ መርሕ ተመሪ እንጂ ከራሳቸው አዲስ የፈጠሩትን የሚከተሉ አይደሉም። አላህ (ሱ.ወ.) ፈጣሪ አምላክ በመሆኑ ለፍጥረታቱ የሚበጀውን ከርሱ ይበልጥ የሚያውቅ ማንም የለም። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{أَلَا يَعۡلَمُ مَنۡ خَلَقَ وَهُوَ ٱللَّطِيفُ ٱلۡخَبِيرُ ١٤}[الملك: ١٤]


‹‹የፈጠረ አምላክ እርሱ ዕውቀተ ረቂቁ፣ውስጥ አዋቂው ሲኾን (ምስጢርን ሁሉ) አያውቅምን፡፡››[አል ሙልክ፡14]

ስለ ፍጡራኑ ባሕርይና ስለፍጥረታቸው፣ስለሚጠቅማቸውና ስለሚጎዳቸው፣ስለሚበጃቸውና ስለማይበጃቸው ነገር ከማንም በላይ የሚያውቅ እርሱ ብቻ ነው። ከሠሪው ይበልጥ ስለሠራው ነገር የሚያውቅ ማንም አይኖርምና። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{قُلۡ ءَأَنتُمۡ أَعۡلَمُ أَمِ ٱللَّهُ}[البقرة: ١٤٠]

‹‹እናንተ ታውቃላችሁን? ወይንስ አላህ? በላቸው፤፡፡››[አልበቀራህ፡140]

ሕግ አውጭና ሰጭው አላህ (ሱ.ወ.) ለሕጉ ፍጹማዊ የሆነ ፍትሕና እውነትን ያጎናጽፋል። አላህ (ሱ.ወ.) ሰብአዊ ፍጡራኑን በአድልኦ ከማየት የራቀ ፍትሐዊ ፈጣሪ ጌታ ነውና። የእስላም መቀጫዎችም በዛሬው ዓለማዊ ሕይወትና በመችጭው ዘላለማዊ ሕይወት የሚፈጸሙ ሲሆኑ፣በአንዱ ወይም በሌላው ምክንያት በዚህ ዓለም ላይ መብቱ ያልተከበረለትና ፍትሕ ያላገኘ



### የመረጋጋት ሃይማኖት

‹‹በሕይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ ውስጣዊ ሰላምና መረጋጋት ተሰማኝ። ሕይወቴ ዋጋ እንዳለውም ተረዳሁ። አንተ የማታየው አላህ የትም ብትሆን ያየሃል፣ሥራዎችህን ሁሉ ይቆጣጠራል፣በትንሳኤው ቀን ተገቢ ዋጋህን ታገኝ ዘንድ ፍትሐዊ በሆነ ሚዛንም ይመዝናቸዋል ማለት ትርጉሙ ምን እንደሆነም ዐወቅሁ፡፡››

አናቶሊ አንደርቡሽ
ሩሲያዊ ጄኔራል

https://www.path-2-happiness.com/am



ሰው ወይም በእኩይ ተግባሩ ዛሬ ያልተቀጣ ሰው፣ብድራቱን በወዲያኛው ዘላለማዊ ሕይወት ያገኛል::

### ሁለተኛ - ሕግጋትን ከስነምግባር ጋር ማስተሳሰሩ፦

ሕግ በመታወጁ ብቻ ዓላማው እውን እንደማሆንና ይህን ለማድረግ የሰዎች አምነውበት መቀበልና ለተግባራዊነቱ መተባበር አስፈላጊ መሆኑ የታመነ ነው:: ሕግ እውን እንዲያደርግ የሚጠበቀው ዓላማና ግብ በአቀራረጹና በድንጋጌዎቹ ጥሩነት ብቻ የሚወሰን ሳይሆን ሕጉ የተደነገገላቸው ሰዎች ከውስጣቸው በመጣ ልባዊ ግፊት ሲተገብሩት ጭምር ነው:: ይህ ውስጣዊ ግፊት የሚመጣው ለሕጉ ፍትሐዊነት ካላቸው እምነት፣ወደው ከመቀበላቸውና ሕጉን ከደነገገው ወገን ድንጋጌዎቹንና ውሳኔዎቹን ወደው በመተግበራቸው ሽልማት እንዳላቸው ከማመናቸው የተነሳ ነው:: የእስላም ሕግጋት የተመሰረቱት በፍላጎትና በእምነት ወዶ በመቀበል ላይ ሲሆን አላህ (ሱ.ወ.) በእስላም ትምሕርትቶች ውስጥ ሙስሊሞች ይህንን እንዲያደርጉ አዟል፦

{وَقُل لَّهُمۡ فِيٓ أَنفُسِهِمۡ قَوۡلَۢا بَلِيغٗا ﴿٦٣﴾}[النساء: ٦٣]

‹‹በነፍሶቻቸው ውስጥ ስሜት ያለው [የሚያጭር] ቃል ተናገራቸው::››[አልኒሳእ:63]

{فَذَكِّرۡ إِنَّمَآ أَنتَ مُذَكِّرٞ ﴿٢١﴾ لَّسۡتَ عَلَيۡهِم بِمُصَيۡطِرٍ ﴿٢٢﴾} [الغاشية: ٢١- ٢٢]

‹‹[ለሌሎች] አስታውስም፤አንተ አስታዋሽ ብቻ ነህና:: በነሱ ላይ ተሿሚ (አስገዳጅ) አይደለህም፤››[አልጋሽያህ:21-22]

ለዚህም ነው የነቢዩ ሙሐመድን ﷺ ተልእኮ አላህ (ሱ.ወ.) በዚህ ክልል ውስጥ የወሰነው:: ነቢዩ ﷺ ፦ ‹‹የተላክሁት መልካም ስነምግባራትን ምሉእ ለማድረግ ነው::›› ብለዋል::

### ሦስተኛ - የሰው ልጆችን ጥቅሞች ግንዛቤ ውስጥ ማስገባቱ፦

እስላማዊ ሕግን ከተቀሩት ሰው ሰራሽ ምድራዊ ሕጎች የተለየ የሚያደርገው፣በዚህች ዓለማዊ ሕይወትና በወዲያኛው ዘላለማዊ ሕይወትም የሚያሸልምና የሚያስቀጣ መሆኑ ነው:: የወዲያኛው ዓለም ምንዳም ሆነ ቅጣት ሁሌም ከዛሬዋ ሕይወት ምንዳና ቅጣት በእጅጉ የላቀ ነው:: በመሆኑም አንድ አማኝ ሰው ሁሌ የአላህን ሕግጋት የመተግበር፣ያዘዘውን የመፈፈጸምና ከከለከለው የመታቀብን አስፈላጊነት የሚያስገነዝብ ብርቱ ውስጣዊ ግፊትና ስሜት ይሰማዋል:: በዚህ ዓለም ላይ ለፈጸመው ነገር ከቅጣት ማምለጥ ቢችል እንኳ አላህ (ሱ.ወ.) የሚያየውና የሚቆጣጠረው መሆኑን፣ሰዎች በዚህ ዓለም የሕይወት ዘመናቸው ለፈጸሙት ሁሉ አላህ (ሱ.ወ.) ፊት ነገ ተጠያቂዎች መሆናቸውን በእርግጠኝነት ያውቃል:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{أَيَحۡسَبُ أَن لَّن يَقۡدِرَ عَلَيۡهِ أَحَدٞ ﴿٥﴾}[البلد: ٥]

‹‹በርሱ ላይ አንድም የማይችል መኾኑን ይጠረጥራልን?››[አልበለድ:5]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{أَيَحۡسَبُ أَن لَّمۡ يَرَهُۥٓ أَحَدٌ ﴿٧﴾} [البلد: ٧]

‹‹አንድም ያላየው መኾኑን ያስባልን?››[አልበለድ:7]

### አራተኛ - የሕግጋቱ ማሕበራዊ ገጽታ፦

እስላማዊው ሕግ የአንዱን ጥቅም ከሌላው ጥቅም አያበላልጥም፤በሌላው ሰው ሒሳብ ለማንም አይወግንም:: እስላምን የሕይወት መመሪያና የአነዋነዋር ሥርዓት አድርገው ያልያዙ ብዙ ሕብረተሰቦችን ወጥሮ ከያዘውና በግለሰብ ጥቅምና በሕብረተሰብ የጋራ ጥቅም መካከል ያለውን ቅራኔ እስላም ፈቶታል:: አንዳንድ ማሕበረሰቦች ግን በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ እንደሚስተዋለው ለግለሰባዊ ጥቅሞች ብልጫ በመስጠት የሚወግኑ ሲሆን፣የሶሽደሊስቱ ሥርዓት ደግሞ ሚዛኑን ወደ ሕብረተሰባዊ ጥቅም በማጋደል የግለሰብን መብት ይደፍቃል:: ከሰው ልጅ ተፈጥሮ በተጻራሪ ግላዊ ነጻነትንና ሀብት የማፍራት መብትን ነፍጎ ግለሰባዊ ማንነትንና ተሰጥኦን በማኮስመን፣ብቃትና ክህሎቱን ብኩን ያደርጋል:: እስላማዊው ሕግ ግን በሚመሰርተው ሕብረተሰብ ውስጥ ሥርዓቱን የሚያንጸው ሚዘናዊ በሆነ ሁኔታ እነዚህን መብቶች በሚያስተናግድ መሰረት ላይ ነው:: ለሙስሊሙ ሕብረተሰብ የጋራ ማሕበራዊ ጥቅሞች ትኩረት የሚሰጥ ቢሆንም የሙስሊም ግለሰብን መብትና ፍላጎቶችም ችላ አይልም:: በፖለቲካው መስክ የአገር መሪ መብት ዜጎች ለሕግና ሥርዓቱ እንዲታዘዙ ማድረግ ሲሆን የዜጎች የመታዘዝ ግዴታ ግን መሪው በአመራሩ የሕግ የበላይነትን የሚያሰፍን፣ለጋራ ጥቅሞች ትኩረት የሚሰጥ በመሆን ግዴታ የተገደበ ነው:: ይህን የማያሟላ ከሆነ ግን እስላም ይህን መብት ይነጥቀዋል:: መሪውን የመታዘዝ ግዴታ የሚጸናውም የአላህን ትእዛዝ መጣስ በሌለበባቸው ነገሮች ላይ ብቻ ይሆናል::

### አምስተኛ - በመርሕ ላይ መጽናትና የትግበራ ገርነት፦

እስላም ከመጀመሪያ ምንጩና መሰረቱ ከሆነው፣የአላህ (ሱ.ወ.) ጥበቃ ከሚደረግለት ቁርኣን በመነጩ የማይለወጡ ጽኑና ቋሚ መደላድሎች ላይ ይቆማል:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{إِنَّا نَحۡنُ نَزَّلۡنَا ٱلذِّكۡرَ وَإِنَّا لَهُۥ لَحَٰفِظُونَ ﴿٩﴾} [الحجر: ٩]

https://www.path-2-happiness.com/am

‹‹እኛ ቁርኣንን እኛው አወረድነው፤እኛም ለርሱ ጠባቂዎቹ ነን፡፡››[አል ሕጅር፡ 9]

ከኋላውም ሆነ ከፊቱ ውሸት በማይመጣበት ሕያው መጽሐፍ ላይ ይሞረኮዛል፦

{لَّا يَأۡتِيهِ ٱلۡبَٰطِلُ مِنۢ بَيۡنِ يَدَيۡهِ وَلَا مِنۡ خَلۡفِهِۦۖ تَنزِيلٞ مِّنۡ حَكِيمٍ حَمِيدٖ ۝٤٢} [فصلت: ٤٢]

‹‹ከኋላውም ከፊቱም ውሸት አይመጣበትም፤ጥበበኛ ምስጉኑ ከኾነው ጌታ የተወረደ [የተላለፈ] ነው፡፡››[ሓ.ሚም አልሰጅዳህ፡42]

ወደር በማይገኝለት ከፍተኛ ጥንቃቄና በተራቀቀ ስልት የተጠናቀረው የነቢያዊው ሱንና (ፈለግ) ብዙዎቹ ዘገባዎችም ለሕግ አወጣጥ መሰረት የሆኑ አጠቃላይ ድንጋጌዎችን ያካተቱ ናቸው፡፡ እንደ ጊዜና ሁኔታዎች መለዋወጥ ተመጣጣኝ የሆኑ ዝርዝር የአፈጻጸም ደንቦችና መመሪያዎችን ከአጠቃላይ ሕግጋቱ ለሚያመነጩ የሃይማኖቱ ሊቃውንት ሰፊ ክፍተት በመለቀቁ ለትግበራ ምቹና ገር የመሆን ዕድላቸው ከፍተኛ ነው፡፡ ዝርዝር የአፈጻጸም ጉዳዮቹ ከመሰረታዊ ሕግጋት አንቀጾች ጋር እስካልተጋጩ ድረስ የእስላማዊውን ሸሪዓን አጠቃላይ ግብና ዓላማዎች (አልመቃስድ) እውን ለማድረግ የሚመነጩ የትግበራና የአፈጻጸም ደንቦች በከፍተኛ ደረጃ የመለወጥ የማደግና የልስላሴ ባሕርያትን የተላበሱ ናቸው፡፡ በመሆኑም ፊት ያልነበሩና አዳዲስ ለተፈጠሩ ተጨባጭ ሁኔታዎች መፍትሔ የሚሰጡ አዳዲስ ዝርዝር ሕጎችን በዚህ መሰረት ላይ በመሞርከዝ ማመንጨትን የሚከለክል ነገር የለም፡፡



### የከበሬታ ሃይማኖት

‹‹እስላም የሰላም፣የእኩልነት፣የነጻነት፣የወንድማማችነት፣የክብርና የልዕልና ሃይማኖት ነው፡፡ ይህ ሁሉ በሕግጋቱ፣በመርሆዎቹና በስነምግባሮቹ ውስጥ በግልጽ ይታያል፡፡ እስላም ውስጥ ያለው ጾም በሌሎች ሃይማኖቶች ውስጥ ካለው ጾም የተለየ ነው፡፡ የሰው ልጆች ችግር መነኩሳት እንደሚያደርጉትና አንዳቸው ተንቀሳቃሽ የአጥንት መዋቅር እስከሚመስል ድረስ የአካል ፍላጎትን ማፈን አይደለም፡፡ በመሆኑም እስላም ሥጋዊ ፍላጎቶችን በመግራት ይቆጣጠራቸዋል እንጂ አያፍናቸውም፡፡ በእስላም ዘንድ ያለው የጾም ዓለማም የተከለከሉና ሐራም የሆኑ ሥጋዊ ፍላጎቶችን መርታት ትችል ዘንድ ነፍሲያን መታገል፣ቁጡብ መሆንንና በመታገስ ራስን መግዛት መለማመድና ራስን ማሰልጠን ነው፡፡ በግልጽና በስውርም አላህ እንደሚያን አውቀን መጠንቀቅ፣ላጡትና ለተራቡት እናዝን ዘንድ የማጣትና የመራብን ስሜት መረዳት መቻል ነው፡፡ በተጨማሪም ጾም ሰውነት ከምግብ አለመፈጨት ችግር ዕረፍት እንዲያገኝ ለማድረግ መልካም አጋጣሚ ነው፡፡ ጾም ለግለሰብ ጤንነት ለመንፈሱና ለአእምሮው ጠቀሜታ ያለው ሲሆን፣ለሕብረተሰብ ደግሞ ለመቀራረብ፣ለተራድኦና ለአንድነት ፋይዳው የጎላ ነው፡፡››

ቢሪሻ በንክመርት

ቡድሂዝምን ትቶ እስላምን የተቀበለ
ታይላንዳዊ የስነትምሕርት ባለሞያ





## እስላማዊው ሸሪዓና ሰው ሠራሽ ሕግጋት . . ልዩነቶችና ተቃርኖዎች

በእስላማዊው ሸሪዓና በሰው ሠራሽ ሕጎች መካከል ከተለያዩ ሁኔታዎች አንጻር ከፍተኛ ልዩነቶች ይገኛሉ፤ከነዚህም መካከል የሚከተሉትን እናገኛለን፦

### ግርማ ሞገስ ቅድስና እና በሰው ዘንድ ያለው ከበሬታ፦

በሃይማኖታዊ ባሕርይው፣በሃይማኖታዊ ይዘቱና ከአላህ (ሱ.ወ.) የተላለፈ መለኮታዊ ከመሆኑ አንጻር፣የእስላም ሸሪዓ ልዩ በሆነ ግርማ ሞገስ፣በቅድስና እና በሰው ልቦና ውስጥ ባለው ከበሬታ ከሰው ሠራሽ ሕጎች ይለያል፡፡

### ሸሪዓው ከሰው ልጅ ተፈጥሮ ጋር የተጣጣመ፣ለሁሉም ዘመንና ስፍራ ምቹ መሆኑ ፦

ሕጉን የደነገገው የሆነውንና ወደፊት የሚሆነውን ሁሉ የሚያውቀው፣ስለፈጠራቸው ፍጥረታት ባሕርያት፣ተፈጥሮና ፍላጎቶቻቸው፣እነሱን የሚመለከተውን ማንኛውንም ነገር ከማንም በላይ የሚያውቅ፣ከአድልኦና ከማናንኛውም ዓይነት ዝንባሌ የጠራው የፍጥረታት ፈጣሪ አምላክ አላህ (ሱ.ወ.) ያስረተላለፈው መለኮታዊ ሕግ በመሆኑ፣ እስላማዊው ሸሪዓ በየትኛውም ስፍራና በየትኛውም ዘመን ለሚኖሩ ሁሉም ሕዝቦች ልዩ ሁኔታዎች፣የተለያዩ ስነምረህዳሮች፣ቋንቋዎች፣ብሔሮች፣ባህሎች . . ምቹ የሆነ የሕግ ሥርዓት ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{فَأَقِمۡ وَجۡهَكَ لِلدِّينِ حَنِيفٗاۚ فِطۡرَتَ ٱللَّهِ ٱلَّتِي فَطَرَ ٱلنَّاسَ عَلَيۡهَاۚ لَا تَبۡدِيلَ لِخَلۡقِ ٱللَّهِۚ ذَٰلِكَ ٱلدِّينُ ٱلۡقَيِّمُ وَلَٰكِنَّ أَكۡثَرَ ٱلنَّاسِ لَا يَعۡلَمُونَ ۝٣٠} [الروم: ٣٠]

‹‹ወደ እውነት ተዘንባይ ኾነህ ፊትህን ለሃይማኖት ቀጥ አድርግ፤የአላህን ፍጥረት ያችን አላህ ሰዎችን በርስዋ ላይ የፈጠረባትን (ሃይማኖት ያዙዋት)፤የአላህን ፍጥረት መለወጥ የለም፤ይህ ቀጥተኛ ሃይማኖት ነው፤ግን አብዛኞዎቹ ሰዎች አያውቁም፡፡››[አል ሩም፡30]

ሰው ሠራሽ ዓለማዊ ሕጎች ግን በሰዎች የተደነገጉ ናቸው፡፡ ሰዎች ደግሞ

https://www.path-2-happiness.com/am

ትናንትና ዛሬ ያሻቸውን ያህል በዕውቀት ቢራቀቁም፣ነገ የሚከሰተውን አያውቁም። ከፊሉን የሰው ልጅ ሕርያት ቢያውቁ ሁሉን ማወቅ አይችሉም። ከዚህ ስንነሳም የሚያወጧቸው ሕጎች ከሁሉም የሰው ልጅ ተፈጥሮዎችም ሆነ ከሁሉም የአካባቢ ሁኔታዎች ጋር የሚጣጣሙ አይሆኑም። ለአንዱ ሕዝብ የሚስማሙ ቢሆን ለሌላው ሕዝብ የሚበጁ አይሆኑም።

## እስላማዊው ሸሪዓ ከእውነታ ከሐቅና ከፍትሕ ጋር የተጣጣመ መሆኑ፦

እስላማዊው ሸሪዓ ከእውነታ ከሐቅና ከፍትሕ ጋር ሙሉ በሙሉ የተጣጣመ የሕግ ሥርዓት ነው። ይኸውም ከአላህ (ሱ.ወ.) የተላለፈ በመሆኑ በሕግ አወጣጡ ውስጥ የመሳሳት፣የግድፈትና እርስበርስ የመጻረር ችግር ፈጽሞ የሌለበት በመሆኑ፣ከበደል፣ከግፍ፣ከጭቆና፣ለስሜትና ለዝንባሌዎች ተገዥ ከመሆን ፈጽሞ የጠራ በመሆኑ ነው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَتَمَّتْ كَلِمَتُ رَبِّكَ صِدْقًا وَعَدْلًا ۚ لَّا مُبَدِّلَ لِكَلِمَٰتِهِۦ ۚ وَهُوَ ٱلسَّمِيعُ ٱلْعَلِيمُ ﴿١١٥﴾}[الأنعام: ١١٥]

‹‹የጌታህም ቃላት እውነተኛና ትክክለኛ ስትኾን፣ተፈጸመች፤ለቃላቱ ለዋጭ የለም፤እርሱም ሰሚው፣ዐዋቂው ነው።››[አልአንዓም:115]

ከፍላጎቶች የጠራውና የተብቃቃው አላህ (ሱ.ወ.) ብቻ ነው፤የነገሮችን ሁሉ ውስጣዊና ውጫዊ ሁኔታዎች ግልጹንና ስውሩንም በፍጹምነት የሚያውቅ እርሱ ብቻ ነው። ዕውቀቱ ሁሉንም ያካበበ ፍጹማዊ ዕውቀት ያለው አምላክ በመሆኑም ለፍጡራኑ የሚበጃቸውን እንጂ አያዛቸውም፤ከሚጎዳቸው ነገር እንጂ አይከለክላቸውም። ሰው ሠራሽ ሕጎች ግን ለስሕተትና ለግድፈት፣ለመዘንጋትና ለዝንባሌዎች አዝማሚያ የተጋለጡ ናቸው። በመሆኑም ከስህተት፣ከጉድለት፣ከመለውጥና ከመቀያየር ነጻ ሊሆኑ አይችሉም። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَلَوْ كَانَ مِنْ عِندِ غَيْرِ ٱللَّهِ لَوَجَدُوا۟ فِيهِ ٱخْتِلَٰفًا كَثِيرًا ﴿٨٢﴾} [النساء: ٨٢]

‹‹ከአላህ ሌላ ዘንድ በነበረ ኖሮ፣በርሱ ውስጥ ብዙን መለያየት ባገኙ ነበር።››[አልኒሳእ:82]

## እስላማዊው ሸሪዓ ለሰብዓዊ ጎን ትኩረት የሚሰጥ መሆኑ፦

እስላማዊው ሸሪዓ የሰው ልጆች እሳቤ ውጤት የሆነ ተራ ሕግ አይደለም። ኃያሉ ፈጣሪ አላህ (ሱ.ወ.) ለፈጠራቸው ሰዎች ምቹና ተስማሚ አድርጎ የደነገገው ከሰብአዊ ፍጡራን ተፈጥሮ ጋር የተጣጣመ መለኮታዊ ሕግ እንጂ። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{أَلَا يَعْلَمُ مَنْ خَلَقَ وَهُوَ ٱللَّطِيفُ ٱلْخَبِيرُ ﴿١٤﴾}[الملك: ١٤]

‹‹የፈጠረ አምላክ እርሱ ዕውቀተ ረቂቁ፣ውስጥ አዋቂው ሲኾን (ምስጢርን ሁሉ) አያውቅምን?››[አል ሙልክ:14]

ገርና ቀለል የሚሆንላቸውንም ከማንም በላይ የሚያውቀው እርሱ ብቻ ነው፦

{يُرِيدُ ٱللَّهُ أَن يُخَفِّفَ عَنكُمْ ۚ وَخُلِقَ ٱلْإِنسَٰنُ ضَعِيفًا ﴿٢٨﴾} [النساء: ٢٨]

‹‹አላህ ከናንተ ሊያቃልልላችሁ ይሻል። ሰውም ደካማ ኾኖ ተፈጠረ።››[አልኒሳእ:28]

ሰው ሠራሽ ሕጎች ግን የሕግ አውጭዎቹን ፍላጎት መሰረት በማድረግ እንደ ዝንባሌዎቻቸውና እንደ አካባቢያቸው ትኩረት የሚቀረጹ ናቸው።

## እስላማዊው ሸሪዓ ከመንፈሳዊ ጎን ጋር የተሳሰረ መሆኑ፦

እስላማዊው ሸሪዓ ውስጣዊና አፍአዊ፣ቁሳዊና ሕሊናዊ፣ግልጽና ስውሩንም የሚዳስስ ሁሉን አቀፍ ሕግ ነው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَٱعْلَمُوٓا۟ أَنَّ ٱللَّهَ يَعْلَمُ مَا فِىٓ أَنفُسِكُمْ فَٱحْذَرُوهُ ۚ وَٱعْلَمُوٓا۟ أَنَّ ٱللَّهَ غَفُورٌ حَلِيمٌ ﴿٢٣٥﴾}

‹‹አላህም በነፍሶቻችሁ ውስጥ ያለውን የሚያውቅ መኾኑን ዕወቁ፤ተጠንቀቁትም፤አላህም መሓሪ ታጋሽ መኾኑን ዕወቁ።››[አበቀራህ:235]

ሰው ሠራሽ ሕጎች ግን በተጻራሪው በግልጹ ቁሳዊ ጉዳዮች ላይ ብቻ የሚያተኩሩ ሲሆን፣ለመንፈሳዊው ጎን ወይም ለመጭው የወዲያኛው ሕይወት ጉዳዮች ምንም ቁብ አይሰጡም። የሰው ሠራሽ ሕጎች መቀጫዎችም በዚህች ዓለም ብቻ የተወሰነኑ ናቸው።

### የጠራ ደስተኛ ማሕብረሰብ


‹‹የእስላምን ሕግጋትና ስነምግባራቱን የሚያከብርና የሚከተል ማህበረሰብ በሁሉም መልካቸው ወነንጀሎች የማይኖሩበት ንጹሕና ደስተኛ ማሕበረሰብ ነው።

ቢሪሻ በንክመርት

ቡድሂዝምን ትቶ እስላምን የተቀበለ ታይላንዳዊ የስነትምሕርት ባለሞያ



https://www.path-2-happiness.com/am



# የእስላም ምንጮች

የእስላም ሃይማኖት ሕግጋቱን፣ዐቂዳውንና ዝርዝር ሕጎቹን የሚያመነጨው ከመለኮታዊ ወሕይ (መገለጥ) - ከቁርኣንና ከነቢዩ ሱንና - ሲሆን ሁለቱ የእስላም አበይተ መሰረታዊ የሕግ ምንጮች ናቸው:: ከዚህ በመቀጠል ከሁለቱ ምንጮች ጋር አጠር ባለ ሁኔታ እንተዋወቃለን፦

## ሀ - ታላቁ ቁርኣን፦

አላህ (ሱ.ወ.) ቁርኣንን ለጥንቁቆች መመሪያ፣ለሙስሊሞች መተዳደሪያ፣እርሱ መመራት ለሻላቸው ሰዎች ልቦና ፈውስ፣መድህን ለወደደላቸው ሰዎች ችቦና ብርሃን ይሆን ዘንድ ወደ መልክተኛው ወደ ሙሐመድ ﷺ አስተላልፎታል:: ቁርኣን ነቢያትና መልክተኞች ከአላህ (ሱ.ወ.) ተልከው ይዘው የመጡትን መሰረታዊ መርሆዎች ያካተተ መጽሐፍ ነው:: ሙሐመድ ﷺ ብቸኛው የአላህ መልክተኛ እንዳልሆኑ ሁሉ ቁርኣንም ብቸኛው የአላህ መጽሐፍ አይደለም:: አላህ (ሱ.ወ.) ወደ ኢብራሂም ጽሑፎችን አውርዷል፤ሙሳንም በተውራት፣ዳውድን በዘቡር (መዝሙር) አክብሯቸዋል:: አልመሲሕ ዒሳም ኢንጂልን ይዘው መጥተዋል:: እነዚህ መጽሐፎች ሁሉም አላህ (ሱ.ወ.) ወደ ነቢያቱና መልክተኞቹ ያስተላለፋቸው ወሕይ (መለኮታዊ መገለጥ) ናቸው:: ይህ ቁርኣን ከአላህ (ሱ.ወ.) የተላለፈ ወሕይ መሆኑን ከሚመሰክሩ ነገሮች ውስጥ አንዱ፣በሁሉም የአላህ መልክተኞችና ነቢያት ያለ ምንም ልዩነት ማመንን የሃይማኖቱ አንድ አቢይ ማእዘን አድርጎ ያረጋገጠ መሆኑ ነው:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{إِنَّ ٱلَّذِيـنَ يَكۡفُرُونَ بِـٱللَّهِ وَرُسُـلِهِۦ وَيُرِيدُونَ أَن يُفَرِّقُـواْ بَيۡنَ ٱللَّهِ وَرُسُـلِهِۦ وَيَقُولُونَ نُؤۡمِنُ بِبَعۡضٍ وَنَكۡفُرُ بِبَعۡضٍ وَيُرِيدُونَ أَن يَتَّخِذُواْ بَيۡنَ ذَٰلِكَ سَبِيلًا ١٥٠ أُوْلَـٰٓئِكَ هُمُ ٱلۡكَـٰفِرُونَ حَقًّاۚ وَأَعۡتَدۡنَا لِلۡكَـٰفِرِينَ عَذَابًا مُّهِينًا ١٥١ وَٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ بِٱللَّهِ وَرُسُـلِهِۦ وَلَمۡ يُفَرِّقُواْ بَيۡنَ أَحَدٍ مِّنۡهُمۡ أُوْلَـٰٓئِكَ سَـوۡفَ يُؤۡتِيهِمۡ أُجُورَهُمۡۚ وَكَانَ ٱللَّهُ غَفُورًا رَّحِيمًا ١٥٢} [النساء: ١٥٠-١٥٢]

‹‹እነዚያ በአላህና በመልክተኞቹ የሚክዱ፣በአላህና በመልክተኞቹም መካከል መለያየትን የሚፈልጉ፣በከፊሉም እናምናለን፣በከፊሉም እንክዳለን የሚሉ፣በዚህም መካከል መንገድን ሊይዙ የሚፈልጉ፤እነዚያ በውነት ከሓዲዎቹ እነርሱ ናቸው:: ለከሓዲዎችም አዋራጅን ቅጣት አዘጋጅተናል:: እነዚያም በአላህና በመልክተኞቹ ያመኑ፣ከነሱም ያልለዩ፣እነዚያ ምንዳዎቻቸውን በእርግጥ ይሰጣቸዋል:: አላህም መሓሪ አዛኝ ነው::››[አልኒሳእ፡150-152]

ዳሩ ግና እነዚህ የቀድሞ መጽሐፍት ብዙው ክፍላቸው ጠፍቷል፤አብዛኞቻቸው ከስመዋል፤ለመዛባት፣ለመጣመም፣ለብረዛና ለክለሳ ተጋልጠዋል::

ታላቁ ቁርኣን ግን አላህ (ሱ.ወ.) ከብረዛና ከክለሳ የመጠበቅ ኃላፊነቱን ለራሱ ወስዷል:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{إِنَّا نَحۡنُ نَزَّلۡنَا ٱلذِّكۡرَ وَإِنَّا لَهُۥ لَحَـٰفِظُونَ ٩} [الحجر: ٩]

‹‹እኛ ቁርኣንን እኛው አወረድነው፤እኛም ለርሱ ጠባቂዎቹ ነን::››[አል ሕጅር፡9]

በቀደሙት መለኮታዊ መጽሐፎች ላይ ተቆጣጣሪ፣ዋቢና ሻሪ አድርጎታልም:: ይህንኑ በማስመልከት አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦


{وَأَنزَلۡنَـآ إِلَيۡكَ ٱلۡكِتَـٰبَ بِٱلۡحَقِّ مُصَدِّقًا لِّمَا بَـيۡنَ يَدَيۡهِ مِنَ ٱلۡكِتَـٰبِ وَمُهَيۡمِنًا عَلَيۡهِ} [المائدة: ٤٨]

‹‹ወደ አንተም መጽሐፉን ከበፊቱ ያለውን መጽሐፍ አረጋጋጭና በርሱ ላይ ተጠባባቂ [ተቆጣጣሪ] ሲኾን በውነት አወረድን፤››[አልማእዳህ፡48]

ለሁሉም ነገር አብራሪና መሪ አድርጎት ያስተላለፈው መሆኑንም ገልጾአል፦

### ቁርኣን . . የመጨረሻው መለኮታዊ መጽሐፍ

‹‹በተውሒድ ባመንኩበት ቅጽበት፣ቁርኣን የአላህ መጽሐፍ መሆኑንና የመጨረሻውና የማጠቃለያው መለኮታዊ መጽሐፍ መሆኑን የሚየረጋግጡ ማስረጃዎችን መፈተሽ ጀመርኩ:: ለዚህ ጉዳይ መፍትሔ እንዳገኝ ያስቻለኝን አላህ አመሰግናለሁ:: ቅዱስ ቁርኣን ለተቀሩት መለኮታዊ መጽሐፎች ሁሉ ዕውቅና የሚሰጥ ብቸኛው መለኮታዊ መጽሐፍ ነው:: የተቀሩት ግን አንዱ ሌላውን ያስተባብላል:: ይህ በእርግጥ ቅዱስ ቁርኣንን ልዩ ከሚያደርጉት ባህርያት አንዱ ነው::››



በሺርሻድ ሕንዳዊ ሰባኪ.



### የቁርኣን ደረጃና ትሩፋቱ

‹‹ቁርኣን ምናባቸውን ሲቀሰቅስ፣ስነምግባራቸውን ሲቀርጽ፣በመቶ ሚሊዮኖች የመቆጠሩ ሰዎችን አእምሮና እሳቤ ሲሞርድ ለአስራ አራት ምእተ ዓመታት በሙስሊሞች ትውስታ ውስጥ ተጠብቆ ኖሯል:: ቁርኣን ከሁሉም ይበልጥ ገርና ቀለል ያለ፣ከሁሉም ይበልጥ ከውስብስብነት፣ከድፍንፍን ምስጢራት፣ከካህናዊ ጣዖታዊ ስርዓታት የጸዳ ዐቂዳን በሰው ልቦና ውስጥ በሰው ልቦና ውስጥ ይተክላል:: የሙስሊሞችን የስነምግባርና የስልጣኔ ደረጃን ከፍ በማድረግ ረገድም ትልቁን ሚና ተጫውቷል:: የማሕበራዊ አነዋነዋርና የማሕበረሰባዊ አንድነት ስርዓት መሰረቶችን የተከለላቸውም እርሱ ነው:: የጤና አጠባበቅ ሕጎችን እንዲከብሩ አበረታቷል:: አእምሮአቸውንም ከብዙ አፈተረቶችና ግምታዊ ቅዠቶች፣ከግፍና ከጭካኔ ነጻ አውጥቷል:: የጫንቃ ተገዥዎችን ሁኔታዎችም አሻሽሏል:: ግፉአን ተዋራጆች በነበሩት ልብ ውስጥም የክብርና የልዕልና መንፈስ ዘርቷል::››

ዎል ዲዮራንት

አሜሪካዊ ደራሲ.

https://www.path-2-happiness.com/am

{وَنَزَّلْنَا عَلَيْكَ ٱلْكِتَـٰبَ تِبْيَـٰنًا لِّكُلِّ شَىْءٍ وَهُدًى وَرَحْمَةً وَبُشْرَىٰ لِلْمُسْلِمِينَ ﴿٨٩﴾}[النحل: ٨٩]

‹‹መጽሐፉንም፣ለሁሉ ነገር አብራሪ፣መሪም እዝነትም፣ለሙስሊሞችም አብሳሪ ኾኖ ባንተ ላይ አወረድነው፡፡››[አል ነሕል፡89]

ቁርኣን መመሪያ እዝነትና በረከት መሆኑን ሲገልጽም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{فَقَدْ جَآءَكُم بَيِّنَةٌ مِّن رَّبِّكُمْ وَهُدًى وَرَحْمَةٌ}[الأنعام: ١٥٧]

‹‹ስለዚህ ከጌታችሁ ግልጽ ማስረጃ መምሪያም፣እዝነትም በእርግጥ መጣላችሁ፤››[አልአንዓም፡157]

ወደ ቀጥተኛው መንገድ የሚወስድ መጽሐፍም ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{إِنَّ هَـٰذَا ٱلْقُرْءَانَ يَهْدِى لِلَّتِى هِىَ أَقْوَمُ وَيُبَشِّرُ ٱلْمُؤْمِنِينَ ٱلَّذِينَ يَعْمَلُونَ ٱلصَّـٰلِحَـٰتِ أَنَّ لَهُمْ أَجْرًا كَبِيرًا ﴿٩﴾}[الإسراء: ٩]


‹‹ይህ ቁርኣን ወደዚያች፣እርሷ ቀጥተኛ ወደ ኾነችው መንገድ ይመራል፤እነዚያንም በጎ የሚሠሩትን ምእመናን ለነሱ ታላቅ ምንዳ ያላቸው መኾኑን ያበስራል፡፡››[አልእስራእ፡9]

የሰው ልጆችን በሁሉም የሕይወት ፈርጆችና የኑሮ ጉዳዮቻቸው ወደ ተመራጩ ቀጥተኛ ጎዳና ይመራቸዋል፡፡

ታላቁ ሕያው መጽሐፍ ቁርኣን ለሰው ልጆች አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ሁሉ በምልዓት ያካተተ፣መሰረታዊ መርሆዎችን፣የእምነትና የዐቂዳ፣የሕግጋትና የበይነሰባዊ ግንኙነት፣የስነምግባርና የግብረገብነት . . መሰረቶችን አቅፎ ይዟል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{مَّا فَرَّطْنَا فِى ٱلْكِتَـٰبِ مِن شَىْءٍ}[الأنعام: ٣٨]

‹‹በመጽሐፉ ውስጥ ምንም ነገር [ሳንገልጽ] አልተውንም፡፡››[አል አንዓም፡38]



## ሁሉን ያካተተ መጽሐፍ

‹‹ቁርኣን የስልጠና እና የስልጣኔ መጽሐፍ ነው፡፡ ያካተታቸው ነገሮች ሁሉ ስለግዴታዎችና ስለ አምልኮተ አላህ አፈጻጸም ብቻ የሚናገሩ አይሉለም፡፡ ሙስሊሞች የሚያበረታቷቸው ግብረገብነትና የትሩፋት ሥራዎች ከሁሉም በላይ ውብ ድንቅና በስነምግባር መለኪያዎች ከሁሉም ይበልጥ ሚዛን የሚደፉ ናቸው፡፡ የመጽሐፉ ቅን አመራር በትእዛዛቱ እንደሚንጸባረቅ ሁሉ በእገዳዎቹም ይንጸባረቃል፡፡››

ሲድኒ ፊሽር

የአሜሪካው ኦሃዮ ዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰር



## ለ - ነቢያዊው ሱንና (ፈለግ)፦

አላህ (ሱ.ወ.) ቅዱስ ቁርኣንን ወደ መልክተኛው ﷺ ሲያስተላልፍ ነቢያዊውን ሱንናም አስተላልፎላቸዋል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{إِنْ هُوَ إِلَّا وَحْىٌ يُوحَىٰ ﴿٤﴾}[النجم:٤]

‹‹እርሱ (ንግግሩ) የሚወረድ ራእይ እንጅ ሌላ አይደለም፡፡››[አልነጅም፡4]

ሱንና እንደ ቁርኣን ሲሆን ይህንኑ በማስመልከት ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹ንቁ ዕወቁ! መጽሐፉና መሰሉ (ሱንና) አብረው ተሰጥቶኛል፡፡ መጽሐፉና መሰሉ (ሱንና) አብረው ተሰጥቶኛል፡፡›› [በአሕመድ የተዘገበ] ነቢዩ ﷺ ለሰዎች የሚያደርሱት እንዲያደርሱ ከአላህ የታዘዙትን ብቻ ነው፡፡ አላህ የታዘዙትን ብቻ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦



### ተወዳጁ ሱንና

‹‹በምድር ላይ ከተሰራጩ በመቶዎች ሚሊዮኖች ከሚቀጠሩ ሰዎች ልብ በሚፈልቅ ታላቅ ሃይማኖታዊ ፍጹምነት እየተበጠረና እየተለወለ፣ድንቁ የሙሐመድ ሱንና እስከ ዛሬው ዘመናችን ድረስ ተጠብቆ ቆይቷል፡፡

ኢይቴን ዲነህ

ፈረንሳዊ ሰዓሊና ፈላስፋ

{إِنْ أَتَّبِعُ إِلَّا مَا يُوحَىٰٓ إِلَىَّ وَمَآ أَنَا۠ إِلَّا نَذِيرٌ مُّبِينٌ ﴿٩﴾}[الأحقاف: ٩]

‹‹ወደኔ የሚወረደውን እንጅ ሌላ አልከተልም፤እኔም ግልጽ አስፈራሪ [አስጠንቃቂ] እንጅ ሌላ አይደለሁም በላቸው፡፡››[አልአሕቃፍ፡9]

በመሆኑም ነቢያዊው ሱንና ሁለተኛው የእስላም የሕግ ምንጭ ነው፡፡ ሱንና እስከ ነቢዩ ﷺ ድረስ በሚዘልቅ ትክክለኛና አስተማማኝ የዘገባ ሰንሰለት የተዘገበ የነቢዩ ንግግር፣ተግባር፣ገለጻ ወይ



https://www.path-2-happiness.com/am

ማረጋገጫ ሲሆን የቅዱስ ቁርኣን ተግባራዊ ማብራሪያ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) በቁርኣን ውስጥ የተካተቱ ጠቅለል ያሉ ወይም ማብራሪያና ገለጻ የሚሹ ጉዳዮችን እንዲያብራሩና እንዲተነትኑ ለነቢዩ ﷺ ፈቅዶላቸዋል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَأَنزَلْنَآ إِلَيْكَ ٱلذِّكْرَ لِتُبَيِّنَ لِلنَّاسِ مَا نُزِّلَ إِلَيْهِمْ وَلَعَلَّهُمْ يَتَفَكَّرُونَ ﴿٤٤﴾} [النحل: ٤٤]

‹‹ወደ አንተም ለሰዎች ወደነሱ የተወረደውን (ፍች) ልትገልጽላቸውና ያስተነትኑም ዘንድ ቁርኣንን አወረድን፡፡››[አልነሕል፡44]

እናም ሱንና ቅዱስ ቁርኣንን ያብራራል፤አንቀጾቹን ይተነትናል፤ጠቅለል ያሉ ድንጋጌዎቹን ይዘረዝራል፡፡ ነቢዩ ﷺ ወደርሳቸው የወረደውን ቁርኣን አንቀጾች አንዴ በአንደበታቸው ሌላ ጊዜ ደግሞ በተግባራቸው አንዳንዴም በሁለቱም ጭምር ያብራሩ ነበር፡፡ ሱንና አንዳንድ ሕጎችንና ድንጋጌዎችን በማብራራት ረገድ ራሱን ችሎ የሚመጣበት ሁኔታም ሊኖር ይችላል፡፡

ነቢዩ ﷺ ከአላህ የታዘዙትን በትጋት ይፈጽሙና ለሰዎች ያብራሩ ስለነበር፣እርሳቸው የሰሩትን አይተው እንዲሰሩ ያዙ ስለነበር የጠራው ነቢያዊ ሱንና የእስላም ሕግጋት እምነት፣አምልኮተ አላህ፣በይነሰባዊ ግንኙነቶችና የስነምግባር ደንቦች ተግባራዊ ማብራሪያና መገለጫ ነው፡፡ እምነታቸው ምሉእ ይሆን ዘንድ ምእመናን በተግባራቸውና በአንደበታቸውም የነቢዩን ﷺ አርኣያ እንዲከተሉ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ሲል አዟል፦



### ቁርኣንና ሐዲስ መሳ ለመሳ

‹‹የነቢዩ ሙሐመድን ሥራዎችና መመሪያዎች የሚመለከቱ ንግግሮች ስብስብ ተደርጎ የሚቆጠረው ሐዲስ የቁርኣን መሙያ (ማብራሪያ) ነው፡፡ አንድ ሰው ሐዲስ ውስጥ ከሕይወት ተለዋዋጭ እውነታዎች አንጻር የስነምግባሩ መሰረታዊ አካል የሆነውንና በነቢዩ ሙሐመድ አእምሮ ውስጥ ይመላለስ የነበረውን ነገር ያገኛል፡፡ ሱንና የቁርኣን ማብራሪያ በመሆኑ አስፈላጊነቱ የግድ ነው፡፡››

**ጃክ ሪሳር**

**ፈረንሳዊ ኦሪየንታሊስት**

{لَّقَدْ كَانَ لَكُمْ فِى رَسُولِ ٱللَّهِ أُسْوَةٌ حَسَنَةٌ لِّمَن كَانَ يَرْجُوا۟ ٱللَّهَ وَٱلْيَوْمَ ٱلْءَاخِرَ وَذَكَرَ ٱللَّهَ كَثِيرًا ﴿٢١﴾} [الأحزاب: ٢١]

‹‹ለናንተ፣አላህንና የመጨረሻውን ቀን የሚከጅል ለኾነ ሰው፣አላህንም በብዙ ለሚያወሳ፣በአላህ መልክተኛ መልካም መከተል [አርአያ] አላቸው፡፡››[አል አሕዛብ፡21]

ክቡራን የነቢዩ ባልደረቦች (ሶሓባ) የነቢዩን ﷺ ንግግሮችና ሥራዎቻቸውን ለቀጣዩ ትውልድ ያስተላለፉ ሲሆን ቀጣዩ ትውልድም ሱንናቸውን በመድብሎች ሰብስቦ በማጠናቀር አቆይቶልናል፡፡ የሱንና ዘጋቢዎችና አጠናቃሪዎች በዘገባ ሰንሰለት አበጣጠርና በሀዲስ አሰባሰብ ላይ ጥብቅ መስፈርቶችን ይከተሉ ስለነበር፣የዘገባ ሰንሰለቱ እስከ ነቢዩ ﷺ ድረስ የሚዘልቅ ይሆን ዘንድ ሐዲሱን የሰማው ሰው ከሰማበት ሰው ጋር በአካል የተገናኘ ዘመነኛው መሆንን፣በዘገባ ሰንሰለቱ ውስጥ የሚገኙ ዘጋቢዎች ሁሉ በሃይማኖታቸው በመልካም ስነምግባራቸው የታመኑ፣እምነት የሚጣልባቸው ፍትሐዊነትን የተላበሱ ታማኞች መሆንን ለሐዲሱ ትክክለኛነት በመመዘኛነት ያስቀምጡ ነበር፡፡

ቁርኣንና ሱንና ማመሳከሪያ ዋቢና ያዘዙትን መፈጸም ከከለከሉትም መከልከል የሚገባ ሁለቱ መሰረታዊ የእስላም የሕግ ምንጮች መሆናቸውን አምኖ መቀበል ግዴታ ነው፡፡ በሁለቱ ምንጮች ውስጥ የሰፈረው ሁሉ እውነት መሆኑን፣የአላህ (ሱ.ወ.)ስሞች፣ባሕርያትና ተግባራት አስመልክቶ በውስጣቸው በቀረበው




### የተበረከተው ሱንና

‹‹የሙሐመድን ሱንና መተግበር የእስላምን ሕልውና እና ዕድገቱን ጠብቆ ለማቆት መሥራት ማለት ነው፡፡ ሱንናን መተውም እስላምን ማክሰም ማለት ነው፡፡ ሱንና እስላም የታነጸበት የብረት መዋቅርና መሰረት ነው፡፡ ያንድን ሕንጻ መሰረትና መዋቅር ካስወገድክ ሕንጻው የካርቶን ቤት ይመስል ፍርክስክስ ቢል ያስገርማልን?! ››

**ሊዮፖ`ርድ ፋይስ**

**ነምሳዊ ፈላስፋ**







https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am

ሁሉ ማመንና፣አላህ (ሱ.ወ.) ለምእመናን ወዳጆቹ ያዘጋጀላቸው ታላቅ ምንዳና ለአስተባባይ ከሃዲዎች ያሰናዳው መራር ቅጣትም ፍጹም እውነት መሆኑን ማመን ግዴታ ነው:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{فَلَا وَرَبِّكَ لَا يُؤْمِنُونَ حَتَّىٰ يُحَكِّمُوكَ فِيمَا شَجَرَ بَيْنَهُمْ ثُمَّ لَا يَجِدُوا فِي أَنفُسِهِمْ حَرَجًا مِّمَّا قَضَيْتَ وَيُسَلِّمُوا تَسْلِيمًا ﴿٦٥﴾}[النساء: ٦٥]

‹‹በጌታህም እምላለሁ (አላህ በራሱ መማሉ ነው) በመካከላቸው በተከራከሩበት ፍርድ እስከሚያስፈርዱህ፣ከዚያም ከፈረድከው ነገር በነፍሶቻቸው ውስጥ ጭንቀትን እስከማያገኙና ፍጹም መታዘዝን እስከሚታዘዙ ድረስ አያምኑም (ምእመን አይኾኑም)::››[አልኒሳእ፡65]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَمَا آتَاكُمُ الرَّسُولُ فَخُذُوهُ وَمَا نَهَاكُمْ عَنْهُ فَانتَهُوا}[الحشر: ٧]

‹‹መልክተኛውም የሰጣችሁን (ማንኛውንም) ነገር ያዙት:: ከርሱም የከለከላችሁን ነገር ተከልከሉ::››[አልሐሽር፡7]


ይህን መንገድ የተከተለ ሰው ምንኛ ታደለ!! የመታደል መንገድም ይህ ነውና!!


## የነቢያዊው ሱንና አሰባሰብ

‹‹በስብስባቸው ሱንናን የሚመሰርቱት እነዚህ ሐዲሶች በአመራረጣቸው ላይ ጥብቅ የሆነ ከፍተኛ ፍተሻ ከማድረግ ጋር በነቢዩ ባልደረቦች ተዘግበው ወይም ከነሱ ተላልፈው የተጠናቀሩ ናቸው::››

ጆሳክ ሪሳር

ፈረንሳዊ ኦሪየንታሊስት





https://www.path-2-happiness.com/am